የመንገድ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ መጓተት - ማነጋገሩን ቀጥሏል
ገጽ 10

ተፈጥሮ እና ሰው
(ቅድመ እና ድህረ 1800)
ገጽ 11

"ከስጋ ደዌ በሽታ መዳን ይቻላል"
ገጽ 12





# እፍድ አዲስ ዘመን

83ኛ ዓመት ቁጥር 145 ጥር 25 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 **ቅዳሜ** ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







ፎቶ፡ አሸናፊ ጉደታ

# በተለያዩ መስኮች

## ለተመዘገቡ ውጤቶች የሚዲያና የኮሙኒኬሽን ዘርፉ አዎንታዊ ሚና ተጫውቷል

**አዲሱ ገረመው**

አዳማ፡- በኢትዮጵያ በተለያዩ መስኮች ለተመዘገቡ ውጤቶች የሚዲያና የኮሙኒኬሽን ዘርፉ አዎንታዊ ሚናውን በተደራጀ መንገድ መወጣቱን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ፡፡

«ውጤታማ ተግባቦት ለኢትዮጵያ ልዕልና» በሚል መሪ ሃሳብ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ተቋማት የጋራ ጉባኤ በአዳማ ከተማ ተካሂዷል፡፡

በጉባኤው መክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር)፣

በተለያዩ መስኮች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## «አፍሪካውያን ነፃ ታሪክና ባህል ምን እንደሚመስል መጥተው እንዲመለከቱ ጥሪ አቀርባለሁ»

- ኮሎኔል ማንግኦንግ አንያጃንግ ዳት ደቡብ ሱዳናዊ የዋር ኮሌጅ ሠልጣኝ

ገጽ 4



አቶ ኃይሉ አዱኛ

## ሸኔ የሽብር ተግባሩን ወደ ከተማ ለማምጣት ያደረገው ጥረት ከሽፏል

- በኦሮሚያ 253 ሚሊዮን ኩንታል ሰብል ተሰብስቧል

ገጽ 4

# የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ለአራት ወራት ተራዘመ

- ተጠርጣሪዎችን ፍርድ ቤት የማቅረብ ሥራ እንዲጀመር ምክር ቤቱ አሳስቧል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚስተዋሉ የጸጥታ ስጋቶችንና የተደቀነውን የጸጥታ ስጋት ሙሉ ለሙሉ ለመቀልበስ ቀሪ ሥራዎችንም ለማጠናቀቅ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ለአራት ወራት እንዲራዘም ወሰነ፡፡ ተጠርጣሪዎችን ፍርድ ቤት የማቅረብ ሥራ እንዲጀመርም አሳስቧል፡፡

ምክር ቤቱ ትናንት ባካሄደው 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 1ኛ ልዩ ስብሰባ በጉዳዩ ላይ ውይይት ካካሄደ በኋላ

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









# «መንግሥት የፕሪቶሪያው ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆን ከአቋም ባሻገር ተግባራዊ እንቅስቃሴ አድርጓል»

*- የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት የፕሪቶሪያው ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆን ከአቋም ባሻገር ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረጉን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለፀ፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የፕሪቶሪያው ስምምነት አተገባበርን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ ሕወሓት ከሰሞኑ ባወጣው መግለጫ የፕሪቶሪያው ስምምነት እንዲከበር መጠየቁን የፌዴራል መንግሥት በአንክሮ እንደተመለከተው አስታውቋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ዋነኛው መፍትሔ የፕሪቶሪያውን ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ መሆኑን የኢፌዴሪ መንግሥት በጽኑ ያምናል። ይሄንንም በተመለከተ የፌዴራሉ መንግሥት ከመነሻው እስካሁን ያለው አቋም ወጥ እና የማይናወጥ መሆኑን ጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የፕሪቶሪያው ከአቋም ባሻገር ተግባራዊ እንቅስቃሴም አድርጓል፤ እያደረገ ይገኛል ሲል አመላክቷል።

አገልግሎቱ እንደገለጸው፤ ለትግራይ ሕዝብ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ እንዲቻል የባንክ፣

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

የቴሌኮም፣ የመንገድ፣ የጤና፣ የትምህርትና የርዳታ ሥራዎችን የሚመሩ የሥራ ኃላፊዎች በትግራይ ተገኝተው ከክልሉ ቢሮዎች ጋር እንዲወያዩ የተደረገው የፕሪቶሪያ ስምምነት በተፈረመ በሳምንታት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

በትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም በኩል 165 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር በዕቅድ ተካትቶ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ወደ ሥራ እንዲገባ መደረጉንና ለአንደኛና ለሁለተኛ ሩብ ዓመታት ማስፈጸሚያ 517 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር በገንዘብ ሚ/ር በኩል ለክልሉ መላኩን አገልግሎቱ አረጋግጧል።

በትምህርት ላይ ከሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት አንድ ነጥብ 46 ቢሊዮን ብር ድጋፍ መደረጉን አስታውሶ፤ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደርም ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ እና ለመንገድ ፕሮጀክት ጥገና ከ418.6 ሚሊዮን ብር በላይ ወደ ክልሉ መላኩን ገልጿል።

በክልሉ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎችን መልሶ ወደ ሥራ ለማስገባት በተደረገው ሁለገብ እንቅስቃሴ 217 ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ ለማስገባት እንደተቻለ አገልግሎቱ ጠቁሟል።

በጤናው ዘርፍ የተለያዩ የኩፍኝና ኮቪድ ክትባቶች መሰጠታቸውንና በ2015/16 በጀት ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ከ600 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ለትግራይ ክልል የጤና ዘርፍ የገንዘብና የግብአት ድጋፍ እንደተደረገ አስታውቋል።

በሌላ በኩል በ2015/16 ዓ.ም 13 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለክልሉ የቀረበ ሲሆን፣ ለ1427 አርሶ አደሮች መጠቀሚያ የሚሆን 1720 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ በዚሁ የምርት ዘመን ፕሮጀክቶች በኩል ለክልሉ ተገዝቶ ሥራ ላይ መዋሉን አመላክቷል።

እንደ መግለጫው ከሆነ፤ የዊዝሆልዲንግ ታክሶችን ጨምሮ ብር 3.9 ቢሊዮን ብር ወደ ክልሉ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ከክልሉ ግብር ከፋዮች የተሰበሰበ ብር ከ138 ሚሊዮን ብር በላይ ወደ ክልሉ ሂሳብ ተላልፏል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለተጠቀሱትና ለሌሎችም ወጪዎች ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ ከ37 ቢሊዮን ብር በላይ የፌዴራል መንግሥት ለትግራይ ክልል ድጋፍ መደረጉን አስታውቋል።

በተመደበው በጀትና ድጋፍ የክልሉ ዕቅድ ተግባራዊ ተደርጎ ለሕዝብ ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣም ይጠብቃል ሲል መንግሥት አመላክቷል።

ተፈናቃዮችን ወደ መደበኛ መኖሪያቸው ለመመለስ እንዲቻል የፌዴራሉ መንግሥት የሚመለከታቸውን አካላት አቀናጅቶ ሥራ ጀምሯል ሲል አገልግሎቱ ጠቁሟል።

አሁንም ቢሆን ለትግራይና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም፣ ልማትና ደኅንነት ሲባል የፕሪቶሪያውን ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ በሚያደርጉ፤ የክልሉን ዕቅዶች ወደ መሬት በሚያወርዱ፤ የክልሉን ሕዝብ ችግሮች በተጨባጭ ለመፍታት በሚያስችሉ ገቢራዊ ነገሮች ላይ ማተኮር አማራጭ የሌለው ነው ብሎ የፌዴራሉ መንግሥት እንደሚያምን ገልጿል።

የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትም ለፕሪቶሪያው ሰላም ስምምነት መፈጸም ሙሉ ድጋፋቸውን እንዲያደርጉ የፌዴራል መንግሥት ጥሪውን አቅርቧል።



ሎሬት ፕሮፌሰር ጥሩሰው ተፈራ እና አምባሳደር ሱሌማን ደደፎ

## ተቋሙ ሰው ሠራሽ ድጋፍ አምርቶ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ሰው ሠራሽ ድጋፍ አምርቶ ለአካል ጉዳተኞች በበቂ ሁኔታ ተደራሽ ለማድረግ በትኩረት እንደሚሠራ የኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ለአካል ጉዳተኞች ሰው ሠራሽ ድጋፍ ለማምረትና ለመጠገን ከሁሉም የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች በጎ አድራጎት ማኅበር ጋር ትናንት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል።

በስምምነቱ ወቅት የኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አምባሳደር ሱሌማን ደደፎ እንደተናገሩት፤ ተቋሙ ሰው ሠራሽ የአካል ድጋፍ በማምረትና በመጠገን ለአካል ጉዳተኞች በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ በትኩረት ይሠራል።

ስምምነቱ አካል ጉዳተኞች የሚስፈልጋቸውን ዊልቼይር፣ ለመንቀሳቀስ የሚረዱ ክራንቾች፣ ማየት ለተሳናቸው ደግሞ መምሪያ ዘንግና ሌሎች መሣሪያዎችን በሙሉ አቅም ለማምረትና ለመጠገን የሚያስችል ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ከውጭ ሀገራት በከፍተኛ ምንዛሬ ወጪ የሚገባውን የአካል ጉዳተኞች ሰው ሠራሽ ድጋፍ ቁሳቁስ በሀገር ውስጥ ለማምረትና የገበያውን ክፍተት ለመሙላት ጥረት ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

ስምምነቱ ተቋሙ ለአካል ጉዳተኞች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን አምርቶ ተደራሽ በማድረግ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት እየሠራ ስለመሆኑ አንዱ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

አካል ጉዳተኞች የማኅበረሰቡ አንድ አካል እንደመሆናቸው የሚያፈልጋቸውን ግብዓት የማሟላት፣ የመደገፍ፣ ሰብዓዊ መብታቸውን ማስከበርና እኩል ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ይገባል፤ ለዚህም ተቋሙ የሚቻለውን ያደርጋል ብለዋል፡፡

በታዳጊ ሀገራት አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሰው ጫና ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመው፤ የሚደርሰውን ጫና በማቃለል ሁለተናዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥና ማኅበረሰቡም ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራበት እንደሚገባ አመላክተዋል።

የሁሉም የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኛ በጎ አድራጎት ማኅበር ምክትል ቦርድ ሰብሳቢ ሎሬት ፕሮፌሰር ጥሩሰው ተፈራ በበኩላቸው፤ ለአካል ጉዳተኞች የሚያስፈልጉ ሰው ሠራሽ ድጋፎችን በማምረትና የተበላሹትን በመጠገን ተደራሽ ማድረግ ማኅበራዊ ኃላፊነትን መወጣት የሚያስችል ተልዕኮ ነው።

የአካል ጉዳተኞች ሰው ሠራሽ ድጋፎች በሀገር ውስጥ መመረታቸው ከፍተኛ ወጪን ያስቀራል፤ በበቂ ሁኔታም ተደራሽ ለማድረግም ይጠቅማል ሲሉ አስረድተዋል።

ምክትል ቦርድ ሰብሳቢው እንዳመለከቱት፤ በርካታ የአካል ጉዳተኞች ሀገር ውስጥ ይገኛሉ። ለአካል ጉዳተኞች የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማሟላት ሰፊ ሀብት የሚጠይቅ በመሆኑ ማኅበረሰቡ ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራበት ይገባል፡፡

ስምምነቱ ከውጭ የሚገቡ የአካል ጉዳተኞች የሰው አካል ድጋፎችንና ለትምህርት የሚስፈልጉ ግብዓቶችን ለማቅረብ እንደሚያስችል ተጠቁሟል።



## የቤት ልማት ዘርፉን የሚረዳ ኤክስፖ ሊዘጋጅ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በቤት ልማት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች እና የቴክኖሎጂ አካላትን ያሳተፈ የቤት ልማት ዘርፉን የሚያጠናክር ኤክስፖ ለሁለተኛ ጊዜ ሊያዘጋጅ መሆኑን አርኪ ኤቨንት ኦርጋናይዘር አስታወቀ፡፡ ዝግጅቱ ከየካቲት 15 እስከ 17 ቀን 2016 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ ይካሄዳል፡፡

የአርኪ ኤቨንት ኦርጋናይዘር ሥራ አስኪያጅ አቶ ቢኒያም ግርማ ኤክስፖውን አስመልክቶ በሰጡት መግለጫው ወቅት እንዳሉት፤ የቤት ልማት ዘርፍን ለማጠናከር በዘርፉ የሚገኙ ባለሀብቶችና የቴክኖሎጂ ፈጣሪዎችን ያሳተፈ ኤክስፖ ለሁለተኛ ጊዜ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ኤክስፖው በቤት ግንባታ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች፤ ከቴክኖሎጂ አሠራር ሥርዓትና ፕሮጀክት ውጤታማነት አንፃር የእርስ በርስ የሃሳብ ልውውጥ የሚያደርጉበት መድረክ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

በኤክስፖው ከባንክ፣ ፈርኒቸር አምራቾች እንዲሁም ቴክኖሎጂ አቅራቢ አካላትን ጨምሮ ከ70 በላይ ድርጅቶች እንደሚሳተፉበት የጠቀሱት አቶ ቢኒያም፤ ኤክስፖው በሚሊኒየም አዳራሽ እንደሚከናወን ጠቅሰዋል፡፡

በተጨማሪም በኢንቴርየር ዲዛይን (ቤት የማስዋብ አገልግሎት) ላይ የተሰማሩ እንዲሁም የእንጨት ሥራ ውጤቶችን የሚያመርቱ ድርጅቶች እንደሚሳተፉ ተናግረዋል፡፡

እነዚህ ድርጅቶች ግብይትን ከማዘመን እንዲሁም የቤት አስተዳደር ሥርዓት ከማቅለል አንፃር ያላቸው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ በዚህ ኤክስፖ የኅብረተሰቡን አቅምን ታሳቢ ያደረገ ዋጋ የሚያቀርቡ ሪልስቴቶች እንደሚሳተፉ አብራርተዋል፡፡

ሥራ አስከያጁ እንዳሉት፤ በአሁኑ ጊዜ በርካታ በቤት ግንባታ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች ይገኛሉ፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ በርካታ ቤት ፈላጊዎች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ኤክስፖው ሁሉንም በአንድ የሚያገናኝ ትልቅ መድረክ ነው፡፡

ድርጅቱ ከተለያዩ የመንግሥት ተቋማት ጋር እንደሚሠራ የጠቀሱት አቶ ቢኒያም፤ ዝግጅቱ ላይ በቤት ግንባታ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ከቴክኖሎጂ አሠራር ውጤታማነት አንፃር ሃሳብ የሚለዋወጡበት መድረክ እንደሚሆን ጠቁሟል።

ድርጅቱ ለሁለተኛ ጊዜ የሚያዘጋጀው ኤክስፖ ከመሆኑ አንፃር የነበሩት ክፍተቶች ተለይተው በጥንቃቄ እና በጥናት የተደገፈ ዝግጅት ማድረጉን አመልክተዋል። በተለይ ከተአማኒነት አንፃር በደንበኞች በኩል የሚነሱ ጥርጣሬዎች ምላሽ ያለው አሠራር የዘረጋ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በዝግጅቱ ላይ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እና ታዳሚዎች የሚገኙ ሲሆን በመርሃ ግብሩ ለቤት ገዢዎች የፓናል ውይይት፣ ሥልጠና እና ሌሎች ሁነቶችንም እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡



አቶ ደሳለኝ ወዳጄ

## የዴሞክራሲ ተቋማት በጀታቸውን በውጤታማነትና በማብቃቃት እንዲጠቀሙ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የመንግሥት የዴሞክራሲ ተቋማት የተያዘላቸውን በጀት በውጤታማነትና በማብቃቃት እንዲጠቀሙ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን የበጀትና የፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ለምክር ቤቱ ተጠሪ የሆኑ የዴሞክራሲ ተቋማትን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን 2016 በጀት የመንፈቅ ዓመት አፈጻጸም ገምግሟል።

የፕላን፣ የበጀትና የፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ደሳለኝ ወዳጄ በወቅቱ እንደገለጹት፤ የመንግሥት የዴሞክራሲ ተቋማት የተበጀተላቸውን በጀት በውጤታማነትና በማብቃቃት መጠቀም ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው፡፡

ያለውን በጀት አብቃቅቶ በውጤታማነት መጠቀም የግድ ይላል ያሉት አቶ ደሳለኝ፤ ለዚህም የግዥ እቅድ በማስቀመጥ በኤሌክትሮኒክስ መንገድ መፈጸም አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አቶ ደሳለኝ አክለውም፤ የሀብት አጠቃቀም ላይ ተገኘው የኦዲት ጉድለት ልክ ማረምና ማስተካከል ይጠይቃል ያሉ ሲሆን ካፒታል በጀት ላይ ዲጂታልና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እየሰፋ መሄድ አለበት ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ደሳለኝ ገለጻ፤ በጀቱን በወቅቱ ለታለመለት ዓላማ ማዋል እንዲቻል እንዲሁም በውጤታማነትና በቁጠባ ለመጠቀም ተቋማቱ ወደ ኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ መግባት አለባቸው፡፡

ፈጣን ቀልጣፋና ተዓማኒነት ያለው አገልግሎት ለማስጠት ተቋማቱ ወደ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ዘዴ መግባት እንዳለባቸው አቶ ደሳለኝ ተናግረዋል፡፡

አቶ ደሳለኝ አክለውም፤ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የግዥ እቅድ በማዘጋጀት በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ግዥ መፈጸም ከቻሉ የበጀት ብክነትና የመልካም አስተዳደር ችግር መቅረፍ ይችላሉ ሲሉ አስረድተዋል።

በቀረበው የበጀት ሪፖርት መሠረት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከዓመቱ 44 ነጥብ 2 በመቶ የበጀት አፈጻጸም ያለው ሲሆን፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈጻጸም ደግሞ 97 ነጥብ 8 በመቶ ነው፣ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 63 ነጥብ 4 በመቶ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ከሦስቱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት አበረታች ውጤት አስመዝግቧል ያሉት ሰብሳቢው፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አሠራሩን መከተል አለባቸው ብለዋል፡፡

ተቋማቱ እራሳቸውን ችለው እንዲንቀሳቀሱ ከአገልግሎት የሚገኝ ገቢ ላይም ትኩረት ማድረግ አለባቸው ያሉት አቶ ደሳለኝ፤ ዘመናዊ የንብረት አወጋገድ ሥርዓት መከተል እንዳለባቸውም አሳስበዋል፡፡

ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው ለተጨማሪ ወጪ እየዳረጉ በመሆኑ ተቋማቱ ያሏቸውን ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ማጠናቀቅ እንዳለባቸውም ጠቁመዋል።

በተጨማሪም አገልግሎት አሰጣጣቸውን ለማዘመን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በስምምነት እየሠሩ እንደሚገኙ ተቋማቱ በሪፖርታቸው አስታውቀዋል፡፡

# የባህል እሴቶችን በአግባቡ በማስተዋወቅ ለትውልድ ግንባታና ብልጽግና መጠቀም ይገባል

## - 15ተኛው ከተማ አቀፍ የባህል ፌስቲቫል ተከፍቷል

**ሄለን ወንድምነው**



ፎቶ ፡- ሀዱሽ አብርሃ

አዲስ አበባ፡- የባህል እሴቶችንና የጥበብ ውጤቶችን በአግባቡ በማወቅና በማስተዋወቅ ለትውልድ ግንባታና ለሀገር ሁለተናዊ ብልጽግና መጠቀም ይገባል ሲሉ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ቀጄላ መርዳሳ ገለጹ። 15ተኛው የከተማ አቀፍ የባህል ፌስቲቫ «ባህሎቻችንን ማወቅ፤ ስብራቶቻችንን መጠገን» በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት በጊዮን ሆቴል ተከፍቷል፡፡

ፌስቲቫሉን መርቀው የከፈቱት የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ቀጄላ መርዳሳ እንዳስታወቁት፤ በሥልጣኔ ሰበብ የረሳናቸውን ባህሎቻችንን እና የዕደ ጥበብ ውጤቶች በአግባቡ በመጠቀምና በማስተዋወቅ ለተተኪ ትውልድ ማሻገር ይገባል።

ትውልዱ አሁን ከገባበት የማንነት መደበላለቅ ወጥቶ በአንድነት ለመቆም የባህል እሴቶች ወሳኝነት አላቸው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በአግባቡ በመጠበቅ ለትውልድ ግንባታና ለሀገር ሁለተናዊ ብልጽግና መጠቀም እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡

ባህሉን የዘነጋ ከዛሬ ወደነገ ለመሻገር መሠረት አይኖረውም ያሉት ሚኒስትሩ፤ በሥልጣኔ ሰበብ የረሳናቸውን የባህል እሴቶች ባህሉን በአግባቡ ያወቀ ትውልድ ወደሚፈለገው የእድገት ደረጃ ለመሻገር ርምጃችንን ያፋጥነዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ትውልዱ የራሱን ባህል በመዘንጋት በባዕድ ሀገር ባህል ለመድመቅ እየተጣጣረ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ይህም የባህል ስብራታችንን የሚያጎላ፣ በአስተሳሰብና በተግባር የሚያደኸየን በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል ብለዋል፡፡

በትውልድ ቅብብሎሽ በርካታ ዓመታትን በመሻገር ዛሬ ላይ የደረሱ ባህሎቻችንንና የጥበብ ሀብቶቻችንን በአግባቡ በመጠበቅና ታሪካቸውን ጭምር በመገንዘብ ተተኪው ትውልድ የሀገሩን ሀብት ሊጠቀምበት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ባህልን በአግባቡ ማወቅ ትውልድን መታደግ፣ ሀገርን ማዳን እና ክፍተትን መሙላት በመሆኑ ዘርፉን ለመታደግ ለሚሠሩ አካላት ሁሉ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ድጋፍ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል፡፡

በከተማ ደረጃ የተዘጋጀው ፌስቲቫል ሀገሪቱ ያሏትን ባህላዊ እሴቶችና የዕደ ጥበብ ውጤቶችን ለማስተዋወቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው አመልክተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ ጃንጥራር ዓባይ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ባህልን ማስተዋወቅ ለከተማዋ ገጽታ ግንባታና ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የሕዝቦችን አንድነት ለማጠናከርና ለሀገራዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

በከተማ ደረጃ ባለፉት ዓመታት በተካሄዱት የባህል ፌስቲቫሎች የባህል ልውውጥ ከማድረግ በተጨማሪም መጤ ባህሎችን፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና አስተሳሰቦችን በተደራጀ መልኩ ከመመከት አንጻር አበረታች ውጤት እንደተገኘ ተናግረዋል፡፡

የማኅበረሰቡን ባህልና ማኅበራዊ እሴቶችን ለማስተዋወቅ፣ የሀገር በቀል ዕውቀትን ለማልማት እንዲሁም ለዕደጥበብ ውጤቶች የገበያ ትስስር ለመፍጠር ፌስቲቫሉ ከፍተኛ ሚና እንዳለው አመላክተዋል፡፡

ፌስቲቫሉ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስተጋብርን ለማጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸው፤ በቀጣይም ብዝሃነትን ባረጋገጠ መልኩ ለሚካሄዱ ፌስቲቫሎች ከተማ አስተዳደሩ ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል፡፡

በፌስቲቫሉ የተለያዩ ብሔሮች ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች፣ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የባህል መንደር ምስረታና የአኗኗር ዘይቤዎች ለዕይታ ቀርበዋል። ፌስቲቫሉ እስከ ጥር 26 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ለሕዝብ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡

በፌስቲቫሉ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት የተለያዩ የመንግሥት ባለሥልጣናትና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# «የእንስሳት ልማት ራሱን በቻለ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት አለመመራቱ ዕድገቱን ገድቦታል»

## - የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት

**ተስፋ ፈሩ**



ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ



ደሳለኝ ቤኛ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፡- የእንስሳት ልማት ራሱን በቻለ ሚኒስቴር መሥሪያቤት አለመመራቱ ዕድገቱን ገድቦታል ሲል የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የእንስሳት ልማት ራሱን በቻለ ሚኒስቴር መሥሪያቤት አለመመራቱና በአስተዳደር ረገድ ድርጅታዊ መዋቅሩ እስካሁን ድረስ ያልተረጋጋ መሆኑ ዕድገቱን ገድቦታል፡፡

ኢትዮጵያ ከ70 ሚሊዮን በላይ የእንስሳት ሀብት ባለቤት ብትሆንም ከዚህ ሀብት እዚህ ግባ የሚባል ጠቀሜታ እያገኘች አለመሆኗን የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በአስተዳደርና አመራር ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት የተረጋጋ አለመሆኑ ዕድገቱን እንደጎዳው ኢንስቲትዩታችን ያስጠናው ጥናት ግኝት አሳይቷል ብለዋል፡፡

አክለውም፤ «የእንስሳት ልማት አንድ ጊዜ በግብርና ሚኒስቴር ስር አንድ ክፍል ሆኖ ይቀመጣል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ የእንስሳትና የዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ተብሎ ይቋቋማል፡፡ የሚፈለገው ውጤት እንዲገኝ ከዚህ ወጥቶ ራሱን ችሎ መደራጀት አለበት» ብለዋል፡፡

ከቅርብ አመታት በፊት የነበረውና አሁን ያለው የስጋና ወተት ዋጋ የተራራቀ መሆኑን ያወሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ፍላጎቱ በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ የእንስሳት ሀብት ልማቱ ግን ከፍላጎቱ ጋር አብሮ እየሄደ ባለመሆኑ በዚሁ ከቀጠልን ስጋ፣ ወተትና እንቁላል ከውጭ ለማስገባት እንገደዳለን ሲሉ ስጋታቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በቀጣዮቹ አምስት አመታት የስጋ ፍላጎት እስከ ሁለት መቶ ፐርሰንት እንዲሁም የፍየልና በግ ፍላጎት እስከ 315 ፐርሰንት ሊጨምር ይችላል፡፡

ይህንን ግዙፍ ተጨማሪ ፍላጎት ቁጭ ብለን ማየት ስለሌለብን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ «በአፍሪካ በእንስሳ ሀብት አንደኝነትን ይዘን ተራብን፤ ስጋ ተወደደ እንዲሁም ለልጆቻችን ወተት አጣን ማለት ትርጉም የማይሰጥ ነው። ስለዚህ አስተዳደርና አደረጃጀት አስተካክለን የእንስሳት ልማት ለሀገራችን ኢኮኖሚ በቂ ጥቅም እንዲሰጥ ማድረግ አለብን ብለዋል፡፡

"Policies and Institutional Factors Affecting the Performances of the Ethiopian Livestock" በሚል ርዕስ ጥናት ያቀረቡት በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የእንስሳት ፖሊሲ ጥናት ፕሮግራም አስተባባሪው ደሳለኝ ቤኛ (ዶ/ር) በበኩላቸው ጥናቱ በእንስሳት ሀብት ፖሊሲ እና በመዋቅራዊ ሂደቱ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የጥናቱ የመጨረሻ ግኝት ምን እንደሆነ ሲያስረዱም፤ የእንስሳት ልማት ዘርፉ በዘልማድ ከሚከናወነው የተሻለ ደረጃ ላይ አልደረሰም፡፡ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚደረጉ ሙከራዎችና ጥረቶች እንዳሉ ሆነው ዘርፉ በፖሊሲ ባለመደገፉ ውጤት ሊመጣ አልቻለም፡፡ ጥሩ ፖሊሲ ቢኖር እንኳን ትግበራውን ለማከናወን የሚያስችል መዋቅር አልተዘረጋም የሚሉ ናቸው ብለዋል፡፡

የእንስሳት ምርቱ ከሕዝብ ብዛታችን እኩል እያደገ ባለመሆኑ ለወደፊቱ ከእንስሳት የሚገኙ አልሚ የሚባሉት ምግቦች እየጠፉ ሲሄዱ ኢትዮጵያ ብዙ ችግር ውስጥ ልትገባ እንደምትችል የጠቆሙት ዶክተሩ፤ ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬም እየቀነሰ ሲሄድ የሀገር ኢኮኖሚን እንደሚጎዳ ገልጸዋል፡፡

ተመራማሪው በጥናታቸው ማጠቃለያ ባቀረቡት ምክረ ሃሳብ የእንስሳት ልማቱ ራሱን የቻለ ፖሊሲ ያስፈልገዋል፤ በሀገሪቷ ኢኮኖሚ ላይ ካለው አስተዋጽኦ አንጻር በሚኒስቴር ደረጃ ተዋቅሮ ታች ድረስ ራሱን የቻለ መዋቅር ሊፈጠርለት ይገባል፤ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት እጅ ለእጅ ተያይዘው መሥራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡

# ሸኔ የሽብር ተግባሩን ወደ ከተማ ለማምጣት ያደረገው ጥረት ከሽፏል

## - በኦሮሚያ 253 ሚሊዮን ኩንታል ሰብል ተሰብስቧል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሸኔ በጫካ የጀመረውን የሽብር ተግባሩን ወደ ከተማ ለማምጣት ያደረገው ጥረት በማኅበረሰቡ ተሳትፎ መክሸፉን የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ፡፡ በኦሮሚያ ክልል 253 ሚሊዮን ኩንታል ሰብል መሰብሰቡ ተገልጿል።

የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ የክልሉን ሁለተኛ ሩብ ዓመት አፈጻጸምን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት፤ አሸባሪው ሸኔ በጫካ የጀመረውን የሽብር ተግባር ወደ ከተማ ለማምጣት ያደረገው ጥረት በኅብረተሰቡ ተሳትፎ ከሽፏል፡፡

አሸባሪው ሸኔ የተለያዩ ጥቃቶችን በንጹሃን ዜጎች ላይ፣ በሕዝብ ንብረት ላይ ባነጣጠረ መልኩ የሽብር ተግባሮችን ሲፈጽም ቆይቷል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ሰላማዊ መንገድን ባለመፈለግ ንጹሃን ላይ ያነጣጠረ የሽብር ተግባር በመፈጸም ይታወቃል ብለዋል፡፡

የሽብርተኛ ቡድኑ በተለያዩ አካባቢዎች እየተወሰዱ ያሉ ኦፕሬሽን ሥራዎችን መቋቋም የተሳነው መሆኑን ጠቅሰው፤ አሁን ሲቪል መስሎ በመንቀሳቀስ የተለያዩ የሽብር ተግባሮችን በማከናወን ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በሕዝቡ ዘንድ የፍርሀት ድባብን ለመፍጠር ተሽከርካሪዎችን የማቃጠል ርምጃ ተግባር ላይ መሰማራቱን ገልጸው፣ በኅብረተሰቡና በመንግሥት የተቀናጀ ሥራ የቡድኑን የገበያ አድማ ሙሉ በሙሉ ማክሸፍ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

ቡድኑ በጠራው አድማ የትራንስፖርትና ገበያ፣ ተማሪዎች ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ፣ ኢንቨስትመንት እንዳይኖር፣ የታመሙ እንዳይታከሙ ያደረገው ጥረት በማኅበረሰቡ ተሳትፎ መክሸፉንም አቶ ኃይሉ ገልጸዋል፡፡

የክልሉ ማኅበረሰብ ከጫፍ እስከ ጫፍ ሰላማዊ እንቅስቃሴውን መቀጠሉን በመግለጽ በተለይም ምዕራብ ኦሮሚያ የትራንስፖርት አገልግሎት ወደ መደበኛ ሁኔታ መመለሳቸውን አስረድተዋል፡፡

መንግሥት ከሽብርተኛው ቡድን ጋር የሚተባበሩ አካላት ላይ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ የሚወስድ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

በሌላ በኩል በ2015/16 የምርት ዘመን ዘጠኝ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በተለያዩ ሰብሎች ማልማት ተችሏል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ እስካሁን 253 ሚሊዮን ኩንታል የተለያዩ የሰብል ዓይነቶች ተሰብስቧል ብለዋል።

በበጋ የስንዴ ልማት ሁለት ነጥብ 78 ሚሊዮን ሄክታር በዘር መሸፈኑን ጠቅሰው፣ በዚህም 105 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ ገልጸዋል።

ለዜግነት አገልግሎት ማኅበረሰቡን በማሳተፍ በ65 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር የሚገመት ሥራዎች እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ የቡኡረ ቦሩ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት፣ የትምህርት ቤት እድሳት፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን መኖሪያ ቤት ግንባታና የአቅመ ደካሞች ቤት እድሳት መከናወናቸውን አስረድተዋል።

በተጨማሪ አራት ሺህ አምስት መቶ ቅድመ መደበኛ ቡኡረ ቦሩ ትምህርት ቤቶች ግንባታን በማጠናቀቅ ሦስት ሺህ 618 የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ መግባታቸውን በመግለጽ በተማሪዎች የትምህርት ቤት ምገባ አምስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ተማሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ጠቅሰዋል፡፡



# «አፍሪካውያን ነፃ ታሪክና ባህል ምን እንደሚመስል መጥተው እንዲመለከቱ ጥሪ አቀርባለሁ»

- ኮሎኔል ማንግኦንግ አንያጃንግ ዳት ደቡብ ሱዳናዊ የዋር ኮሌጅ ሠልጣኝ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- መቀመጫቸውን በኢትዮጵያ ያደረጉ ወታደራዊ አታሼዎች፣ ዲፕሎማቶችና አፍሪካውያን የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይን ጎብኝተው ነፃ ታሪክና ባህል ምን እንዲመስል እንዲመለከቱ ደቡብ ሱዳናዊው የዋር ኮሌጅ ሠልጣኝ ኮሎኔል ማንግኦንግ አንያጃንግ ዳት ጥሪ አቀረቡ፡፡

በመከላከያ ዋር ኮሌጅ እየሠለጠኑ ከሚገኙ አፍሪካውያን አንዱ የሆኑት ኮሎኔል ማንግኦንግ አንያጃንግ ዳት የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይን አስመልክተው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአውደ ርዕዩ ብዙ አፍሪካውያን በቅኝ ግዛት ሥር በነበሩበት ጊዜ ጭምር የተከናወኑ ሁነቶች በአግባቡ ተሰንደው የቀረቡበት ነው፡፡ በመሆኑም መቀመጫቸውን በኢትዮጵያ ያደረጉ ወታደራዊ አታሼዎች፣ ዲፕሎማቶችና አፍሪካውያን የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይን ጎብኝተው ነፃ ታሪክና ባህል ምን እንደሚመስል እንዲመለከቱ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይ በሕይወት ዘመኔ ካየኋቸው አስደሳች ነገሮች አንዱ ነው ያሉት ኮሎኔሉ፤ በመገናኛ ብዙኃን ጉዳዩን ተመልክተውት የነበረ ቢሆንም ቦታው ላይ ተገኝተው ሲመለከቱት እንዳስገረማቸው ጠቁመዋል፡፡

በአውደ ርዕይው ብዙ አፍሪካውያን በቅኝ ግዛት ሥር በነበሩበትጊዜጀምሮየተከናወኑሁነቶችጭምርየቀረቡበት መሆኑን ጠቅሰው፤ የተገለጡት ታሪኮች ነፃ ታሪኮችና ባህሎች ምን እንደሚመስሉ ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው።

አውደ ርዕይው በአፍሪካ ያለውን የአሠራር ሥርዓት፣ አስተሳሰብና ያልተበረዘና ነፃ የሆነ ታሪክ እንዲሁም ባህል መጥተው እንዲመለከቱና የሁላችንም ታሪክ በአግባቡ የተገለጸበት ስለሆነ እንዲኮሩበት እጋብዛለሁ ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ አፍሪካውያን ነፃነታቸውን እንዲጎናጸፉ በማድረግ በኩል ትልቅ ሚና እንደነበራት ጠቁመው፤ ዛሬም እንደ አህጉር ሽብርተኝነትን ጨምሮ በርካታ የጋራ ተግዳሮቶች አሉባቸው፡፡

እነዚህን ተግዳሮቶች ለመሻገር፣ ጠንካራና የበለጸገች አፍሪካን እውን ለማድረግ አንድነታቸውን ማጠናከር እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በመተባበር ያዘጋጀው «ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን» የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ሳምንት አንድ አካል ሆኖ ጥር 2 ቀን 2016 ዓ.ም በኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ መከፈቱ ይታወሳል፡፡

# በተለያዩ መስኮች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ ሀገር በተለያዩ መስኮች ለተመዘገቡ ውጤቶች የሚዲያና የኮሙኒኬሽን ዘርፉ አዎንታዊ ሚናውን በተደራጀ መንገድ መወጣቱን አስታውቀዋል። ይህንን በይበልጥ ማጐልበት ያስፈልጋልም ብለዋል።

ተልዕኳችን የተቀናጀና የተናበበ የተግባቦት ሥራን ለማከናወን የሚያስችል ሥርዓት መፍጠር፣ በኅብረብሔራዊ ወንድማማችነት ማዕቀፍ ሕዝቡን ማሰባሰብ እንዲሁም መግባባት እንዲፈጠር ማድረግ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ በዚህ አመት በየደረጃው ያሉ የኮሙኒኬሽንና የሚዲያ አካላት በተደራጀና በተሟላ መልኩ ወደ ሥራ መግባታቸውን ገልጸዋል።

የሀገርና የመንግሥት ገጽታን መገንባት እና የመረጃ ተደራሽነትን ማሳደግና ሁለንተናዊ የኅብረተሰብ ተሳትፎን ማሳደግም የተልዕኮው አንዱ አካል መሆኑን ጠቅሰዋል።

በእነዚህ ሂደቶች ባለፉት ስድስት ወራት መንግሥት ትኩረት ባደረገባቸው በተለይም በአምስቱ የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ማለትም፣ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በማዕድን፣ በቱሪዝምና በአይሲቲ መስኮች ላይ ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ፣ የሕግ የበላይነትን ለማስጠበቅና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ሚዲያና ኮሙኒኬሽን አዎንታዊ ሚና እንደነበረው ተናግረዋል።

የመልካም አስተዳደር በተለይም የአገልግሎት አሰጣጥ ዜጐች ከኑሮ ውድነት አኳያ የሚያነሷቸው ጉዳዮች፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲሁም በዲፕሎማሲ መስኮች ላይ በማተኮር ሰፊ ርብርብ መደረጉን ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ በጐ ጐኖቹ እንደተጠበቁ ሆነው ሥራዎች ላይ ተግዳሮት የሚፈጥሩ ሁኔታዎችም ነበሩ።

ወቅቱ የበይነ መረብ ዘመን በመሆኑ መረጃዎች ሆን ተብለው በተዛባ መልኩ ተቀነባብረው ኅብረተሰቡን ለሁከትና ለብጥብጥ እንዲዳረግ የሚያደርጉ ዘመቻዎች መከሰታቸውን ሚኒስትሩ አንስተዋል። የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችና በውስጥ ባሉ ባንዳዎች አማካኝነት ኅብረተሰቡን እረፍት የሚነሱ ተግባራት በተፈጸሙበትና በርካታ ጥቃቶች ሀገሪቷ ላይ በሚቃጡበት ወቅቶች ውስጥ ነው ውጤቶች የተመዘገቡት ብለዋል።

በሀገሪቷ ተፈጥረው ከነበሩና አሁንም ካሉ የፖለቲካ ስብራቶች በተለይም የፖለቲካ ገበያ ጋር ተዳምረው የኮሙኒኬሽንና የሚዲያ ዘርፉ ሥራዎቹን ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዳያደርጉ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች አሁንም መቀጠላቸውን ተናግረዋል። የተጀመሩትን ውጤታማ ሥራዎች በማጐልበት ማስቀጠል እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

መላ ሕዝቡን ገዢ ትርክት በሆነው ኅብረብሔራዊ ወንድማማችነት የማሰባሰብና የሀገሪቱን ገጽታ በመገንባት ጠንካራ የኮሙኒኬሽንና ሚዲያ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

በቀጣይ መንግሥት ትኩረት ባደረገባቸው መስኮችና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ርብርብ እንደሚደረግም ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

ጉባኤው መንግሥት ትኩረት ባደረገባቸው መስኮች ላይ የተናበበ የኮሙኒኬሽን ሥራ ለማከናወን የሚያስችል ነው ብለዋል።

«ውጤታማ ተግባቦት ለኢትዮጵያ ልዕልና» በሚል መሪ ሃሳብ ለሚዲያና ኮሙኒኬሽን ተቋማት የተዘጋጀው ጉባኤ ዛሬም ቀጥሎ የሚካሄድ ሲሆን፣ በትናንትናው ዕለት ውሎ ሀገራዊ የኮሙኒኬሽን ሥራ ያለበት ደረጃ፣ እንዲሁም የክልል የኮሙኒኬሽን ያከናወኗቸው ሥራዎች ዙሪያ የሱፐርቪዥን ሥራዎችና የፌዴራል ተቋማት የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎች ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ተደርጐባቸዋል።

በጉባኤው የፌዴራልና የክልል የኮሙኒኬሽን የቢሮ ኃላፊዎች እንዲሁም የሚዲያ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።

# የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ውሳኔውን ያጸደቀው በሁለት ተቃውሞ፣ በሦስት ድምጸ ተአቅቦና በአብላጫ ድምጽ ነው፡፡

የመንግሥት ምክትል ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ ምህረቱ ሻንቆ (ረ/ፕሮፌሰር) በአማራ ክልላዊ መንግሥት የተፈጠረውን የፀጥታ መደፍረስ ተከትሎ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በመውጣቱ በአማራ ክልል የነበረውን የፀጥታ ስጋት መቀልበስ መቻሉን አስታውሰዋል፡፡

አዋጁ ተግባራዊ መደረጉ ክልሉን ከመፍረስ አደጋ መታደጉን፣ ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ማስከበር መቻሉንም አንስተዋል፡፡ ሆኖም ቀሪ ሥራዎችንም ለማጠናቀቅ የክልሉንም ሰላምና ደህንነት ለማስቀጠል አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እንዲራዘም የውሳኔ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

የአዋጁ መራዘምን ምክንያት ያብራሩት የፍትህ ሚኒስትሩ ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ አዋጁ በሥራ ላይ በቆየባቸው ጊዜያት በአማራ ክልል ተደቅኖ የነበረውን አደጋ ለመቀልበስ ማስቻሉን፣ ተቋርጠው የነበሩ በረራዎችና እንቅስቃሴዎችን ማስቀጠል መቻሉን አስታውሰዋል፡፡

የሰላም ጥሪ ለተቀበሉና የወንጀል ተሳትፏቸው አነስተኛና መካከለኛ ለነበሩ ዜጎች የተሃድሶ ሥልጠና በመስጠት ወደ ኅብረተሰቡ ተቀላቅለው ሰላማዊ ኑሯቸውን እንዲቀጥሉ ማስቻሉንም ጠቅሰዋል፡፡

የክልሉን ፖለቲካዊ አስተዳደራዊ መዋቅር መልሶ ማዋቀር መቻሉንና የፀጥታ መዋቅሩን ደግሞ መልሶ የማደራጀት ሥራ መጀመሩን ተናግረዋል፡፡ በክልሉ ያለውን ሁኔታ ጉልህ በሆነ መንገድ ማሻሻል መቻሉንም ገልፀዋል፡፡

ሆኖም አሁንም የፀጥታ ስጋቶች በመኖራቸው ቀሪ ሥራዎችንም ለማጠናቀቅ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጠቅላይ ዕዙ ቢራዘም ለሕዝብ ሰላምና ደህንነት አስፈላጊ መሆኑን እንደሚያምን ተናግረዋል፡፡ አዋጁ በሥራ ላይ በቆየባቸው ጊዜያት በኢትዮጵያ በተለይም በአማራ ክልል ብዙ ጥፋቶችን ማስቀረቱ ተጠቅሷል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ ሰብሳቢ አቶ አዝመራው አንዴም በበኩላቸው፤ ላለፉት ስድስት ወራት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በቁጥጥር ስር የሚገኙ ተጠርጣሪዎች ወደ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ እንዲደረግ ምክር ቤቱን አሳስበዋል፡፡

በዋና ዋና ማቆያ ቦታዎች ባደረጋቸው ጉብኝቶችና ውይይቶች ተጠርጣሪዎችን አስመልክቶ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት አለመፈጸሙን ማረጋገጥ መቻሉንም አንስተዋል። በሁሉም ወረዳዎችና አካባቢዎች ወርዶ ለመመልከት የፀጥታ ሁኔታው እንደገደበም ገልፀዋል፡፡ ቦርዱ ባለው ወቅታዊ ሁኔታ የማራዘም ጥያቄውን እንደማይቃወምም ገልጸዋል፡፡

አዋጁ እንዲቀጥል ማድረግ ጥፋትን በማስቀረት ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን፣ የሀገርን አንድነት በእኩይ ዓላማ ለመናድ በተደራጀ መንገድ የሚደረገውን እንቅስቃሴ እና የተደራጀ የፕሮፖጋንዳ አጀንዳን ለመቀልበስ ስለሚጠቅም አስፈላጊ መሆኑን የምክር ቤት አባላት አመልክተዋል፡፡

ከነባራዊ ችግር አንጻር እንዲሁም ሰላም እንዲጸና አዋጁ መቀጠሉ አስፈላጊ እንደሆነም በመጥቀስ፤ ከነባራዊ ሁኔታ አኳያም ማስቀጠሉ ተገቢ መሆኑን በማመን አብዛኞቹ የምክር ቤት አባላት አዋጁ እንዲራዘም ደግፈዋል፡፡

በተቃራኒውም በተቃውሞ የተከራከሩ የምክር ቤት አባላቱ አዋጁ እንዲራዘም የተነሳው ሃሳብ የተሻለ የሰላም ሁኔታ ለማምጣት የሚደረገውን ሂደት ስኬታማ እንዳይሆን ያደርገዋል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ድርድርና ንግግር እንጂ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ማስቀጠሉ አይጠቅምም፣ ኢኮኖሚውንም እየጎዳው ይገኛል፣ በአብዛኛው ሰው ላይ የመታፈን ስሜት እንዲሰማው የሚያደርግና ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብትን የሚጥስ በመሆኑ ሊቀጥል አይገባም በማለትም ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረው ነበር፡፡

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ 1299/2015 እንዲወጣ የወሰነው ሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ እንደነበር ይታወሳል፡፡

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት

የውስጥ ገፆች




ከጎዳና የፋሽን ትርዒት እስከ ዲዛይን ትምህርት ቤት

ገጽ 9



መልካም ዓይኖች - ትናንትን ሳስፉ፣ ነገን ለሚያሻግሩ እጆች

ገጽ 17

## « ዳያስፖራው

ለገበታ ለሀገርና ለትውልድ ከ30ሚሊዮን ዶላር በላይ ድጋፍ አድርጓል »

- ዶክተር መሐመድ እድሪስ
- የዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር

ገጽ 6



ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

አፍሪቃዊቷ መልኅቅ

## ለከተማዋ ኢኮኖሚ መነቃቃት የፈጠረው፤ የቱሪዝም ዘርፉ ልማት

**ዳንኤል ዘነበ**

አዲስ አበባ በኢትዮጵያ በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ከፍተኛ ገቢ ከሚያስገኙት መካከል በቀዳሚነት ትጠቀሳለች። የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ እና የልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት መገኛ የሆነችው የአዲስ አበባ ከተማ የጎብኚዎችን ቀልብ ትስባለች። በተለየ በቅርቡ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት ተገንብተው በተጀመሩ ገበታ ለሸገር፣ የእንጦጦ ፓርክ እና መሰል የቱሪዝም መዳረሻዎች ተመራጭ እየሆኑ ነው። በከተማዋ የኢትዮጵያን ምድረ ቀደምትነት የሚያስመሰክሩ ቅሪተ አካላት የሚገኙበት ብሔራዊ ሙዚየምን ጨምሮ 18 የሚደርሱ ሙዚየሞች የአዲስ አበባ ድምቀቶችና የጎብኚዎች ምርጫ እንደሆኑ ይታወቃል። በተለይ የሆቴልና ሆስፒታሊቲ (ኮንፍረንስ) ቱሪዝምን ጨምሮ ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን ታስተናግዳለች።

የኢትዮጵያ አየር መንገድን የያዘችው አዲስ አበባ ከውጭ ልዩ ልዩ የሀገሪቱን ክፍሎች ለመጎብኘት የሚመጡ ቱሪስቶች በቅድሚያ አርፈውና ዙሪያ ገባዋን ተመልክተው የሚሄዱባት ነች። ከዚህ የተነሳ በቱሪዝም ከሚገኝ ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ ትወስዳለች። ባለፉት ስድስት ወራት ከመዲናዋ የቱሪዝም ዘርፍ ከ55 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚው ፈሰስ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታውቋል።

በቢሮው የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ማስፋፋት ዳይሬክተር አቶ ሳምሶን ዓይናቸው እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ ከተማ የቱሪዝም ዘርፍ በገቢና ሥራ ፈጠራ ከፍተኛ ድርሻ



እንዳለው በማመን ትኩረት ሰጥቶት ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችንና ታላላቅ ፕሮጀክቶች ማለትም ፓርኮች፣ አደባባዮች፣ ሙዚየሞችና ተጨማሪ ማራኪ የመስህብ ቦታዎች እንዲለሙ ተደርጓል። በጥቂት ሙዚየሞች ላይ ተንጠልጥሎ የነበረው የከተማዋ የቱሪዝም መዳረሻ ወደ ባለብዙ አማራጭነት ያሸጋገረ መሆኑን አመልክተዋል።

«እነዚህ ፕሮጀክቶች የቱሪስቱን ቆይታ ሊያራዝሙ የሚችሉ በመሆናቸው ለሀገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛል። በባለፉት ስድስት ወራት ብቻ በቱሪዝሙ ዘርፍ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ቱሪስቶች በተለያዩ መንገዶች ከ55 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ ሆኗል» ብለዋል።

አቶ ሳምሶን፣ በስድስት ወራቱ አፈጻጸም ከዕቅድ አንጻር ከፍተኛ ሥራ መከናወኑን ጠቅሰው፤ ሦስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን የሀገር ውስጥ ቱሪስት ለመሳብ ታቅዶ ከአራት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ወደ ከተማዋ መጥተዋል። ከዕቅዱ አንጻር 58 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱን ገልጸዋል። ከሀገር ውስጥ ቱሪስቶች 25 ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ ሆኗል። በተጨማሪ 465 ሺህ 366 የውጭ ሀገራት ቱሪስቶች ወደ ከተማዋ መምጣታቸውን ተናግረዋል። ከውጭ ሀገራት ቱሪስቶች 29 ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ መሆኑንም አመላክተዋል።

ከቱሪዝም ዘርፉ በአብዛኛው ለመንግሥት በቀጥታ ከሚገባ ገንዘብ ይልቅ፣ ለተለያዩ አገልግሎቶች ፈሰስ የሚደረገው ገንዘብ እንደሚልቅ አያይዘው ያነሱት ዳይሬክተሩ፣ ከቱሪስቶች ለሙዚየም ጉብኝት ክፍያ፣ ለፓርኮች ጉብኝት፣ ለሆቴል አገልግሎት፣ ለምግብ፣ ለትራንስፖርት፣ ለስጦታና ማስታወሻ ዕቃዎች ግዢና ለተለያዩ በሚገኝ ገንዘብ ኢኮኖሚውን ማጠናከር የሚቻልበት ፈሰስ ተገኝቷል። ወደ ከተማዋ የመጡ የሀገር ውስጥና ውጭ እንግዶች ለተለያዩ የቱሪዝም ዓላማዎች የመጡ ናቸው። በዋናነትም በተለያዩ ሁነቶች ለመሳተፍ፣ ለኢሬቻና ለሃይማኖታዊ በዓላት፣ ለጉብኝት፣ ለዘመድ ጥየቃ፣ ለሕክምና አገልግሎት፣ ለስፖርታዊ ውድድሮችና ለተለያዩ ጉዳዮች የመጡ ናቸው የሚሉት አቶ ሳምሶን ፣ ይህም የቱሪዝም ዘርፉ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ገቢ ማደግና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ከፍተኛ ሚና እንዳለውም አብራርተዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት ስድስት ወራት በቱሪዝም ዘርፉ ከሰባት ሺህ በላይ ወጣቶችና ሴቶች በቋሚና ጊዜዊነት የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ሆነዋል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ይህም በከተማዋ የቱሪዝም ዘርፍ በገቢና ሥራ ፈጠራ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው በማመን በቱሪዝም ልማት የተሠራው ሥራ ድምር ውጤት እንደሆነም አስታውቀዋል።

በመጨረሻም፣ የቱሪዝም ዘርፉ ከማኅበራዊ ፋይዳው ይልቅ ወደ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሽግግር ያደገበት ሁኔታ መፈጠሩን የተናገሩት ዳይሬክተሩ፣ የቱሪዝም ዘርፉን በአግባቡ መጠቀምና በመንከባከብ የተሻለ ዕድገት ማስመዝገብ አስፈላጊ በመሆኑም በቀሪ ስድስት ወራት ውስጥ እንደ ከተማ ያሉ የቱሪዝም መስሕብና መዳረሻዎችን ለጎብኚዎች ምቹ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራና በተለይም ቱሪዝምን ማዕከል ያደረጉ የሥራ ዕድል ፈጠራዎች እንደሚከናወኑ አመላክተዋል። በተጨማሪም የከተማዋን የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስት ቁጥር ለማሳደግ የተለያዩ ሁነቶች እንደሚዘጋጁም ተናግረዋል። በከተማው ውስጥ ያሉ የቱሪስት መስሕብ ቦታዎችን በዓለም አቀፍ መድረኮች የማስተዋወቅና ተደራሽነታቸውን የማድረግ ሥራ እንደሚሠራም አቶ ሳምሶን አስታውቀዋል ::

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# ወቅታዊ

# ‹‹ዳያስፖራው ለገበታ ለሀገርና ለትውልድ ከ30ሚሊዮን ዶላር በላይ ድጋፍ አድርጓል››

*-ዶክተር መሐመድ እድሪስ*

*-የዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር*

**ስምስም መንግሥቱ**

በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካን፣ በአውሮፓ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በአፍሪካ እና ኢትዮጵያ ኤምባሲ ባልከፈተችባቸው ጭምር በተለያየ የዓለም ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከፍተኛ ነው። በጥናት የተደገፈ መረጃ ማቅረብ ባይቻልም፤ በቁጥር ደረጃ እጅግ ከፍተኛ የሚባል እንደሆነ ይነገራል፡፡

ኢትዮጵያውያኑ ከሀገራቸው ወጥተው በስደት በሌላ ሀገር ለመኖር ሲመርጡ የተለያዩ ምክንያቶች አሏቸው፡፡ አንዳንዱ ሀገር ውስጥ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ አልመች ብሏቸው፣ ሌሎች ደግሞ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ፣ የተቀሩት ደግሞ ተምሮ እራስን ለማሻሻል በሚል አላማ ከሀገር ይወጣሉ፡፡

ኢትዮጵያውያኑ የሄዱበትን ዓላማ ለማሳካት ሌትከቀን በሥራ፣ በትምህርት፣ ኑሮን ለማሸነፍ ይደክማሉ፡፡ ኢትዮጵያውያኑ ለስኬት ለመብቃት ሌተቀን ሲደክሙ ግን ሀገራቸውን በልባቸው ይዘው ነው፡፡

በሀገራዊ ወቅታዊ የፖለቲካ አለመመቸት ምክንያት አኩርፈው ከሀገራቸው የወጡ ቢሆኑም ለመኖር ብለውም በትውልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነት የውጭ ሀገር ለመሆን ቢገደዱ እንኳን አካላቸው እንጂ በሀሳብ ውሎና አዳራቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፡፡ ይህንንም እውነታ ባገኙት አጋጣሚ በተለያየ መንገድ ሀሳባቸውን ሲገልጹ ይደመጣሉ፡፡ ስኬታቸውም ለግላቸው ብቻ እንዳልሆነ በተለያየ መንገድ በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ይገለጻል፡፡

በተለያየ ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ያላቸው ድጋፍ ቤተሰብን ከመርዳት ይጀምራል፡፡ ለቤተሰባቸው የሚልኩት የውጭ ምንዛሪ ደግሞ በተዘዋዋሪ በሀገር ምጣኔ እድገት ላይ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ ከዚህ አልፎ ደግሞ በሚኖሩበት ሀገር ያገኙትን ትምህርት፣ የሥራ ክህሎት፣ ቴክኖሎጂ በትውልድ ሀገራቸው ውስጥ በመተግበር፣ ልምድና ተሞክሮአቸውንም በማካፈል የማይናቅ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

ከፍ ሲልም በተለያየ ኢንቨስትመንት በመሰማራት መዋዕለነዋያቸውን በሀገራቸው ያፈሳሉ፡፡ ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ ከሀገራቸው ርቀው ቢገኙም በዚህ መልኩ ሀገራቸውን እያገዙ ይገኛሉ፡፡

በተወሰነ ጊዜም ሀገራቸው በመምጣት የሀገራቸውን ወቅታዊ ሁኔታ በማየት የሀገር ገጽታ ግንባታ ላይ ሚናቸውን የሚወጡ እንዳሉም ይታወቃል፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ ከሀገራቸው ከወጡ ጀምሮም ያልመጡም ይኖራሉ፡፡

በተለያየ ምክንያት ወደ ሀገር ያልመጡና በውጭ ተወልደው ስለሀገራቸው የማያውቁትን መንግሥት ጥሪ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም ውጭ ሀገራት ተወልደው ኢትዮጵያን በአካል የማያውቋት የሁለተኛው ትውልድ አባላት ጠንካራ ተሳትፎ እንዲያደርጉ መንግሥት በማበረታታት ላይ ነው፡፡

እኛም የዳያስፖራው ማህበረሰብ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካ እያደረገ ስላለው ተሳትፎ እንዲሁም በዲፕሎማሲው ስላለው አበርክቶ ከዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መሐመድ እድሪስ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡ መልካም የንባብ ጊዜ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ ዳያስፖራው በኢንቨስትመንት፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያለው ሀገራዊ ተሳትፎ ምን ይመስላል ከሚለው ብንጀምርስ ?**

**ዶክተር መሐመድ፤** የዳያስፖራውን ሀገራዊ ተሳትፎ በሶስት መንገድ ወይንም ማዕቀፍ መግለጽ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ከዳያስፖራው ስብጥር ወይንም አይነት የሚመነጭ ተሳትፎ ነው፡፡ አንዱ የኢኮኖሚ ዳያስፖራ ብለን የምንወስደው ነው። ዳያስፖራዎች በሚኖሩበት ሀገር ያፈሩትን ሀብት ወይንም ጥሪት ሀገራቸው ውስጥ በማዋል ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው እንዲጠቅም እንዲሁም ለዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር በአጠቃላይ ለሀገር እድገት እንዲውል የማድረግ ፍላጎት ያላቸው ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ያሉት ደግሞ የእውቀት ዳያስፖራ ናቸው፡፡ እነዚህ ዳያስፖራዎች ትምህርታቸውን በሀገር ቤት ተከታትለው ከጊዜ በኋላ ወደ ውጭ ሀገር የሄዱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ወይንም ደግሞ በስደት በሚኖሩበት ሀገር ውስጥ ተምረው እውቃታቸውን አሻሽለው የተሻለ ክህሎት ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህኛው ዘርፍ እውቀትና ክህሎት ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሰራው ሥራ ይጠቀሳል፡፡

ስብጥሩ በነዚህና በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት፣ በፖለቲካው ዘርፍ፣ በሁለተኛ ትውልድ፣ በሚሉ የሚገለጽ ሲሆን፤ የነዚህ ሁሉ ስብጥር የሚስተዋልበት የዳያስፖራ ተሳትፎ ነው በሀገር ውስጥ ያለው። ለአብነትም ዳያስፖራው በኢንቨስትመንት ዘርፍ በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ የሚገለጽ ተሳትፎ አድርጓል፡፡ በተመሳሳይ በተለያየ የኢንቨስትመት ዘርፍ ለመሰማራት ፍላጎት ያለው ደግሞ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

በአነስተኛ ኢንቨስትመት ላይ የተሰማሩትን ትተን ዋና ዋና ወይንም ከፍተኛ በሚባለው፤ ባለፉት ሶስት ዓመታት ብቻ ከአምስት መቶ በላይ የዳያስፖራ ባለሀብቶች በተለያየ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ በመሰማርት ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡ እነዚህ ባለሀብቶች ለዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥረው፣ ምርትም አምርተው ወደ ገበያ በመግባት ውጤታማ በሚባል ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ በ2015ዓ.ም ብቻ ከ264 በላይ የሚሆኑ ዳያስፖራ ባለሀብቶች በሀገራቸው ኢንቨስት ለማድረግ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡

በእውቀትና በቴክኖሎጂ ሽግግርም በተመሳሳይ ጥሩ የሚባል እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ባለፉት ሶስት አመታት ብቻ ከሰባት መቶ በላይ የሚሆኑ የዳያስፖራ የእውቀት፣ የክህሎትና የቴክሎጂ ሽግግር ፕሮግራሞች ተከናውነዋል፡፡ ፕሮግራሞቹ የጤና፣ የስልጠና፣ የትምህርት፣ ኮምፒውተር ሳይንስ፣ ውሃና መሰል ፕሮግራሞች ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ፤ አንዱ ፕሮግራም ብቻም እስከ አንድ መቶ ዳያስፖራዎችን ሊያሳትፍ ይችላል፡፡ ተሳትፎው እንደየይዘቱ አነስተኛ ቁጥር ወይንም በዛ ያለ ተሳታፊ ሊኖረው ይችላል። በዚህ መልኩ ነው የዳያስፖራውን ስብጥር ታሳቢ ያደረገ ሥራዎች በመከናወን ላይ የሚገኙት፡፡

ሌላው ከስብጠሩ ማእቀፍ የሚመነጨውና የትኩረት አቅጣጫ የሆነው፤ ሁለተኛው ትውልድ ዳያስፖራ ላይ የሚሰራው ሥራ ነው፡፡ ሁለተኛው ትውልድ ዳያስፖራዎች ሀገራቸውን እንዲያውቁ ለማስቻል የሚደረግ ጥረት ሲሆን፤ በዚህ ረገድ ደግሞ የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር በማድረግ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ለማነቃቃት ያስችላል፡፡ እንዲሁም የሀገር ገጽታን ለመገንባት የሚሰራ ሥራ ነው፡፡ በተለያየ የዓለም ሀገራት የሚኖሩ ሁለተኛው ትውልድ ዳያስፖራዎች በቤተሰብ፣ ጓደኞች በቡድን ሆነው ወደ ሀገር ቤት እንዲመጡ ነው የሚበረታቱት፡፡

ዳያስፖራውን የተመለከቱ ጉዳዮች በአምስት ዓመትና በአስር ዓመት መሪ እቅዶች የሚመራ ነው። እነዚህን እቅዶች መሠረት በማድረግ ዳያስፖራውን በቋሚነት የምናሳትፍበት ዘርፎች አሉ፡፡ ሆኖም ግን ሀገር ከዳያስፖራው ምን ትፈልጋለች? ዳያስፖራውስ ከሀገር ምን ይፈልጋል ? የሚሉ ሃሳቦች ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል፡፡

በተለይም ሀገር ከዳያስፖራው ምን ይፈልጋል ለሚለው፤ በዚያኛው ወገን ወይንም በዳያስፖራው



በኩል ያለውን አቅርቦት ታሳቢ ያላደረገ፣ ሀገር ቤት ውስጥ ያለውን ፍላጎት ብቻ መሠረት ያደረገ እቅድ አቅዶ መነሳት ፈተና ውስጥ ይከተናል፡፡ ስለዚህ ዳያስፖራው ምን ይፈልጋል ስንል፣ ዳያስፖራው ምን አይነት አቅም አለው፣ ከአገልግሎት አንጻርስ ምን ይፈልጋል፣ የሚለው መለየት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ ዳያስፖራው ከሚፈልገው ማዕቀፍ በመነሳት ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡

ዳያስፖራው፣ የቤት ልማት ፕሮጀክት ሊፈልግ ይችላል፡፡ የቤት ልማት ፕሮጀክት መሠረተ ሀሳቡ ለዳያስፖራው ቤት መስጠት አይደለም፡፡ ዳያስፖራው የውጭ ምንዛሪውን በሀገር ቤት በማስቀመጥ ሀገር ውስጥ ላሉ የግልም ሆነ የመንግሥት ተቋራጮች ሥራ መፍጠር ነው፡፡ እንዲህ ያለው እንቅስቃሴ ለሀገር የውጭ ምንዛሪ ያስገኛል፡፡ በዚህ መልኩ ለንግድ፣ ለኢንቨስትመንት፣ ለቱሪዝም የሚመጡ ዳያስፖራዎችን ፍላጎት በመጨመርና እድሉን በማስፋት ተጠቃሚ መሆን ይቻላል።

ዳያስፖራው በውጭ ያካበተውን ልምድ፣ ያገኘውን ሙያና ትምህርት መሠረት በማድረግ በሙያው ሀገሩን ማገልገል ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በትምህርት፣በጤና፣በአጠቃላይ በመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ የእውቀት ክህሎት ሽግግር ምን አይነት ምቹ ሁኔታ ያስፈልጋል በሚለው ላይ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡

ሌላው ወቅታዊ ሁኔታ የሚያመጣው ወይንም የሚፈጥረው የዳያስፖራው ተሳትፎ ነው፡፡ ወቅታዊ ሁኔታዎቹ አንዳንዶቹ ፕሮጀክቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ለአብነትም እንደ ታላቁ ኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ፣ ገበታ ለሀገር፣ ገበታ ለትውልድ ያሉ በመንግሥት እየተከናወኑ ያሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ይጠቀሳሉ። ለታላቁ የህዳሴ ግድብ የዳያስፖራው ተሳትፎ ከ70 ሚሊዮን ዶላር በላይ ይሆናል፡፡ ገበታ ለሀገር የመጀመሪያው ፕሮጀክት ላይም ወደ 29 ሚሊዮን ዶላር የሚሆን ተሳትፎ ተደርጓል። ለገበታ ለትውልድ ደግሞ ወደ አንድ ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ ነው ተሳትፎው፡፡ በተለይ ደግሞ አስቸጋሪ ናቸው በሚባሉ ወቅቶች ለምሳሌ፤ ኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ ተከስቶ በነበረበት ወቅት፣ በጦርነት ፣ በተለያየ ምክንያት ሰዎች ከቄያቸው ተፈናቅለው ለችግር ሲዳረጉ፣ ዳያስፖራው በተቻለው አቅም በመረባረብ በገንዘብና በተለያየ መንገድ ይሳተፋል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ ባስፈለገበት ወቅትም እንዲሁ ድጋፍ ከማድረግ አልተቆጠበም፡፡ በ2015ዓም ከዳያስፖራው ማህበረሰብ ወደ ስድስት ሚሊዮን ዶላር በማሰባሰብ ለተቸገሩ ኢትዮጵያውያን እንዲውል ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በአይነት ከ10 ሚሊዮን ዶላር በላይ ዋጋ ሊያወጡ የሚችሉ ድጋፎች ተደርገዋል። በገንዘብም በአይነትም የተደረገው ድጋፍ ከፍተኛ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከዳያስፖራው ስብጥር የሚመነጩ ተሳትፎዎችን ስንመለከት የዳያስፖራው ማበህረሰብ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካ ያደረገው ተሳታትፎዎችን በመጠን ለመለካት የራሱ የሆነ ሥራ የሚያስፈልገው ቢሆንም፤ ድርሻው ከፍተኛ ወይንም ሰፊ እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡

**አዲስዘመን፡- በዲፕሎማሲው ዘርፍ ያላቸው አበርክቶ እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር መሐመድ፡-** የውጭ ግንኙነት ሥራ ተቀዳሚ ዓላማ ተደርጎ የሚቀመጠው፤ የአንድን ሀገር ብሄራዊ ጥቅም ማስጠበቅ ነው፡፡ ብሄራዊ ጥቅም ደግሞ አንድ ትልቅ አጀንዳ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም ብሄራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ በአንድ ተቋም ሥራ ብቻ ይሳካል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ምንም እንኳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጭ ሀገራት ኢትዮጵያን የመወከል ሥራ ቢሰጠውም የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ የበርካታ ተቋማትና የሁሉም ዜጎች ርብርብ ይጠይቃል፡፡ ከዚህ አንጻር የዳያስፖራው ማህበረሰብ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንደ አንድ ባለድርሻ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የማስጠበቅ ድርሻ አለው፡፡

ወደ ዝርዝር ጉዳይ ስንመጣ ግን ፤እራሱ የውጭ ጉዳይ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ሥራ እንዲያሳካቸው

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

# ‹‹ዳያስፖራው ለገበታ ለሀገርና ለትውልድ...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

የሚፈልጋቸውን ሥራዎች ብንመለከት አንደኛው የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሥራ ነው:: የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሥራ በአንድ በኩል በውጭ ሀገር ያለን ሀብት ወደ ሀገር ውስጥ በማምጣት የሀገር ውስጥ መዋዕለ ነዋይ ፍሰትን መጨመር፣ የሥራ እድልን ማሳደግ እንዲሁም የእውቀትና የክህሎት ሽግግርና መጨመር ነው:: በዚህ በኩል የዳያስፖራው ማህበረሰብ ቀጥተኛ የሆነ ድርሻ አለው::

አንድም ዳያስፖራው እራሱ በውጭ ሀገር ካፈራው ሀብት፤ ሁለትም በውጭ ሀገራት ካለው የተለያየ አማራጭ የፋይናንስ እድል ሲሆን፣ ዳያስፖራው ከሚኖርበት ሀገር የገንዘብ ብድር የማግኘት እድልም አለው:: በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ በተለያዩ የውጭ ሀገር ከሚገኙ ባለሀብቶች ጋር ጥምረት በመፍጠር፣ የሚያደርገው ጥረት በሀብት ፍሰት ላይ የሚኖረው ሚና ይጠቀሳል። ስለዚህ ዲፕሎማሲን ለማሳካት ከሚያስችሉ ነገሮች አንዱና ቁልፍ ተዋናይ ተደርጎ የሚወሰደው የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ነው::

የዚህ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሌላው መገለጫ፤ በንግድ ዘርፍ ያለው ነው:: ለኢትዮጵያ ምርቶች ገበያ መፍጠር ነው:: ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ቤት መጥተው የሚፈጥሩት ቢዝነስ ወይንም ንግድ ብቻ ሳይሆን፤ በውጭ ሀገራትም በርካታ የንግድ ተቋማትና እንቅስቃሴዎች አሏቸው:: የኢትዮጵያን ንግድ ወዳሉበት ሀገር በመውሰድ እሴት ጨምረው መሥራት ይችላሉ::


ስለዚህ ዳያስፖራዎች አዳዲስ ምርቶችን ያስተዋውቃሉ:: የምርት መዳረሻም ሆነው ያገለግላሉ:: የኢትዮጵያን ምርትም ገዥ ናቸው። የተለያዩ የኢትዮጵያ ምርቶች የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) በሰንጠረዥ ብናስቀምጣቸው፤ በተለይም ዋና ዋና የሚባሉት ላይ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት ትውልደ ኢትዮጵያውያን ናቸው:: ፤ልምሳሌ በቡና የወጪ ንግድ ላይ ወደ አምስት መቶ የሚሆኑ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ይገኙበታል። ትልልቅ የሚባሉ የኢትዮጵያ የወጪ ምርቶችም በኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ስኬት ላይ ቁልፍ ሚና አላቸው ማለት ነው::

በሌላ በኩል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያሳካ የሚጠበቅበት፤ የፖለቲካ ዲፕሎማሲ ነው:: የፖለቲካ ዲፕሎማሲ በዋነኛነት ኢትዮጵያና ሌሎች አቻ ሀገራት የሚኖራቸውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ማጠናከር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ በሌሎች ባለብዙ ወገን ግንኙነቶች ላይ ተደማጭነቷ እንዲጨምር ማድረግ ነው::

በዚህ በኩልም ዳያስፖራው እራሱን የቻለ፣ በቁመቱ ልክ የተመጠነ ሚና አለው:: ቀደም ሲል እንዳነሳሁት የዲፕሎማሲ ሥራ በአንድ አካል ወይንም ተቋም ላይ ብቻ የሚወድቅ፣ የሚገኘው ስኬትም ሆነ ውድቀት እንዲሁ የአንድ አካል ብቻ መሆን እንደሌለበት ሁሉ ዳያስፖራውም በፖለቲካ ዲፕሎማሲውም በራሱ ልክ የተለካ ሚና አለው ማለት ነው::

**አዲስ ዘመን የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ከማስከበር አንጻር ዳያስፖራው እያደረገው ያለውን አስተዋጽኦ ቢያብራሩልን ?**

**ዶክተር መሓመድ** -በሁሉም የዓለም ሀገራት ባንል እንኳን በጣም ብዙ በሚባሉ ሀገራት ውስጥ ዜጎቻችን ይኖራሉ:: ይህ ማለት የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ተደራሽ ባልሆኑባቸው ሀገራት ጭምር ማለት ነው። ስለዚህ ዜጎቻችን አምባሳደሮቻችን ናቸው ማለት ነው። ስለኢትዮጵያ የማሳወቅ፣ የመናገር፣ ኢትዮጵያን የመምሰል ተልእኮ ይወጣሉ። በሳይንስና ምርምር እንዲሁም በጣም ትላልቅ በሚባሉ ዓለምአቀፍ ተቋማትና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ ብዛት ያላቸው ትውልደ ኢትዮያውያን አሉ:: ዜጎቻችን በሚኖሩባቸው ሀገራት ውስጥ በሚገኙ በነዚህ ትላልቅ ተቋማት ውስጥ መሥራታቸው በራሱ ውክልና አለው። በመኖራቸው ደግሞ ሌላ የሚገኝ የፖለቲካ ትርፍ አለ ማለት ነው::



**የኢትዮጵያን የፖለቲካ ዲፕሎማሲ ለማሳካት ዳያስፖራው በራሱ ልክ የተሰፈረ ድርሻ አለው**

ከዚያ አለፍ ብሎ ደግሞ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቁ የሚፈለጉ አጀንዳዎች ሲኖሩ፤ በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመጀመሪያው ተሰላፊ ይሆናሉ ማለት ነው:: የትኛውም የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የማስጠበቅ ጉዳይ በተለያየ መንገድ ስለሆነ የሚሰራው ዳያስፖራው የራሱን ድርሻ ይይዛል ማለት ነው::

አንድን ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ፤ ከአንድ ሀገር ጋር መደራደር ሊያስፈልግ ይችላል:: ስለዚህ ዳያስፖራው በሚኖርበት አካባቢ መራጭ፣ ወይንም ተመራጭ ነው:: ሰራተኛም ሊሆን ይችላል:: ወይንም በጋራ በሚፈጥራቸው አደረጃጀቶች የራሱን ድምጽ ለማሰማት የሚችልበት እድል አለው ማለት ነው:: ስለዚህ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ዲፕሎማሲ ለማሳካት ዳያስፖራው በራሱ ልክ የተሰፈረ ድርሻ አለው::

በሌላ በኩል የፖለቲካ ዲፕሎማሲያችንን እንዲያሳካ የሚጠበቅበት፤ የባህልና የገጽታ ግንባታ ሥራ ነው:: ይሄ ከውጭ ግንኙነት ሥራችን አንዱ እንደመሆኑ መጠን፤ ዳያስፖራው በባህል፣ በገጽታ ግንባታ፣ በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት በኩል ትልቅ የሚባል አሻራ አለው:: ሌሎች ያሉትን ተሳትፎዎች እንኳን ትተን በዚህ ዘርፍ ብቻ ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ እያበረከቱት ያለው አስተዋጽኦ በገንዘብ ቢለካ፣ በተቋም ደረጃም ቢሆን እንስራ ብንል የማይቻል ከፍተኛ የሆነ ስኬት ነው::

ዳያስፖራው የሚያንቀሳቅሳቸው የባህል ሬስቶራንቶችና መዝናኛዎች፣ ዳያስፖራው በሚኖርባቸው የውጭ ሀገራት ውስጥ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ይዘት ያላቸው የሚያከብራቸው የኢትያጵያን ባህል፣ ወግና ሥርዓት የሚያንፀባርቁ በዓላት የሀገር ገጽታ ግንባታ ማሳያዎች ናቸው:: እነዚህ ሁሉ አፍ አውጥተው የሚናገሩ በተግባር የሚታዩ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ናቸው::

እነዚህን በጀት መድቦ ለመሥራት ቢሞከር በቢሊዮን የሚቀጠር ገንዘብ ይጠይቃል። ዳያስፖራው ገንዘብ ሳይጠይቅ የሚወጣው ተግባር ነው:: መለያ ወይንም ብራንድ ማድረግ ላይ ክፍተት ሊኖር ይችል እንደሆን እንጂ በተለያየ መንገድ የሚወጡት ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ ከፍተው በሚሰሩባቸው ሬስቶራንቶችና ምግብ ቤቶች ውስጥ ከኢትዮጵያውያኑ በላይ ነጮቹ ናቸው የሚጠቀሙት። በተለይም በአሜሪካን የተለያዩ ግዛቶች የሚታየው ሀቅ ይህ ነው::

የአትክልት ምግብ (ቬጂቴሪያን) የሚባለው ሥጋ ተመጋቢ ላልሆነ ሰው ከሚያቀርቡት ምግብ ጀምሮ ተመራጭ የሆነ ስብጥር ያለው ምግብ በማቅረብም ይታወቃሉ:: በዚህ በኩል ብራንዲንግ ላይ ብንበረታ እራሱን የቻለ ለገጽታ ግንባታ መዋል ይችላል::

ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ስንሄድ ቋንቋቸውን የሚናገሩ፣ የኢትዮጵያን ባህል ደግሞ የሚያውቁ፣ በተለያየ ምክንያት የተረሱ ባህሎቻችንን፣ታሪኮቻችንን፣ በራሳቸው ቋንቋ የሚናገሩ፣ የሚያስተጋቡ፣ የህዝብ ለህዝብ ትስስራችንን የሚያጠናክሩ፣ ሥራዎችን የሚሰሩ ዲያስፖራዎች በርካታ ናቸው::

በውጭ ዲፕሎማሲ እንደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ልናሳካው የሚገባው የምንፈልጋቸውን ዘርፎች ዳያስፖራው በቁመቱ ልክ ይወስዳል:: ትልቅ የሆነ ሚናም ይጫወታል:: የእከሌ ሥራ ነው ወይንም የአንድ አካል ተልእኮና ተግባር ነው ተብሎ የሚነሳ ጉዳይ አይደለም::

**አዲስ ዘመን፦ በቆይታችን ያላነሳናቸው ያልተገለጹ ነገሮች ካሉ ቢጨምሩ**

**ዶክተር መሐመድ፦** አንዳንዴ እኛ በምናስበው ልክ ዳያስፖራውን የመሳል ሁኔታ አለ። በአንዳንድ ወቅት የዳያስፖራ ተሳትፎ ገንዘብ ላይ እንዲያተኩር ሊፈለግ ይችላል:: በዚህ ጊዜ ዘመቻው፣ እንቅስቃሴው፣ አጀንዳው በአብዛኛው ወደዚያ ያተኩሩና የማህረሰቡም የዳያስፖራውም ተሳትፎ እዛ ላይ ሊታሰር ይችላል። በሀገር ቤትም በውጭ ሀገር የሚኖሩ አንዳንዶች ጉዳዩን ያልተረዱ ጉዳዩን ላልተገባ የፖለቲካ ፍጆታ ሲጠቀሙበት ይስተዋላል። ይሄ ስህተት ነው::

በሌላ ጊዜ ደግሞ የገጽታ ግንባታ ሥራ ወይ በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ወይንም በፖለቲካ ዲፕሎማሲ በዲጂታል ንቅናቄዎች አካባቢ በጣም አንገብጋቢ ይሆንና፣ እዚህ ላይ ሰፊ የዘመቻ ሥራ እንሰራለን። ሙሉ ባለድርሻ አካላትን እዛ ላይ እናሳትፋለን። ዳያስፖራዎቻችን፣ ኤምባሲዎቻችን ሙሉ ትኩረታቸውን እዛ ላይ እንዲያደርጉ እንሰራለን። እዚህ ላይ በሚሰራው ሥራ ደግሞ የዳያስፖራው ተሳትፎ የድጋፍ ሰልፍ ከመውጣት ጋር ይተሳሰርና ድጋፍና ተቃውሞ ከዚህ ጋር ይተሳሰራል።

ይሄን ጉዳይ የማነሳው የዳያስፖራውን ተሳትፎ በሁለተናዊ መልክ ካላየነው፤ ከሁሉም ህብረተሰብ ወይንም የዳያስፖራ አቅም ከሁሉም ለማምጣት፤ ሀገርንም ዳያስፖራንም መጥቀም አለብን ብለን ካላሰብን፤ ስለዳያስፖራ ያለው አመለካከት ወይንም ተሳትፎ ወቅታዊ ይሆናል:: ይህ ደግሞ አንዱን ዘርፍ ብቻ እንይዝና እቅዳችን፣ ሀብታችን፣ የሰው ኃይላችን፣ የተግባቦት ሥራችንም በዛው ላይ ይታጠራል:: የዳያስፖራ ዲፕሎማሲ ሲባል ጠቅለል ተደርጎ በስፋት መታየት አለበት::

ለምሳሌ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ትልቅ ተነሳሽነት(ኢኒሼቲቭ) ነው:: ነገር ግን ወደ አተገባበር ሲመጣ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ፤ አጀንዳ ላይ በአብዛኛው ሰፍኖ የሚታየው፤ የተጎዱ ዜጎችን ከውጭ ሀገር ማስመለስ ላይ ነው:: ነገር ግን ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ፣የዲፕሎማሲ ዓላማ በራሱ፤ ብሄራዊ ጥቅሞቻችንን በማስጠበቅ በሀገር ውስጥም በውጭም ሀገር የሚገኙ የዜጎቻችንን ጥቅም ማስጠበቅ ነው:: ሁለተኛው ዜጋህን እንደዲፕሎማት ተጠቅመህ የምታሳካው ዲፕሎማሲ ነው::

ሦስተኛ የዜጎችን ክብር ማስጠበቅ ነው:: አራተኛ እያልክ የምትዘረዝራቸው በርካታ አመለካከቶች አሉና በነዚህ ላይ በሰፊው መሥራት ካልተቻለ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ በአንዱ ዘርፍ ላይ ብቻ ሊያተኩር ይችላል። እቅድህ ተግባቦትህ ሪፖርትህ እዛ ላይ ብቻ ይሆናል ማለት ነው:: የዳያስፖራውም ተሳትፎ ልክ እንደዚያው ነው እና ሙሉ ቅርጹንና ይዘቱን ካሰብን ብዙ እንደ ሀገር በርካታ ጥቅሞችን ይዞልን ይመጣል።

**አዲስ ዘመን፦ ስለሰጡን ማብራሪያ በጣም እናመሰግናለን።**

**ዶክተር መሐመድ ፦** እኔም አመሰግናለሁ::


ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም
ቴሌብር
telebirr
በቴሌብር ዓለም አቀፍ ሀዋላ
ገንዘብ ይቀበሉ!
10%
ስጦታ
ያግኙ
አጋሮቻችን
Thunes.
TalkRemit
WorldRemit
AZIMO
Taptap Send
ria Money Transfer
MTN Rwanda
small world
MasterRemit
Send money with LOVE
Moneytrans
Remitly
Promises Delivered
MAJORITY
mukuru
ooredoo
GURUSH
ስለ አገልግሎታችን መረጃ ለማግኘት www.ethiotelecom.et ይጎብኙ

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ከጎዳና የፋሽን ትርዒት እስከ ዲዛይን ትምህርት ቤት

**ዳግም ከበደ**

ብዙዎች ስኬት ‹‹በራስ የተቀመጠ ግብ ላይ በጥረት መድረስ›› መሆኑን በመግለፅ ለቃሉ የተብራራ ትርጉም ያስቀምጡለታል። መሻታቸው ከልብ ሲደርስ፤ ያሰቡትን ኢላማ ሲመቱ፣ እቅድና ፍላጎታቸው መሬት መርገጡን ሲገነዘቡ፤ በትግልና በትዕግስት ያገኙትን ድል ያጣጥሙታል። ይህ ስኬታቸው ለነገ ሌላኛው ታላቅ ሕልማቸው መሰረት ከመሆኑ በላይ ለብዙሀኑ ደግሞ አርዓያና መነሳሳትን የሚፈጥር ይሆናል።

የዛሬ እንግዳችንም ለዚህ ተምሳሌት ነች። ከልጅነት ህልሟ ጋር የተገናኘች፤ አሁን ላለችበት ደረጃ ሙሉ አቅሟንና እውቀቷን የሰጠች የፋሽን ዲዛይነር ነች። ሙያው ከልጅነት ጀምሮ ልትደርስበት የምትፈልገው ሕልሟ ነበር። ዛሬ ላይ ራሷን ከማብቃት አልፋ ብዙኃን ሕልማቸው ዳር እንዲደርስ ምክንያት እየሆነች ነው።

የፋሽን ዲዛይነር ሰናይት ጥበቡ ትባላለች። የፋብሪክ ፋሽን ዲዛይን ትምህርት ቤት ባለቤት ናት። ተወልዳ ያደገችው ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ በምትገኘው የደብረብርሀን ከተማ ነው። በልጅነቷ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ላይ ያስጠራው አትሌቲክስ (ሩጫ) ወዳጅ ነበረች። ትምህርት ቤቷን በመወከል በተለያዩ ውድድሮች ላይ ተሳትፋለች። የፋሽን ዲዛይን ሙያ ቀዳሚ ምርጫዋ ባይሆን ኖሮ ዛሬ ሰናይትን በስፖርት መድረኮች ላይ ልናያት እንችል እንደነበር ፈገግ እያለች ትናገራለች።

ሰናይት ከቤተሰቦቿ ሳትርቅ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለውን ትምህርቷን በደብረብርሃን ከተማ ተከታትላች። በቀለም ትምህርት አቀባበሏ ጎበዝ ስለነበረች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ለመከታተል የግድ የትውልድ መንደሯን ትታ የካቶሊክ ሚሽን ትምህርት ቤት ወደሚገኝበት ዱራሜ ማቅናት ነበረባት። ይህ የቤተሰቡ ውሳኔ የሰናይትን የሕይወት አቅጣጫ ያስቀየረና ለዛሬ እሷነቷ መሰረት የጣለ ጭምር ሆነ።

### ዱራሜ- የአዳሪ ትምህርት

ለቤተሰቡ አራተኛ ልጅ የሆነችው ዲዛይነር ሰናይት የዱራሜ የካቶሊክ ሚሽን ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በምትከታተልበት ወቅት ቀደም ሲል ከነበራት ስፖርታዊ ፍቅር ባሻገር ተሰጥዖ እንድታገኝ የሚያስችላት አንድ አጋጣሚ ተፈጠረ። በጊዜው የአዳሪ ትምህርት ቤቱ በግቢው የጥልፍና ስፌት ትምህርት ቤት ነበረው። በመምህራኑ በኩል ተማሪዎች በቀለም ትምህርት ላይ እንዲያተኩሩ ግፊት ቢኖርም ለሙያው ፍላጎት የነበራቸውን ተማሪዎች ያለምንም ጫና እውቀቱን እንዲያገኙ እድሉ ይፈጥርላቸው ነበር። ሰናይት ወደ ዱራሜ ከመምጣቷ በፊት በአንድ የካቶሊክ ሲስተሮች ቤት አዳነች ወልደሰንበት በምትባል ሲስተር አማካኝነት የሹራብ መስሪያ ማሽን የማየት አጋጣሚውን አገኘች፡፡ ወደ ስልጠናው ለመግባትም ልዩ ፍላጎት አደረባት።

በዚህ አጋጣሚ ነው በዱራሜ አዳሪ ትምህርት ቤት ሰናይት ሲስተር ማርያ ሮዛ ከምትባል ጣሊያናዊት ልዩ ድጋፍና ክትትል አግኝታ የጥልፍ፣ ዲዛይንና፣ ስፌት ሙያን ክረምት ላይ መማር የጀመረችው። በዚያን ጊዜ የሙያው ፍቅር እና የወደፊት ህልሟም አብሮ ተወለደ።

ከሕንድ፣ ከጣሊያንና ከተለያዩ አገራት የመጡ መምህራን በፍጥነት በምታሳየው ለውጥና በስራዋ ብቃት ይደሰቱና ያበረታቷት እንደነበር ታስታውሳለች። የትምህርት ቤቱን የፀሎት ቤት ዲኮር ስታደርግና ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ሲኖሩ ለስራው ሰናይት ተመራጭ ሆነች። የቀለም ትምህርቷን ሳይነካ የፋሽን ዲዛይኒንግ ፅንሰ ሀሳብን መማሯ ይበልጥ ወደ ዘርፉ እንድትሳብና ፍቅሩ እንዲያድርባት አደረጋት።

የፋሽን ዲዛይነሯ ሰናይት ከ10ኛ እስከ 12ኛ ክፍል በዱራሜ ካቶሊክ ሚሽን ትምህርት ቤት የቀለም ትምህርቷን ተማረች። ከዋናው ትምህርቷ ውጪም የዲዛይንና ፋሽን ሙያ ፍቅር እንዲኖራት ትምህርት ቤቱ ምክንያት ሆነላት። በዚህ ሁኔታ ላይ ነበር የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ የተፈተነችው። በወቅቱ ውጤት አምጥታ የቀድሞው ናዝሬት ቴክኒካል ኮሌጅ የአሁኑ አዳማ ዩኒቨርሲቲ ተመደበች። ይሁን እንጂ የደረሳት የትምህርት ክፍል ሰናይትን ከሕልሟ የሚያደርስ አልሆነም። ነገር ግን በኮሎጁ ቆይታ አድርጋ በኤሌክትሪካል ኤሌክትሮኒክስ ሙያ ትምህርቷን ተከታተለች።



የፋሽን ዲዛይነር ሰናይት ጥበቡ

የዛሬዋ የስኬት እንግዳችን ሰናይት የዲዛይን እና ፋሽን ፍቅር ቢያሸንፋትም ለቀለም ትምህርት እጅ የምትሰጥም አልነበረችም። የመጀመሪያ ድግሪዋን ያዘች፤ ይህን ይዛ ስራ ወደመፈለግ ግን አልገባችም። ይልቁኑ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማቅናት ከተመረጡ ከ5 የአፍሪካ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በትብብር ይሰራ ወደነበረው ‹‹Africa Virtual University›› በኮምፒውተር ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ በመማር ኢንተርናሽናል አድቫንስ ዲፕሎማ መያዝ ቻለች። በዚህም ሙያ ተቀጥሮ ከመስራት ይልቅ የኮምፒውተር መለዋወጫ ሱቅና ኢንተርኔት ቤት ከፍቶ መስራትን ምርጫዋ አደረገች።

በካቶሊክ ሚሽን ትምህርት ቤት በጥብቅ ስነ ምግባር እና የስራ ጥንካሬ ነበር ታንፃ የተማረችው። ወደ ስራው ዓለም ስትገባም ይህ ተፅዕኖ አድርጎባት በአዲስ አበባ ገርጂ አካባቢ የከፈተችው ሱቅ ለደንበኞች በሚማርክና መንፈስን በሚያድስ የዲዛይን ውጤት የተከፈተ ነበር። በአካባቢው ተመራጭና ብዙዎች የሚያዘወትሩት የኢንተርኔት እና የንባብ ክፍልም ነበረው። የንግድ ዓለሙን ስትቀላቀል ንፅህና፣ ማራኪ ገፅታ፣ አዳዲስ የፈጠራ ሀሳብ የሰናይት መርሆች ሆነው የሕይወት መንገዷን ተቀላቀሏት።

### ቤተሰብና ንግድ

‹‹በስራው ትንሽ እንደቆየሁ ቤተሰብ መስርቼ ልጆች ወለድኩ›› የምትለው የፋሽን ዲዛይነሯ፣ በአዲስ አበባ ኑሮዋን ብታደርግም በባለቤቷ ስራ ምክንያት ወደ ትውልድ አካባቢዋ ደብረብርሀን ከተማ ለመመለስ ተገደደች። ወደ ደብረብርሃን የመመለሷ ዋና ሀሳብ ባለቤቷ በከፈተው ትምህርት ቤት በመስራት ድጋፍ ማድረግ ቢሆንም እንዳሰበችው ግን እቅዷን ሳታሳካ ቀረች። ይህን ጊዜ በራሷ የንግድና የፋሽን ዲዛይን ሀሳብ ተጠመደች።

የሰናይት የልጅነት ሕልሟ የዲዛይንና ፋሽን ሙያ ለዓመታት በቤት ውስጥ ብቻ ተገድቦ ቆየ። ልጆቿንና ቤቷን በፈጠራ ስራዎቿ ማስዋብ ብትችልም ወደ አደባባይ ወጥታ ሙያዋን ለማሳደግ ግን ሁኔታዎች አልፈቀዱላትም ነበር። ወደ ሕልሟ ለመቅረብ ግን ጥረቷን አላቆመችም። እዚያው ደብረብርሃን እያለች የሴቶች አልባሳት መሸጫ ቤት የመክፈት ሀሳብ ይመጣላታል። ወዲያው ተግባራዊ ታደርገዋለች። በጊዜው ሴቶች ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ ቡቲክ ቤት ስላልነበር የንግድ ሀሳቧ ወዲያው ተቀባይነት አገኘ።

በሳምንት ሁለት ሶስት ጊዜ ወደ መርካቶ በመምጣት ተወዳጅነት ያላቸው አልባሳትን መርጣ በማቅረብ ገበያውን መቆጣጠር ቻለች። ከቀድሞ ስራዋ አንፃርም ልብስ ቤቱ ለፋሽንና ዲዛይን ፍቅሯ የቀረበ በመሆኑ በፍላጎት ነበር የምትሰራው። በዚህ ሁኔታ በደብረብርሃን ለአራት ዓመታት ስትሰራ ቆየች። በትውልድ ከተማዋ የጀመረችው ንግድ ግን ሊዘልቅ አልቻለም። ምክንያቱ ደግሞ ለልጆች የተሻለ ትምህርት ፍለጋ በቋሚነት አዲስ አበባ መመለስ ነበረባት።

### ወደ አዲስ አበባ

ዲዛይነር ሰናይት ቤተሰቧንም ንግዱንም ወደ አዲስ አበባ በቋሚነት ይዛ መጣች። በወቅቱ የባለቤቷ ስራ ደብረብርሃን የሚያመላልስ በመሆኑ ልጆቻቸውን የመንከባከብ ተደራቢ ኃላፊነት ነበረባት። ለጫናው ሳትበገር ስራዋን ቀጠለች። በተጨማሪም ለፋሽን ዲዛይኒንግ ሙያዋ የሚያግዛትን ትምህርት ከአልባሳት ንግዱ ጎን ለጎን መማር ጀመረች።

አጫጭር ስልጠናዎችን በተለያዩ የፋሽን ዲዛይኒንግ ትምህርት ቤት ወሰደች። በዚህ ሳታበቃ አራኬል በሚባል ኮሌጅ በጀርመኖች ስፖንሰር አድራጊነት የሚሰጥ ስልጠናን ተከታተለች። ቀድሞ የነበራት ልምድና ተሰጥዖ ስላገዛት አራት ዓመት የሚወስደውን ስልጠና በአንድ ዓመት ውስጥ በብቃት ልታጠናቅቅ ቻለች። ከዚህ በኋላ ነበር ሰናይትና የፋሽን ዲዛይን ሙያ በሙሉ ጊዜ የተገናኙት።

ስልጠናዎቹን እንዳጠናቀቀች ባለቤቷ በስጦታ በገዛላት ልብስ መስፊያ ማሽን (ሲንጀር) በቤት ውስጥ የፈጠራ ውጤቶቿ የሆኑ አልባሳት መስራት ጀመረች። የትዳር አጋሯ ድጋፍና ማበረታታት ወደ ስኬት ይገፋት ጀመር። ጓደኞቿ፣ በማኅበራዊ ድረ ገፅ የምታገኛቸው ደንበኞች ጭምር ምርጫቸው አደረጓት። በዚህ ጊዜም ከሙያዋ ጋር የተያያዙ የፈጠራ ውጤቶቿ ሕይወት መዝራት የጀመሩ።

### ኮቪድ-አዲስ የፈጠራ መንገድ

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለማችን ላይ መከሰት ሰናይትና ባለቤቷ የጀመሩትን ንግድ ክፉኛ ጎዳው። ትምህርት ቤቱንም አልባሳት መሸጫውንም ለመዝጋት አስገደዳቸው። ሰናይት ግን ዓለም አቀፍ ፈተናን በደቀነው ወረርሽኝ ምክንያት እጅ ለመስጠት አልፈቀደችም። ይልቁኑ በቤት ውስጥ ለረጅም ጊዜ መቀመጧ ለአዲስ የፋሽን ዲዛይኒንግ ፈጠራ ሀሳብ ረድቷታል። በብዛት የሰራቻቸውን አልባሳት ለማስተዋወቅና የሙያ ደረጃዋን ለማሳደግ የጎዳና ላይ ፋሽን ትርዒት የማዘጋጀት ሀሳብ የመጣላትም በዚያው ጊዜ ነበር። በማኅበራዊ ሚዲያ ስራዎቿን ማስተዋወቅም ቻለች።

‹‹በኮቪድ ጊዜ በርካታ ልብሶችን ዲዛይን ማድረግ ቻልኩ። ኢትዮጵያዊ ባሕልን የሚወክሉ፣ ዘመናዊና ለተለያየ የአየር ፀባይ ወቅቶች የሚለበሱ ነበሩ›› የምትለው ዲዛይነር ሰናይት፤ በቀላል ወጪና በአገር ውስጥ በሚገኙ ጨርቆች አስውባ እንደሰራቻቸው ትናገራለች። እነዚህን ልብሶች የምታስተዋውቅበት አጋጣሚ ስታስብ ነበር ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ያልተለመደውን ‹‹የጎዳና ላይ የፋሽን ትርዒት›› ለማዘጋጀት የወሰነችው።

### የጎዳና ላይ የፋሽን ትርዒት

የሰራቻቸው አልባሳት ለእይታ እንዲበቁና እንዲተዋወቁ እውቅ ሞዴሎችን ተጠቅማ የፋሽን ትርዒት ለማዘጋጀት ወሰነች። ሂደቱ ግን ቀላል አልነበረም። ሕዝብ የሚበዛበት አካባቢ የሚገኙ ሕንፃዎች በር ላይ ፍቃድ ለማግኘት እልህ አስጨራሽ ትግል አድርጋለች። ተባባሪ አካላትን በሚፈለገው መንገድ አለማግኘት፣ የፋይናንስ እጥረትና አንዳንድ አካላት ለዘርፉ ትክክለኛ ግንዛቤ አለመያዛቸው ቢፈትናትም እጅ እንዳልሰጠች ትናገራለች።

የጎዳና ላይ ፋሽን ትርዒቱን ለማድረግ ያሰበችበት ዋና ዓላማ ኢትዮጵያዊ ምርት፣ ቀለምና ባሕል ያለውና ዘመናዊ ልብስ በቀላል ዋጋ ሊሰራ እንደሚችል ለማኅበረሰቡ ግንዛቤ ለመፍጠር ነበር። ይህንን ሀሳቧን ይዛ አልባሳቱን ዲዛይን አድርጋ እና ሞዴሎቿን መርጣ አጠናቀቀች።

ከብዙ ጥረት በኋላ የጎዳና ላይ የፋሽን ትርዒቱንም በገርጂ አልፎዝ ህንፃ ስር ለብዙ ሺ ሕዝብ በነፃ አሳየች። ወቅቱን መለስ ብላ ስታስበው ‹‹ፈተናዎች የነበሩት ቢሆንም እጅግ ስኬታማና ለዛሬ የፋብሪክ ፋሽን ዲዛይን ትምህርት ቤት መፀነስ መሰረት ነበር›› ትላለች።

### ፋብሪክ- የዲዛይንና ፋሽን ማሰልጠኛ

ዲዛይነር ሰናይት የመጀመሪያውን የጎዳና ላይ ፋሽን ትርዒት ካደረገች በኋላ ስራዎቿ በብዙሃን ዘንድ ተቀባይነት አገኙ። በሙያው የበለጠ አስተዋጽኦ እንዲኖራት የሚገፋፏት በዙ። በርካታ ደንበኞችን አፈራች። ከዚህ በኋላ ነበር ለበለጠ ራዕይ መትጋት የጀመረችው። እርሷ የመጣችበትን መንገድ ለማቅለልና በሙያው ብዙሃንን ለማፍራት በማሰብ የዲዛይኒንግ ትምህርት ቤት ለመክፈት ወሰነች። በዚህ ጊዜም የባለቤቷ ድጋፍ አልተለያትም። እቅዷን በአምስት ዓመት ውስጥ ለማሳካት አስባ የነበረ ቢሆንም፣ በሁለት ዓመት ውስጥ ተግባራዊ አደረገችው። ፋብሪክ የዲዛይኒንግ ትምህርት ቤት በተለምዶ ፊጋ ፍየል ቤት በሚባለው አካባቢ በሰናይት ራዕይ ከስምንት ወር በፊት ተመሰረተ።

የሰናይት የዲዛይኒንግና ፋሽን ሙያ ከንግድና ከጎዳና ፋሽን ትርኢት አልፎ የዘርፉ የልህቀት ማእከል ለመሆን እየተንደረደረ ይገኛል። በመጀመሪያው ዙር ከ90 በላይ ተማሪዎች ሙያውን ተምረዋል። መምህራንን ጨምሮ ስምንት ሰራተኞችን ቀጥራ እያሰራች ትገኛለች። የጎዳና ላይ የፋሽን ትርዒቱንም ለሁለተኛ ገዜ በራሷ ዲዛይንና ሞዴሎች ለእይታ አብቅታለች።

‹‹ተማሪዎቼ ሕልማቸውን እንዲከተሉ አበረታታለሁ። ያለኝን እውቀት ሳልሰስት ልክ እንደቤተሰብ አጋራለሁ›› የምትለው ሰናይት፤ ማኅበራዊ ኃላፊነቷን ለመወጣት ሙያውን መማር ፈልገው አቅም ለሌላቸው ተማሪዎች የነፃ የትምህርት እድል እንደምትሰጥም ትናገራለች። አጠቃላይ ተማሪዎቿ ቤተሰባዊ ስሜት እንዲያድርባቸው ከማድረግ ባሻገር የሚማሩበት ከባቢ ምቹና ንፁህ እንዲሆን እንደምትተጋ ትገልፃለች። ሕሊና እረፍት አግኝቶ የፈጠራ ስራም የሚበረታታው ምቹ ከባቢ ሲኖር እንደሆነ ስለምታምን ትምህርት ቤቷም በዚያ የተቃኘ ነው።

### የዲዛይነሯ ራዕይ

ዲዛይነር ሰናይት ፋብሪክ በፋሽን ኢንዱስትሪው ተፅእኖ የሚፈጥሩ ባለሙያዎችን እያፈራ እንደሚቀጥል ትናገራለች። ቅርንጫፎችን አስፍታ ዓለም አቀፍ ደረጃ ላይ መድረስ ቀጣይ ሕልሟ ነው። ኢትዮጵያዊ ቀለምና የባሕል ተፅእኖ ያረፈባቸውን አልባሳት በጋርመንት (ኢንዱስትሪ ደረጃ) ለማቅረብ እንደምትተጋም አልሸሸገችም።

ሌላው የዲዛይነር ሰናይት እቅድ ለሁለት ጊዜ ያካሄደችውን የጎዳና ላይ የፋሽን ትርዒት ዓለም አቀፍ ደረጃውን ጠብቆ በኢትዮጵያ፣ በአውሮፓ፣ በአፍሪካና በልዩ ልዩ የዓለማችን ክፍሎች ማቅረብ እንደሆነ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራት ቆይታ አጫውታናለች። እኛም የልብ መሻቷ እንዲደርስ እየተመኘን ለዛሬው አበቃን!!

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የመንገድ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ መጓተት - ማነጋገሩን ቀጥሏል

**በኃይሉ አበራ**

ሀገሪቱ በአስር ዓመቱ መሪ እቅድ ትኩረት ለመሠረተ ልማት ግንባታ ትኩረት ሰጥታለች፡፡ በእዚህም ከሚገነቡት መካከል የመንገድ መሠረተ ልማቶች ይጠቀሳሉ። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባለፈው 2015 በጀት ዓመት ባደረገው አንድ መድረክ ላይ እንደተጠቆመው፤ ሀገሪቱ አንድ ትሪሊዮን ብር የሚጠይቁ ከ22 ሺ ኪሎ ሜትር በላይ የአስፋልት ኮንክሪት የመንገድ ግንባታዎችን እያካሄደች ነበር፡፡

ሀገሪቱ የመንገድ መሠረተ ልማትን ጨምሮ ለልማት አስፈላጊ የሚባሉ መሠረተ ልማቶችን በመገንባት እነዚህ ግንባታቸው በተለያየ ደረጃ ከሚገኙ የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታዎችና በቀደሙት ዓመታት ከተካሄዱ የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ሀገሪቱ የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታዎችን ከዚህም በላይ ማካሄድ የምትችል ቢሆንም፣ በዘርፉ በሚታዩ ለመንገድ ግንባታ ተግዳሮት በሆኑ ችግሮች ሳቢያ አፈጻጸም ላይ ክፍተት ይታይባታል፡፡ ከካሳ ክፍያ፣ ከወሰን ማስከበር፣ ከግብአት አቅርቦት እጥረትና ከመሳሰሉት ጋር በተያያዘ የመሠረተ ልማት ግንባታ ስራዋ በእጅጉ እየተፈተነ ይገኛል፡፡ ሰሞኑን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴርንና የተጠሪ ተቋማቱን የ2016 በጀት ዓመት ያለፉትን ስድስት ወራት ሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ባዳመጠበትና እሱን ተከትሎ በተካሄደው ውይይት ላይ የተጠቆመውም ይሄው ነው፡፡

በመድረኩ ላይ እንደተጠቆመው፤ በሀገሪቱ በየክልሉ ግንባታቸው እየተካሄደ ባለ የመንገድ መሠረተ ልማት ሥራዎች ላይ የመጓተት ችግሮች በስፋት ይስተዋላሉ። በየክልሉ ለሚገኙ የመንገድ ፕሮጀክቶች በወቅቱ አለመጠናቀቅ የተቋራጮችና አማካሪዎች የማስፈፀም አቅም ችግሮች በተግዳሮትነት ሲነሱ ቆይተዋል። የጥራት መጓደል፣ ለልማት ተነሺዎች የካሳ ክፍያ በወቅቱ አለመፈፀም፣ የፕሮጀክት በጀት ክፍያ በወቅቱ አለመለቀቅ፣ ከዋጋ ንረት ጋር የተያያዙ እንዲሁም የግብአት ችግሮች ሌሎች በዋናነት የሚነሱ ችግሮች ናቸው፡፡

የሚኒስቴሩን ሪፖርት ያዳመጡት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በየክልሉ ግንባታቸው የተጓተተ የመንገድ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችንና የመንገድ ጥገና ስራዎችን የተመለከቱ ጥያቄዎችን አቅርበው ምላሽና ማብራሪያ እንዲሰጥባቸውም ጠይቀዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማ መሠረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ፣ ቋሚ ኮሚቴው ክትትል ካደረገባቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች መካከል የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው 45 ፕሮጀክቶች ብቻ ናቸው፡፡ 109 ፕሮጀክቶች መጓተታቸውን ጠቅሰው፣ 84 የመንገድ ፕሮጀክቶች ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ግንባታቸው የተቋረጠ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ የምክር ቤት አባላት የመረጣቸውን ሕዝብ በሚያወያዩበት ጊዜ ሕዝቡ ቅሬታ ካነሳባቸው መካከል አንዱ የመንገድ ፕሮጀክቶች መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ እንደሚገባ አሳስበዋል።

እቅድ ተይዞላቸው ያልተሰሩ መንገዶችን፣ ሥራቸው ተጀምሮ የተጓተቱ የመንገድ ፕሮጀክቶችን፣ በከተሞች ያለው የመሬት አስተዳደር ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጥ መሆኑንና በትክክል ካሳ ለተገመተላቸው የመሬት ባለቤቶች በወቅቱ ካሳ እየተከፈለ አለመሆኑንም የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አመልክተው፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ምላሽና ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል ።

ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱት የመንገድ እና ሌሎች የከተሞች መሠረተ ልማት ጥያቄዎች የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ በሰጡት ምላሽና ማብራሪያ፤ የሕዝቡ የአገልግሎት ፍላጎት የመንገድ መሰረተ ልማት ማግኘት መሆኑንና ጉዳዩ በትኩረት እንደሚታይም አስታውቀዋል። የማህበረሰቡ ትኩረት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ትኩረት መሆኑን አስታውቀው፣ የተነሱት ገንቢ ሀሳቦችና ጥያቄዎች መሆናቸውን ተናግረዋል፤ ሁሉም በእቅድ ተይዘው እየተሰራባቸው መሆኑን አመልክተዋል።

በመንገድ ፕሮጀክቶችን ላይ የሚታየውን ችግር በየደረጃው ለመፍታት እንደሚሰራ ጠቅሰው፣ለእዚህም ሚኒስቴሩ በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ የሚሠሩ በሚል ለይቶ ችግሮቹን ለመፍታት መስራት መጀመሩን ገልጸዋል፡፡

በአዎንታዊነት የሚወሰዱ ስራዎች አንዳሉም ጠቅሰው፣ የተቋሙ የማስፈፀም አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ገልጸዋል፡፡ ለእዚህም በቱሪዝም መዳረሻ አካባቢዎች በርካታ የመሠረተ ልማት ግንባታ ስራዎች መካሄዳቸውን በአብነት ጠቅሰዋል፡፡ እነዚህ ግንባታዎች በፍጥነት እየተሰሩ መሆናቸውንም ነው ያመለከቱት። ቱሪዝሙም ያለመንገድ እና ያለመሠረተ ልማት እውን መሆን እንደማይችል አስታውቀው፣ ተጨማሪ ፕሮጀክቶች ለመሥራትም መሥሪያ ቤቱ አቅም እየፈጠረ መሆኑንም ተናግረዋል።

ከፍተኛ የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ያለውን የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታ በፀጥታ ኃይሎች ትብብር እንዲጠናቀቅ የሚደረግበት ሁኔታ እንዳለም ጠቅሰው፤ ለእዚህም እየተከፈለ ያለ ዋጋ ትልቅ ነው ብለዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች ያለው የፀጥታ ችግር ፕሮጀክቶች በሚከናወኑባቸው እና ግብአት የሚወጣባቸው አካባቢዎች ላይ ችግር እያስከተለ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሚኒስትሯ እንዳሉት፤ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ላይ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ፡፡ የሙያ እና ከማስፈፀም አቅም እንደተጠበቀ ሆኖ ከግብአት ጋር የተያያዘው በተለይ የሲሚንቶ እጥረት በከፍተኛ ደረጃ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡ የአስፓልት እጥረት ሌላው ተግዳሮት ሲሆን፣ ይህን ከውጭ ሀገር የሚመጣ ግብአት ችግር መፍታት የሚቻልበትን አማራጭ ለማግኘት የሚያስችል የቤት ሥራ ተወስዶ እየተሰራበት ነው። በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የምርምር ማዕከልም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ የመጣውን የአስፓልት ግብአት መተካት በሚያስችሉ አማራጮች ላይ ምርምሮች እየተካሄዱ ይገኛሉ።

ግንባታ ብቻም ሳይሆን ከግንባታ በኋላም ለግንባታ የሚወጣውን ያህል ወጪ ለጥገናም እንደሚወጣ ሚኒስትሯ ጠቁመው፣ በዚህ ሥራ እያተረፍን ነው ወይ የሚለውን ለመመለስ ከባለሙያዎች እና ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የጥናት ማዕከል በጋራ በመፍጠር ሃሳብ ለማፍለቅ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም አንስተዋል። በጥናቱም አንድ መፍትሄ ላይ ሲደርስ የግብአት ችግሮችን በመሠረታዊነት በብዙ ርቀት መፍታት እንደሚቻል ይገልፃሉ።

ሚኒስትሯ እንዳብራሩት፤ ሌላው የዘርፉ ችግር ከወሰን ማስከበር ጋር የተያያዘው ነው፡፡ የወሰን ማስከበር ጉዳይ የመንገድ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም መሠረታዊ ተግዳሮት መሆኑ ቀጥሏል። በፌዴራል እና ክልሎች ለተመሳሳይ የመሠረተ ልማት ግንባታ ለተመሳሳይ ቦታ ክልል ለያዘው ፕሮጀክት እና የፌዴራል መንግሥቱ ለያዛቸው ፕሮጀክቶች የተለያየ አገር ውሳኔ የሚመሥሉ የካሳ ጥያቄዎች ይቀርባሉ። ይህን ችግር በተለመደው መንገድ ብቻ በመሄድ መፍታት አይቻልም፤ ሁሉም ሰው በየአካባቢው ያሉ ማነቆዎችን ለመፍታት እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል፤ በተለይ ክልል አካባቢ ያሉትን ችግሮች በምን መልኩ በመሠረታዊነት መፍታት እንችላለን የሚል ትልቅ ሰነድ አዘጋጅተናል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ሰነዱ ለእዚህ ምክር ቤት እንደሚቀርብም አስታውቀዋል፡፡

አሁን እየተሰራበት ባለው መንገድ የአንድ የመንገድ ፕሮጀክት ዋጋ አንድ ቢሊዮን ብር ከሆነ ለካሳ ክፍያ የሚጠየቀው ሁለት ቢሊዮን እየሆነ መምጣቱ እንደማይቀርም አስገንዝበዋል፡፡ ይህም ትርፍ ነው ወይስ ኪሳራ የሚለውን በሕዝብ ሀብት አተያይ በማየት ስራውን ማስተዳደር የሚቻልበት ውሳኔ እንደሚፈለግ ጠቅሰው፤ ይህም የዘርፉ አንዱ መሠረታዊ ችግር መሆኑን አንስተዋል።

የካሳ ክፍያው በትክክለኛ መንገድ ተገምቶ የመጣ ሆኖም ተቋሙ ጋ ሲደርስ በተለያየ ምክንያት በተለይም ከበጀት እጥረት አኳያ ክፍያው በወቅቱ እየተፈጸመ ያልሆነበት ሁኔታ እንዳለ ጠቅሰው፣ ከዚህ ውጪ መንግስት የሚቻለውን ሁሉ ለመንገድ መሰረተ ልማት ዘርፉ ክፍያ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል፡፡ በመሆኑም ተቋሙ የሚጠይቃቸው የካሳ ክፍያ በጊዜ ከመክፈል ጋር የተያያዙ ችግሮች በከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር

> **ቋሚ ኮሚቴው ክትትል ካደረገባቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች መካከል የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው 45 ፕሮጀክቶች ብቻ ሲሆኑ፣ 109 ፕሮጀክቶች ተጓትተዋል፤ 84 የመንገድ ፕሮጀክቶች ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ግንባታቸው ተቋርጧል**

መስሪያ ቤት በኩል እንደ ክፍተት የሚወሰዱና መፈታት ያለባቸው መሆናቸውን ገልጸዋል፤ ችግሮቹ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ሲንከባለሉ የመጡና ችግሮቹን መፍታት እንደ ተቋም የሁሉንም አካላት ድጋፍ የሚጠይቅ መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑን አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል ለፕሮጀክቶች መተግበሪያ ከሚለቀቀው ክፍያ መዘግየት ጋር የተያያዙ መሠረታዊ ችግሮች መኖራቸውንም ሚኒስትሯ አመልክተዋል፡፡ የተቋራጮች፣ የአማካሪዎች፣ የማስፈጸም አቅም ችግር እንዳለም ጠቅሰው፣ ለሰሩት ስራ በመሠረታዊነት መክፈል ሲቻል ብቻ ፕሮጀክቱን ወደፊት ማስኬድ እንደሚቻልም ይገልፃሉ። መንግሥት የተቻለውን ያህል ክፍያ ለመሠረተ ልማት ዘርፉ ቅድሚያ እየሰጠ እንደሚገኝ አስታውቀው፣ አሁንም ያሉበትን መሠረታዊ እጥረቶች ለመፍታት መረዳዳት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ በተለይ ከመንገድ መሠረተ ልማት ጉዳይ ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር በመሠረታዊነት ለመፍታት ባለፈው ዓመት የተፈጠሩት የአደረጃጀት እና የአሰራር ማዕቀፎች እገዛ ወሳኝ ነው። ይህ አሰራር በየአካባቢው የሚገኙትን 188 የመንገድ ፕሮጀክቶች ለመቆጣጠር አስችሏል።

ከማዕከል ብቻ ሆኖ እነዚህን ሁሉ የመንገድ ፕሮጀክቶች መቆጣጠር እንደማይቻል ሚኒስትሯ አስታውቀው፣ በአካባቢው ያለው የፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማኔጅመንት ፅሐፊ ውሳኔ ማሳለፍ በሚችልበት መንገድ በሰው ኃይል እና በአደረጃጀት ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ ይህም በሂደት የሚያመጣቸውን ለውጦች በመወሰድ ችግሮችንም በአደረጃጀት ለመፍታት ጥረት እንደሚደረግ ተናግረዋል።

ከከተማና መሠረተ ልማት ውጪ በሆኑና የሌላ ዘርፍ ተሳትፎን እና የመንግሥትንም ድጋፍ በሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመሥራት እና ስራዎችን ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ በመምራት ከመንገድ ጋር የተያያዙ ፈተናዎችን ለመፍታት መልካም አጋጣሚዎችን መጠቀም እንደሚያስፈልግም ሚኒስትሯ አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር መሐመድ አብዱራህማን በበኩላቸው፤ ከመንገድ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችና ከጥገና ስራዎች ጋር ተያይዞ ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል። እሳቸው እንዳብራሩት፤ የዓለም ገና ቡታጀራ መንገድ ፕሮጀክት አካል የሆነው የሆሳዕና ከተማ መንገድ እና የፍሳሽ መሄጃ ስራዎች በጥሩ ሁኔታ እየተከናወኑ መሆናቸውን ይገልፃሉ። ፕሮጀክቱ በግል የሥራ ተቋራጭ ይሰራ እንደነበረ አስታውሰው፣ የመንገድ አስተዳደር መስሪያ ቤቱ በአፈፃፀም መጓደል በታዩ ክፍተቶች በተቋራጩ ላይ እርምጃ መውሰዱን አስታውቀዋል።

የመንገድ አስተዳደር መስሪያ ቤቱ እርምጃዎችን የመወሰድ እና ማስተካከያዎችን የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት ጠቅሰው፣ በዚህ መሰረትም እርምጃዎችን እየወሰደ መሆኑንም አስታውቀዋል። የአፈፃፀም ጉድለት በሚታይባቸው የሥራ ተቋራጮች ላይ ኮንትራቱን እስከማቋረጥ የሚደርስ እርምጃ የመውሰድ ሁኔታዎች እንዳሉም ጠቅሰው፤ ለእዚህም በማሳያነት በሆሳዕና ከተማ በሚሰራው የአምስት ኪሎሜትር መንገድ ሥራ ተቋራጭ ላይ የተወሰደን እርምጃ ገልጸዋል፡፡ የተቋራጩ አፈፃፀም አመርቂ ባለመሆኑ ኮንትራት በማቋረጥ በራስ አቅም እንዲሰራ መደረጉን ጠቁመዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳብራሩት፤ የመንገድ አስተዳደሩ በስድስት ወራቱ ለመከወን ካቀዳቸው 54 የዲዛይን ፕሮጀክቶች መካከል 21 ያህሉን በጸጥታ ችግር መተግበር አልቻለም። የስድስት ወራቱ የዲዛይን ስራዎች አፈጻጸም 57 በመቶ መሆኑም ሌላው ለአፈጻጸሙ ዝቅተኛነት በምክንያትነት የሚጠቀስ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በውጭ አማካሪ ድርጅት ለተሰራ ሥራ ክፍያ ለመፈጸም የውጭ ምንዛሪ መዘግየት ማጋጠሙን ጠቅሰው፣ በዚህ የተነሳ የተጓተቱ ፕሮጀክቶች መኖራቸውንም ዋና ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል። በተለያዩ ምክንያቶችም 84 ፕሮጀክቶች መቋረጣቸውን እና ሙሉ በሙሉ የኮንትራት ውላቸው መሰረዙንም ይናገራሉ። የግብዓት እጥረት፣ የወሰን ማስከበር ችግር እና የተጋነነ የካሳ ተመን ችግሮች መቀጠላቸውንም አስታውቀዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ በመንገዶች ጥገና እና ግንባታ በስድስት ወራቱ የተሻለ አፈጻጸም የታየበት ሁኔታ መኖሩንም ይጠቁማሉ። በአሁኑ ሰዓት አጠቃላይ የመንገድ ሽፋን በኢትዮጵያ 169 ሺህ 450 ኪ.ሜ መድረሱን ኢንጂነር መሐመድ አብዱራህማን አስታውቀዋል፤፤ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት የተቋረጡ 64 የመንገድ ፕሮጀክቶች መካከልም 15ቱን ማስጀመር መቻሉን አስታውቀዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ የመንገድ ፕሮጀክቶች ስኬቶች፣ መሠረታዊ ተግዳሮቶች እንዲሁም ቀጣይ ስራዎች በምን መልኩ መከናወን ይገባቸዋል በሚሉት ላይ በልዩ ሁኔታ መነጋገር እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ከካሳ ክፍያና ከሥራ ተቋራጮች ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች እንዲሁ ተቋም ውስጥም ያሉ ጉዳዮችና ተግዳሮቶችን መነሻ በማድረግም በቀጣይ በምን መልኩ ማስኬድ እንደሚገባ በጥናት በመለየትና የሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎችን በመጠቀም በሁሉም አካባቢዎች ያሉ የመንገድ መሠረተ ልማት ችግሮችን በመሠረታዊነት መፍታት እንደሚገባ አስታውቀዋል።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# ተፈጥሮ እና ሰው (ቅድመ እና ድህረ 1800)

ግርማ መንግሥቴ

ባልታሰበና ባልተጠበቀ ሁኔታ ወደ'ዚህ ከባድና ውስብስብ ርእስ ተገባ። እየከበደ በሄደ ቁጥር እልህ እየፈጠረ በመምጣቱ ምክንያት ላለመፋታት ውሳኔ ላይ ተደረሰ። እነሆም በሚከተለው መልክ ይቀርብ ዘንድም ፍቃድ ሆነ።

ለነገሩ፣ የተፈጥሮን አንድ በመቶ (100%) እንኳን ገና ላላወቀው ሰው ስለ "ሰው እና ተፈጥሮም ይሁን "ተፈጥሮና ሰው ለመጻፍ ቀርቶ ለአፍታ እንኳን ለመናገር ቢከብድና ቢቸግረው ምንም የሚደንቅ ነገር የለውም። ምክንያቱ ደግሞ ስለማያውቁት ነገር ለመጻፍ መሞከር በራሱ አለማወቅ ነውና ነው።

ነገር ግን፣ ሰው የተፈጥሮን አንድ በመቶ እንኳን ገና አላወቀም ማለት ሰው ከተፈጥሮ ውጪ ነው ማለት ባለ መሆኑ፤ ተፈጥሮና ሰው ገና በቅጡ አልተዋወቁም ማለት ተፈጥሮ ለሰው ልጅ ያበረከተችው፣ እያበረከተች ያለችውንና ልታበረክት የምትችለውን አለማወቅ ማለት ባለ መሆኑ፤ ሰው ስለ ተፈጥሮ ምንም አላወቀም ማለት ከተፈጥሮ ጋር እየተጣላ አይደለም ማለት ባለመሆኑ፤ ሰው "ተፈጥሮን በቁጥጥር ስር ለማዋል ባለው መሰረት የለሽ ቅዥትና ከጣራ በላይ ፍላጎት በራሱ ላይ ቅጣትን እያወረደ አይደለም ማለት ስላልሆነ ወዘተ ስለ ተፈጥሮ እና ሰው ለመጻፍ ሙከራ ማድረግ ባያሸልም እንኳን አያስጠይቅምና (አንባቢ እያነበበ እንዳለው) እየሞከርን እንገኛለን።

በነገራችን ላይ፣ ሰው እና . . .፤ ሰው እና . . .፤ . . . እና ሰው፤ ሰው እና . . .፤ እየተባለ ብዙ ሲነገር (ለምሳሌ"ሰውና እግዚአብሔር፣ "ሰውና መላእክት . . .)፤ ብዙም ሲጻፍ ይታያል። እነዚህ ሁሉ በሚባሉበት ወቅት ከበስተ ጀርባቸው ያለው ምንድን ነው? ሰው ከተፈጥሮ ተነጥሏል ማለት ነው፣ ሰውና ተፈጥሮ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው/አይደሉም ለማለት ነው? ሰውና ተፈጥሮ በትክክል ተገናኙ የሚባለው መቼና ምን ሲሆን ነው? ሰው የአምላኩን ትእዛዝ እየፈፀመ ነው? ሰው ከፈጣሪው ጭምር እየተጣላ ነው? ሰው ከራሱ ከሰው ጋር እየተጣላ ነው? የምሁራንን ማብራሪያ ይጠይቃል።

ለምሳሌ ያ ሰውዬ "ሰው ማህበራዊ እንስሳ ነው አለ ተብሎ ሲነገር ስለ መኖሩ ሁላችንንም ዋቢ አድርጎ አደባባይ የሚወጣ ካለ ያዋጣዋል። ያኛው ደግሞ "ሰው ፖለቲካዊ እንስሳ ነው አለ ተብሎ በተገኘ መድረክ ሁሉ በጆሯችን ሲንቆረቆር ስለ መኖሩ አሁንም ምስክሮቹ እኛው ነን። ሀበሻ በቀበሮ አሳብቦ "ለሰው ሞት አነሰው ማለቱን እዚህ ላይ ላስታወስ ጉዳዩ እንቆቅልሽ እየሆነበት እንደሚሄድ ምንም ጥርጥር የለውምና እንዳላነሳነው ተቆጥሮ ማለፉ የተሻለ ይሆናል። "እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ተፀፀተ የሚለውንም እንደዛው።

"ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ለእግዚአብሔር ክብር የተፈጠረ ከፍጥረታት ሁሉ የላቀ፤ በራሱ ነፃ ምርጫ የሚንቀሳቀስ ህያው ፍጥረት ነው፡፡ የሚለው ኃይማኖት ነክ ብያኔ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለውና እድሜ ጠገብ አተያይና ግንዛቤ ነው። እንዲሁም፡-

ሰው ዓለም ሳይፈጠር በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የነበረ እና በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ለእርሱ ክብር የተፈጠረ ነው (ኤፌ 14፡11-12፤ ዘፍ 1፡ 1 – 25 ኢሳ 43፡7)፤ ሰው እንደ እንስሳ በደመነፍስ የሚንቀሳቀስ ሳይሆን ክፉንና ደጉን የሚለይ ግብረገባዊ ፍጡር መሆኑ (ዘፍ 2፡ 15 – 17)፤ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሰው የሚያስፈልገውን ሁሉ ካዘጋጀ በኋላ ሰውን በመልኩና ባምሳሉ ፈጠረው፤ ሰው የእግዚአብሔር ተወካይ ወይም እንደራሴ በመሆን ምድርን የሚያስተዳድር ችሎታ ያለው (ዘፍ 2፡ 15 – 17) ነው የሚለው ገዥ ቃል ስለ ሰው በተነሳ ቁጥር ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም። በሌሎች ኃይማኖቶችም ተመሳሳይ ባይሆን እንኳን የተራራቀ እንደማይሆን ተስፋ አለ።

**ተፈጥሮና ፍጥረታትን በተመለከተ ደግሞ፤**

እግዚአብሔር ፍጥረታትን የፈጠረው ሰውንና መላእክትን ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ ሲሆን የተቀሩትን ፍጥረታት ግን ለአንክሮ ለተዘክሮ ለምግብ ስጋ፣ ለምግብ ነፍስ ነው። (መዝ.148፣1-3፤ ራዕ4፣11፤ የሐ.ሥራ14፣17፤ ሮሜ.1፣20)፤ ሰው ከፍጥረታት ሁሉ የከበረ ነው፡፡ (መዝ.48፣12)፤ በመሆኑም፣ በምድር ላይ የሚኖሩ ፍጥረታት በሙሉ ገዥ፣ አዛዥ ሊሆን ችሏል ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ፈለገው በተፈጥሮ ዘና ይል ዘንድ ተፈቅዶለታል ማለት ነው - "በአግባቡ ከሚለው ራሱን ነጠለ እንጂ።

እዚህ ላይ፣ "ሰውን በተመለከተ አንድ ማጠናከሪያ ሀሳብ ይሆነን ዘንድ ወንጌል የተባሉ ሰው በአንድ ጽሑፍ መግቢያቸው ላይ "ሰው ምንድ ነው? የሚለው ጥያቄ ያለጥርጥር እጅግ መሠረታዊ የሆነ የፍልስፍናና የሥነ-መለኮት ተግባራዊ ጥያቄ ነው። ሰዎች መጀመሪያ ከየት መጣን? ለምንስ መጣን? መሄጃችንስ ወዴት ይሆናል? የሚሉና ሌሎችም ተመሳሳይ ጥያቄዎች ይሆናሉ። ፍልስፍና እዚህን ጥያቄዎች ለማጥናትና መልስ ለማግኘት በየዘመናቱ በተነሱ ፈላስፋዎቹ አማካይነት የተለያዩ ሙከራዎችን አድርጓል። የብዙዎቹን ፍልስፍናዎች የአጠናን ዘዴና መልሶቻቸውን ስናይ፣ ሰዎች ለእነዚህ ጥያቄዎች እርግጠኛ መልስ ለማግኘት አለመቻላቸውን እንረዳለን። ያሉትን አስፍረን ወደ ርእስ ጉዳያችን እንመለስ።

ስለ "ሰውም ሆነ "ተፈጥሮ ያልተባለ የለም እና ታሪካዊውን ሀቲት (ኦሪጅን) እዚሁ ላይ ገታ እንድናደርግ እና ወደ ምድራዊው እውነታ እንመለስ።

በሚገባ እንደሚታወቀው፣ ከላይም እንደጠቃቀስነው፣ ሰው ተፈጥሮን የመጠቀም ልዩ እድልን ይዞ ነው ወደዚህ ምድር ዱብ ያለው። በመሆኑም፣ ጥያቄው "ለምን ተጠቀመ?" ሳይሆን "እንዴት ነው እየተጠቀመ ያለው?" የሚለው ነውና እሱን ማየቱ ይበጃል።

አሁን ያለንበት ዘመን በግልፅ እንደሚያሳየው ሰውና ተፈጥሮ ከምር የተጣሉበት ጊዜ ነው ያለው። ወቅቱ ተፈጥሮ አምርራ ከመቀየሟ የተነሳ የሰው ልጅ ላይ ፊቷን ያዞረችበት ከባድ ወቅት ስላለመሆኑ መከራከሪያ ነጥብ የለም። ለዚህ ቀዳሚ ማስረጃና መረጃው ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥ ሲሆን፣ መገለጫውም እየደረሰ ያለው አደጋ፤ እየወደመ ያለው ሀብትና ንብረት፤ እየተራቆተ ያለው አረንጓዴና ለምለምና ለም መሬት፤ እንደ ባለሙያዎች አስተያየት የዚህ ሁሉ ውድመት ተጠያቂው ሰው ሲሆን፤ ምክንያቱ ደግሞ የተፈጥሮና ሰው የከረረ ግጭትና እንደ ቅድመ 1800 ዘመናት እጅ ለእጅ ተያይዞ መሄድ አለመቻል ነው።

"የተፈጥሮ እና ሰው መጋጨት ሲባል ምን ማለት ነው? ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል። "የተፈጥሮና ሰው መጋጨት ማለት የሰው ልጅ በተሰጠው ነፃ ፍቃድ አማካኝነት ተፈጥሮን በአግባቡ መጠቀም ሳይችል ሲቀር፤ ወይንም፣ የአጠቃቀም ጉድለት መታየት ነው ተብሎም ሊመለስ ይቻላል። "ውጤቱስ? ከተባለ ከስነ-ምህዳር ጀምሮ መዛነፍን ማስከተሉ መልስ ሆኖ ቢመጣ፤ ወይም የሰው ልጅ ተፈጥሮን ከመጠቀም ወደ መበዝበዝ (አቢዩዝ፣ ኤክስፐሎይት ማድረግ) መሸጋገሩ ነው ቢባል፤ "ይህ ብቻ አይደለም ካልተባለ በስተቀር "ስህተት የሚል አይኖርም።

ደን "ከምድር መሬት ውስጥ 30 በመቶውን የሚሸፍን እና 80 ከመቶው ብዝሃ-ሕይወቷን የያዘ የሕይወት ድጋፍ ስርዓት" ነው የሚለው የባለሙያዎችና ጥናቶቻቸው ድምዳሜ ላይ ተግባብተም ተጨባጩን ዓለም እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

ድሮ፣ "ተፈጥሮ ሁል ጊዜ የሰዎች መኖ ነች፣ እኛ በሕይወት ለመትረፍ በእሱ ላይ እንመካለን። ሰውና ተፈጥሮ ስምሙ እንደ ነበሩ የማይናገሩ የታሪክ ድርሳናት የሉም - በተለይ ከ1800ዎቹ አስቀድሞ ፍቅራቸው ልዩ ነበር ነው የተባለው። የሁለቱ ፍቅር፤ የሁለቱ ተደጋጋፊነት፤ የሁለቱ ተመጋጋቢነት፤ ለዚህች ውብ ዓለም የሁለቱ አስፈላጊነት እንደ ብርቅ የሚታይበት ዘመን ነበር አሉ። "ዘንድሮስ? ጥያቄው ይሄ ነው።

የደን አያያዝ ልምዶች የምስክር ወረቀትን ለማስተዋወቅ፣ ሕገ-ወጥ የደን ስራዎችን ለመዋጋት፣ የንግድ ፖሊሲዎችን ለማሻሻል፣ የደን አካባቢዎችን ለመጠበቅ እና ሌሎችም ከመንግስት ኤጀንሲዎች፣ ኩባንያዎች፣ ማሕበረሰቦች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ ከሚሰራው፤ አምራቾች በዚህ አቅጣጫ ጥረታቸውን እንዲያረጋግጡ ለመደገፍ የደን ጥበቃ የምስክር ወረቀት አገልግሎት ከሚሰጠው፣ ከ"የዓለም የዱር እንስሳት ፈንድ (WWF) የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ አሁን ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የሰው ልጅ መጥፊያውን የተያያዘው ሲሆን፣ ለዚህም የሚከተሉት ማስረጃዎች ናቸው።

- ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ ወደ 17 ከመቶው የአማዞን ደኖች ጠፍተዋል፤
- በተደረገው ስሌት መሠረት እ.ኤ.አ. በ 2019 ወደ 30 የሚጠጉ የእግር ኳስ ሜዳዎችን የሚያክል ሞቃታማ የደን አካባቢ በየደቂቃው ይጠፋል፤
- ባለፉት 25 ዓመታት ከደቡብ አፍሪቃ ከሚበልጠው አካባቢ ደኖች ቀንሰዋል፤
- በየዓመቱ ስዊዘርላንድ የሚያህል አካባቢ በደን መጨፍጨፍ ይደመሰሳል።

እንደ ዓለም የዱር እንስሳት ፈንድ መሠረት ከሆነ ደኖች የምድር ገጽን ከ30 በመቶ በላይ የሚሸፍኑ ሲሆን፣ እነዚህ የደን አካባቢዎች ከአንድ ቢሊዮን ለሚበልጡ ሰዎች በቀጥታ ምግብ፣ መድኃኒት እና ነዳጅ በቋሚነት ይሰጣሉ፡፡ ይህ ማለት የአንድ ቢሊዮኖች ሕይወት ሙሉ ለሙሉ የተንጠለጠለው በደን ላይ ሲሆን፣ ደን ጠፋ ማለት የእነዚህ ሕይወት አደጋ ላይ ወደቀ ማለት ይሆናል።

ለእናት ተፈጥሮ ተገቢውን ትርጉም ይሰጥ ዘንድ የሚጠበቀው የሰው ልጅ ተፈጥሮን ሲዋጋ እና ሲያወድም የሳተላይት የመሬት ቁጥጥር ስርዓቶች (አገራት ለደን መሬት አጠቃቀሞች እና ለውጦች እና የደን ተግባራት የእንቅስቃሴ መረጃን ለመለየት እና ለመሰብሰብ የሚያግዙት) እንኳን ሊያስታግሱት አልቻሉም፤ ብሔራዊ የደን ፖሊሲዎችን በማቀድ፣ በዘላቂ ልማት ላይ አስተማማኝ የደን ሀብት መረጃን ማዳበርን የሚደግፈው፤ በደን ላይ ጥራት ያለውና አስተማማኝ መረጃን ለማመንጨት የሚተጋው የዓለም እርሻ ድርጅት (ፋኦ) ሀይ ሊለው አልተቻለውም።

ምን ይሄ ብቻ፣ ሰውን የደን ልማት ስትራቴጂ እና የደን ተግባር ዕቅዶች ደንን ከማውደም ሊመልሱት አልቻሉም። ሰው ለደን ደህንነት ሲባል እየተሰራጩ ያሉ መረጃዎች (ለምሳሌ በwww.forestprotection.net ላይ የሚለቀቁ) ሊያስተምሩት፤ ወይም፣ የባህርይ ለውጥ ያመጣ ዘንድ ሊያግዙት አልተቻላቸውም። አይሰማም። እራሱ ካልጠፋ በስተቀር ከጥፋት የሚመለስ ሁሉ አይመስልም። በሌሎች ፍጡራን የማይታየው እራስ በራስ መገዳደል በሰው ልጅ ዘንድ የእለት ተእለት ተግባር ከሆነ ውሎ አድሯል። ለራሱም አልተመለሰ እየተባለ ነው።

ይህ እራስን ማጥፋት ከመምጣቱ በፊት፣ ከላይ በጠቀስነው የመረጃ ምንጭ መሰረት፣ ቀጣይነት ያለው የሰው ልጅ የቀድሞ ዘመን የሰውና የእናት ተፈጥሮ ግንኙነት መመለስ አለበት፤ ማለትም የነበረውንና የተቋረጠውን ግንኙነት ሊያድስ፤ ወደ ቅድመ 1800ዎቹ ክፍለ ዘመናት ሊመለስ ሁኔታዎች እያስገደዱት ይገኛሉ።

እንደ ደን ተንከባካቢ ምክር ቤት (FPC) ጥናት (ሪፖርት) ከግማሽ በላይ የሚሆነው የምድር ምድራዊ ብዝሃ ሕይወት በደን ውስጥ ነው፡፡ ሞቃታማ ደኖች በዛሬው ጊዜ በዓለም ላይ ወደ 90 በመቶ የሚጠጉ ዝርያዎችን ይይዛሉ፡፡ ይህ ማለት ደን ማልት ምን ማለት እንደ ሆነ በራሱ ይናገራልና የሰው ልጅ የደን አያያዝ ጉዳይ በእጅጉ ያሳስባል።

የተደረጉ ጥናቶች ሁሉ እንደሚስማሙበት፣ እንደ የእፅዋት እድገት፣ የካርቦን ቅደም ተከተል፣ የአበባ ዱቄት፣ የዘር መበታተን እና አልሚ ንጥረ ነገሮችን መልሶ መጠቀም እና የመሳሰሉት የስነምህዳር ሂደቶች ለምግብ ደህንነት እና ለምግብነት አስፈላጊ በሆነው ብዝሃ-ሕይወት ላይ የተመረኮዙ ናቸው፡፡ ስለሆነም የደን ሥነ-ምህዳሮችን መጠበቅ እጅግ አስፈላጊና ለሰው ልጅ ሰው ሆኖ መቀጠል ወሳኝ እርምጃ ነው።

እንደ የአየር ንብረት ለውጥ እና ከባዮኢነርጂው ዘርፍ የእንጨት ፍላጎት መጨመር በመሳሰሉ ስነምህዳራዊ እና ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እድገቶች በርካታ ችግሮች እየገጠሙት ያለው የተፈጥሮ ሀብት (ደንና ሌሎችም) ኃላፊነት በጎደለው አጠቃቀም ምክንያት ብዝሃ ሕይወት እየቀነሰ ነው፡ ፡ በጫካዎች ላይ የሚደርሰውን ጫና መቀነስ፣ ሥነ-ምህዳሩን ወደ ነበረበት መመለስ እና ባዮሎጂካዊ ሀብቶችን በዘላቂነት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት እየደረሰ ያለው ከፍተኛ የእሳት ቃጠሎ፣ ተደጋጋሚና የተራዘመ ድርቅ፣ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ፣ እሱን ተከትሎ የሚመጣው ጎርፍ ወዘተ ሁሉ ምክንያትና መነሻቸው የዓለማችን የደን መራቆት ሲሆን፣ ከ1800ዎቹ ወዲህ ለመራቆቱ ዋናው ምክንያት የሰው ልጅ መሆኑ ተረጋግጧል። ዓለማችን በአንታርክቲክ አካባቢ ብቻ 1.75 ሚሊዮን ስኴር ኪሎ ሜትር የውቅያኖስ አካባኒ ግግር በረዶ አጥታለች፤ ይህ ከ1981-2010 ባለው ጊዜ ውስጥ ከተከሰተው በአማካኝ ያህሉን ሲሆን፤ ኃላፊነቱን መውሰድ ያለበት ሰው እንጂ ሌላ አይደለም።

የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ያለው ግጭት በዚሁ ተጠናክሮ የሚቀጥል ከሆነ በ2050 የዓለም የሙቀት መጠን 1.5 ዲግሪ ሴልሺየስ (2.7° ዲግሪ ፋራናይት)፤ በ2100 ደግሞ ከ2 – 4 ዲግሪ ሴልሺየስ (2.7° ዲግሪ ፋራናይት) ይደርሳል ተብሎ ተተንብዮአል (ተፈርቷል)። ይህ እንዳይሆን፣ ጦሱም ለፕላኔቶች ሁሉ እንዳይተርፍ ሰው ኃላፊነቱን ወስዶ ከወዲሁ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። ("ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ፤ አለበለዚያ . . . የሚለውም እዚህ ጋ ይሰራል።)

በ17ኛ ክፍለ ዘመን የ"ተግባራዊ እውቀት ፈልሳፊ፣ እንግሊዛዊው ፍራንሲስ ቤከን እንዳለው ከሆነ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ለተፈጥሮ ትርጉም የሚሰጠው ሰው ከተፈጥሮ በጣም ተለያይቷል። እናም በሕይወት ውስጥ በማንኛውም መንገድ መሳተፍን ማሰብ አይችልም። በሁለቱ መካከል ያለው ጤናማ መስተጋብር በጣም እየቀነሰ ነው። (እዚህ ላይ የ17ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርዓያቆብ ስለ ሰውና ተፈጥሮ በ"ህተታው ያለውን መመልከት ጉዳዩን ከፍ ከማደረጉም በላይ በጉዳዩ ላይ ኢትዮጵያ ለዓለሙ ያደረገችውን አስተዋፅኦ ለመረዳት እንደሚያግዝ ሳንናገር ብናልፍ ንፍገት ይሆናልና ስንጠቅሰው "በኩራት!!! ነው።)

በአቶሚ ላይ ሰፍሮ እንደሚነበበው "አካባቢያዊ ችግሮችን በተመለከተ ፈላስፋዎችና ፕሮፌሰሮች የመጨረሻውን ፍርድ ሰጥተዋል - አንድ ሰው ከተፈጥሮ ባህሪው (እና እራሱን፤ እንደዚሁም ለውጦቹን) ይቀይራል፤ ወይንም ደግሞ ከምድር ፊት ይጠፋል። (ለበለጠ መረጃ am.atomiyme.comን ይጎብኙ) ከሁለት ዓመት በፊት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እንዳለው ከሆነም የሰው ልጅ (በተለይም መሪዎች) ባስቸኳይ እናት ተፈጥሮ መልሳ ታገግም፤ ወደ ነበረችበትም ትመለስ ዘንድ ፈጣን እርምጃ መውሰድ ካልቻሉ የሰው ልጅ ወደ እማይቀለበስ ቀውስ ውስጥ ይገባል።

ሰው ሆይ ስማ

ስማ . . . ሲል ያዘመው ማን ነበር??

# ማህደረ ጤና

## "ከስጋ ደዌ በሽታ መዳን ይቻላል"

*ዶክተር ሽመልስ ንጉሴ*



**እየሩስ ተስፋዬ**

ስጋ ደዌ በሽታ በባክቴሪያ አማካኝነት የሚከሰት ነው፡፡ በሽታውን ቶሎ ካልታከሙት ከፍተኛ አካል ጉዳት የሚያስከትል ሲሆን፤ በተለይም ዓይን፣ እጅ እና እግር ላይ ጉዳት በማድረስ ለከፍተኛ የሥነ ልቦና ችግር የሚዳርግ ነው፡፡ ለዚህም ነው በበሽታው የታየዙ ሰዎች ከጤናቸው ባሻገር በሥነ ልቦና፣ በኢኮኖሚ እና በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ችግር ሲያጋጥማቸው የሚስተዋለው፡፡

በሽታው ለረዥም ዓመታት ከሰዎች ጋር የኖረ ሲሆን፤ የበሽታው ዋና መንስኤ ማይክሮ ባክቴሪየም ይባላል፡፡ ባክቴሪያው የተገኘው እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1873 አርማወር ሃንሰን በተባለ ሳይንቲስ ነበር፡፡ ከዛ በፊት የሥጋ ደዌ በሽታ ‹‹በዘር ይተላለፋል፤ የፈጣሪ ቁጣ ነው፤ እርግማን ነው።›› በማለት ከአምልኮ ጋር የማያያዝ ሁኔታ ነበር፡፡ እነዚህን ምክንያት በማድረግ በታማሚዎች ላይ ከፍተኛ መገለል ይደርስባቸው ነበር፡፡ እድሜ ለሳይንቲስቱ በባክቴሪያ አማካኝነት እንደሚተላለፍ አረጋግጦ ዛሬ ላይ ብዙዎች ታክመው ለመዳን በቅተዋል፡፡

በአለርት ኮምፐርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የቆዳ እና አባላዘር ስፔሻሊስት ሀኪም የሆኑት ዶክተር ሽመልስ ንጉሴ እንደሚሉት፤ በሽታው በጀርም እንደመተላለፉ መጠን በፍጥነት ካልታከሙት ወደ ሌሎች ሊተላለፍ ይችላል። ሌላው በበሽታው የተያዘ ሰው ህክምናውን ሳይከታተል ቀርቶ ለረዥም ዓመታ ከቆየ ሌሎች ሰዎች በዚህ በሽታ የመያዝ ዕድላቸው የሰፋ ነው። በተጨማሪም የተያዘው ሰው በሚያስነጥስበት እና በሚያስልበት ወቅት ከአፍ እና ከአንፍጫው የሚወጡ ፈሳሾች ይኖራሉ፡፡ እነዛ ፈሳሾች በአየር ቧንቧዎች አማካኝነት ወደ ጤነኛ ሰው ሰውነት ከገቡ በሽታው የመተላለፍ ዕድል አለው፡፡

ባክቴሪያው በጣም ደካማ የሚባል ሲሆን፤ ለምሳሌ አንድ መቶ ሰዎች ለባክቴሪያው ተጋላጭ ቢሆኑ እንኳን ከአምስት በላይ ሰዎች የመያዝ ዕድ እንደሌላቸው የሚያስረዱት ዶክተር ሽመልስ፤ ባክቴሪያው ወደ ሰውነታችን ቢገባ እንኳን በሽታን የመከላከል አቅማችን ጠንካራ ሆኖ ከተገኘ ባክቴሪያውን በመግደል በበሽታ የመያዙ ዕድላችን እንዲቀንስ ያደርገዋል ይላሉ፡፡

እንደ ዶክተር ሽመልስ ማብራሪያ በስጋ ደዌ በሽታ የተያዘ ሰው የተለያዩ ምልክቶች ሊታዩበት ይችላል። ቆዳን እና ነርቭን የሚያጠቃ እንደመሆኑም የእጅ ጣት ጫፍ እና የእግር መረገጫ አካባቢ፤ የመደንዘዝ፣ በደንብ ያለመሰማት፣ በድን የመሆን ስሜት፣ እንደ እሳት የማቃጠል (መለብለብ)፣ እንደ ኤሌክትሪክ ያለ ንዝረት ያሉ ስሜቶች ምልክቶቹ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በጣም የነርቭ ጉዳት ሲያጋጥም የእጅ እና የእግር አለመታዘዝ፣ ዓይን እንዳይጨፈን ማድረግ እና የዕይታ ችግር መኖር፤ እቃ ለማንሳት መቸገር፣ መድከም፣ መስነፍ እና ቁስለት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በተጨማሪም፣ እጅ እና እግርን የመውረር ስሜትን ያስተናግዳሉ፡፡

ቆዳ ላይ ነጣ ነጣ፣ ገርጣ ገርጣ ያሉ ምልክቶች ሊታይ እንደሚችል የሚገልጹት የቆዳ እና አባላዘር ስፔሻሊስቱ ዶክተር ሽመልስ፤ አፍንጫ፣ ፊት እና ጆሮ አካባቢ ህመም የሌላቸው ጉብታዎች እንዲሁም እጅ እና እግር የመጣመም (የመበላሸት) ነገር ሊስተዋልባቸው እንደሚችል ጨምረው ይናገራሉ፡፡

ለስጋ ደዌ በሽታ አጋላጭ ምክንያቶቹ የተለያዩ ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው እና በማንኛውም የዕድሜ ክልል ላይ ያለ ሰው በበሽታው ሊጠቃ ይችላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በአንድ ቤት ለረዥም ጊዜ ተፋፍጎ አብሮ መኖር (Overcrowding) ከአጋላጭ ምክንያቶች መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡ የሰውነት በሽታን የመከላከል አቅም ከፍተኛ ከሆነ በበሽታ ላይያዝ ይችላል፡፡ በተቃራኒው ሰውነት በሽታን የመከላከል አቅም አነስተኛ ከሆነ ለበሽታው የመጋለጥ ዕድል እንደሚኖር እየተሠሩ ያሉ ጥናቶች መኖራቸውን በመጥቀስ ዶክተር ሽመልስ ያስረዳሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ከንጽህና ጉድለት ጋር በተያያዘ የግል እና የአካባቢን ንፅህና አለመጠበቅ፣ የተበከለ ውሃ እና ምግብ መጠቀም ለበሽታ ሊያጋልጡ እንደሚችል ይገለፃል፡፡ ይህም ለስጋ ደዌ በሽታ ብቻ ሳይሆን ለሌላ በሽታ እንደሚያጋልጥ ዶክተር ሽመልስ ያስረዳሉ። ስለዚህም እጅን በውሃ እና በሳሙና በመታጠብ፣ የግል ንጽህናን እንዲሁም የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ፣ ንጽህናው የተጠበቀ ውሃ እና ምግብ በመጠቀም ሰውነታችን በሽታ የመከላከል አቅም እንዲኖረው ማድረግ ይገባል፡፡ በዋነኛነት ግን በበሽታው ለረዥም ጊዜ ተይዞ ካልታከመ ሰው ጋር በጋራ መኖር አጋላጭ ምክንያት እንደሆነ በመጥቀስ፤ ስጋ ደዌ በሀገራችን የተወሰኑ ቦታዎች ላይ ተሰራጭቶ ይገኛል፡፡ ሁሉም አካባቢ ላይ ሊኖር እንደሚችል ቢጠበቅም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ብቻ የመገኘቱ ነገር ላይም ‹‹ለምን ይሆን?›› ተብሎ ጥናቶች እየተካሄዱ እንደሆነ ዶክተር ሽመልስ ይናገራሉ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከስጋ ደዌ በሽታ ጋር በተያያዘ አዳዲስ ኬዞች እየተመዘገቡ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም ምክንያት በበሽታው የተያዙ ሰዎች ወደ ጤና ተቋም በፍጥነት አለመሄዳቸው እንደሆነ በተደጋጋሚ ይነሳል፡፡ ስለዚህም ብዙዎች በበሽታው ተጠቅተው ከፍተኛ አካል ጉዳት ከደረሰባቸው በኋላ ወደ ህክምና ተቋማት መምጣታቸው እና በቂ ግንዛቤ አለመኖሩ አዳዲስ ኬዞች እንዲመዘገቡ አድርጓል፡፡

የዓለም የጤና ድርጅት በስጋ ደዌ የሚያዙ ሕፃናት ከአምስት በመቶ መብለጥ እንደሌለበት ይመክራል። የእኛን ሀገር የተመለከትን እንደሆነ ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ 10 በመቶ ሕፃናት በስጋ ደዌ በሽታ እንደተያዙ መረጃዎች እንደሚያመላክቱ ዶክተር ሽመልስ ያስረዳሉ። ሕፃናቱ ከቦታ ቦታ (ከሚኖሩበት መንደር) የመንቀሳቀሳቸው ነገር አናሳ እንደመሆኑ መጠን እነርሱ በሚኖሩበት አካባቢ በስጋ ደዌ የተያዙ ሰዎች ቁጥር ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል አመላካች በመሆኑ ብዙ ሥራ እንድንሠራ ያደርገናል ይላሉ፡፡

ዶክተር ሽመልስ እንዳሉት ከሆነም፤ የስጋ ደዌ በሽታ ሕፃናት ላይ ተመሳሳይ ምልክት ያሳይ እንጂ እነርሱ የበሽታውን ምልክት ለመግለጽ ይቸገራሉ።በዚህ መሠረት ምልክቶቹ በሚገባ ሲታዩ በሽታው የሚታወቅላቸው ሲሆን፤ መለስተኛ ደረጃ ላይ እያሉ ወደ ህክምና የማምጣቱ ነገር አናሳ መሆን እና ከላይ የተገለጸው ምክንያት በስጋ ደዌ የታያዙ ሕፃናት ቁጥር ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ከስጋ ደዌ ጋር በተያያዘ ላለፉት 10 ዓመታት በየዓመቱ በአማካይ ሦስት ሺህ አዳዲስ ኬዞች ይመዘገባሉ። ከአጠቃላይ የህዝቡ ቁጥር ከተነሳን ግን በሽታውን ተቆጣጥረነዋል ያሉት ዶክተሩ፤ የተያዘውም ሰው ቁጥር ትንሽ ነው ሊባል ይችላል፡፡ የዓለም የጤና ደርጅት መስፈርት መሠረት ብናደርግ የኢትዮጵያ ወደ 0 ነጥብ 2 ሲሆን፣ ከአንድ በመቶ በታች መሆኑ ጥሩ የሚባል ነው፡፡ እንደ ሀገር ትልቅ ለውጥ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን አሁን አሳሳቢ እየሆነ የመጣው የሚታዩት አዳዲስ ኬዞች በመሆናቸው ብዙ መሥራትን ይጠይቃል ባይ ናቸው፡፡

እንደ ዶክተር ሽመልሽ ገለፃ፣ በየዓመቱ ከአንድ ሺህ በላይ አዳዲስ ኬዞች ከሚመዘገብባቸው 13 ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት፡፡ ከአፍሪካ ደግሞ አምስት ሀገራት ሲሆኑ ናይጄሪያ፣ ኢትዮጵያ፣ ማዳጋስካር፣ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ እና ሞዛምቢክ ናቸው፡፡ የዓለም የጤና ድርጅት እ.አ.አ በ2030 የስጋ ደዌ ስርጭትን ዜሮ የማድረስ እቅድ አለው፡፡ ይህንን ለማሳካት ግን እንደ ሀገር ብዙ መሥራትን ይጠይቃል የሚለት ዶክተር ሽመልስ፣ ግቡን ለማሳካት አዳዲስ ኬዞች ሲያጋጥሙ እና ስርጭቱ እንዳይስፋፋ ለማድረግ ቶሎ ቶሎ ማከም፣ ታካሚዎችን መለየት፣ ህክምናውን በአግባቡ እንዲወስዱ ማድረግ እና ኅብረተሰቡን ማስተማር ይገባል፡፡

ህክምናውን በተመለከተ ዶክተር ሽመልስ እንደሰጡት ማብራሪያ፤ በስጋ ደዌ ለሚታመሙ ሰዎች በሁሉም የጤና ተቋም ህክምናው በነፃ ይሰጣል፡፡ ለታካሚዎች የነርቭ እንዲሁም የላቦራቶሪ ምርመራ ተደርጎላቸው ‹‹ባክቴሪያው መጠኑ ምን ያህል ነው?›› ለሚለው ናሙና በመውሰድ ያለበት ደረጃ ይለያል። በዚህም መሠረት የባክቴያው ቁጥር አናሳ ከሆነ መድኃኒቶችን እስከ ስድስት ወር እንዲወስዱ ይደረጋል። የባክቴሪያው መጠን ከፍተኛ ከሆነ እና የበሽታው ደረጃ ከፍ ያለ ከሆነ ግን መድኃኒቶችን ለአንድ ዓመት እንዲወስዱ ይደረጋል።

በሽታው የሚድን ሲሆን ባክቴሪያውም ቀላል የሚባል አይነት ነው፡፡ በአብዛኛው ጊዜ የበሽታው ደረጃ ከፍ የሚያደርገው ቶሎ የመገኘቱ እና ያለመገኘቱ ነገር እንደሆነ በተደጋጋሚ አጽንኦት ሰጥጠው የሚናገሩት ዶክተር ሽመልስ፣ ስጋ ደዌ የሚድን በሽታ በመሆኑ በተለያዩ ወረዳዎች ላይ የጤና ባለሙያዎች ግንዛቤ አናሳ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ስልጠና መስጠት ይገባል። ኅብረተሰቡም በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ መሥራት ያስፈልጋል በማለት ያስረዳሉ፡፡

ስጋ ደዌን ለመከላከል ክትባት የለውም። ማንኛውም ሰው ቆዳው አካባቢ የመቆጣት፣ የመደንዘዝ እና የተለየ ምልክት ካየ በአፋጣኝ ወደ ህክምና ተቋም በማምራት ራሱን እንደሁም ሌሎችን ሰዎች ከአካል ጉዳተኛነት፤ እንዲሁም ከስነ ልቦናዊ ችግር መከላከል እንደሚኖርበት ያሳስባሉ፡፡

በቀጣይም ስጋ ደዌን አስቀድሞ ለመከላከል እየተሠራ ሲሆን፤ በሽታው ያለበት ሰው በጉርብትና፣ አብሮት የሚኖረው ሰው እና በአካባቢው ያሉትን ሰዎች ተጋላጭ እንዳይሆኑ አንድ እንክብል በመውሰድ ለመከላከል ጅምር ሥራዎች አሉ፡፡ በዚህም እስከ ሦስት ዓመት ድረስ በበሽታ እንዳይያዙ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህን በሀገራችን ተግባራዊ ለማድረግ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ዶክተር ሽመልስ ይጠቁማሉ። በአጠቃላይ ስጋ ደዌን ለማጥፋት በዚህ ዙሪያ ከሚሠሩ መንግሥታዊ ከሆኑ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በቂ በጀት በመበጀት፣ በትብብር እና በድጋፍ፤ እንዲሁም ማኅበረሰቡን በማንቃት በሰፊው መሥራትን ይጠይቃል፡፡

# ተናጋሪው ዶሴ

# በማቀፍ ፋንታ ማነቅ

**አስመረት ብስራት**



እናት ማለት የልብ ትርታ ናት፡፡ እናት እኮ የመልኳ ውበት፤ የቤቷ ባለጠግነት፤ የሰውነቷ ሙቀት የተሳሰረ የፍቅር በር ነው፡፡ እናትነት በዘመን የማይጠወልግ፤ በጊዜ የማያረጅ በወራት የማይደበዝዝ ዘላለም አብሮ የሚኖር የሰውነት ምሳሌ ነው፡፡

አንዲት እናት በእቅፏ ያለውን ሕፃን ስታጠባ በዓይነ ሕሊናችሁ እዩት። ይህ ሁኔታ እናት ለልጇ ርኅራኄና ፍቅር ከምታሳይባቸው መንገዶች አንዱ ነው። በቁም ነገሩ በብዙዎች ዘንድ የሚታወቅ ሐቅ ቢሆንም እንኳን የእናት ፍቅር በልጇ እድገት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ጥናቶች አረጋግጠዋል።

በዓለም የጤና ድርጅት የአእምሮ ጤና እንክብካቤ ዘርፍ የተዘጋጀ አንድ ጽሑፍ እንዲህ ይላል። “ከእናታቸው ተለይተው ያደጉ ሕፃናት ደስታ የራቃቸውና በጭንቀት የተዋጡ እንደሚሆኑ፣ አንዳንዴም ከፍተኛ የፍርሃት ስሜት እንደሚያድርባቸው ጥናቶች ያሳያሉ።” ይኸው ጽሑፍ አንድን ጥናት ጠቅሶ እንደተናገረው፣ ከልጅነታቸው አንስቶ ፍቅርና ትኩረት ያገኙ ልጆች ችላ ከተባሉት ይልቅ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ አላቸው።

ታዲያ እድሜ ረዝሞ እርጅና ከነግሳንግሱ የመጣ እለትም ቢሆን የእናት መልካም ውለታዋ እየታወሰ ሕይወቷ እስከቆየ ደረስ ብቻ እስትንፋሷ ይኑርልኝ እየተባለ እናትን ጨካኙ ሞት እስኪወስዳት ደረስ መንከባከብ ደግሞ የልጅ ግዴታ ሆኖ ይቀመጣል። የእናትነትን ውለታ ለመመለስ ዳግም እናትን አምጦ መውለድ ካልተቻለ ከባድ መሆኑን ወልደው ያዩቱ የእናትና ልጅ የትስስር ገመዱን ጥብቀት የተረዱቱ አስረግጠው ይናገሩታል።

ለዛሬ በተናጋሪው ዶሴ አምድ ይዘንላችሁ የቀረብነው ታሪክ ግን እውነት የእናትና ልጅ ፍቅር በዚህ ልክ ወርዶ ልጅ እናቱን ለማጥፋት የሚያስችል ደረጃ ይደርስ ይሆን የሚያስብል ጥያቄን ያጭራል። ታሪኩ እንዲህ ነው.....

አዲስ አስራት ይመር እና የ78 ዓመት ወላጅ እናቱን አብረው ነበር የሚኖሩት። የአዲስ እናት እድሜ ዘመናቸውን በሙሉ ለአንዱ ልጃቸው ሕይወታቸውን መክፈል እስኪቀራቸው ድረስ መደረግ የሚገባውን በሙሉ አድርገው ነው ያሳደጉት።

ከአፋቸው ነጥለው እያጎረሱት፤ እሳቸው ታርዘው እሱን እያለበሱት ድሃ እናት መሆን የሚገባትን መልካም ነገር በሙሉ እያደረጉለት ኖረዋል። አዲስም ልፋታቸውን ሜዳ ላይ ሳያስቀር ተምሮ ትልቅ ደረጃ ደርሶላቸዋል።

መጀመሪያ አካባቢ የእናቱን ውለታ ለመመለስ የሚታትር ጠንከራ ሰራተኛ ሆነ። ሰርቶ ያገኘውን እናቱን ለማስደሰት ያውለው ነበር። እየቸገራቸው ሳይሸጡት ያቆዩት ቀድሞ በነበራቸው ቤት ላይ እቁብ እየጣለ አዳዲስ ተጨማሪ ክፍሎች ሰራ። ችግሮች አልቀው ገንዘብ ተገኘ። ድህነት አልፎ ወደ ሀብት መንገድ ለመጀመር የመጀመሪያዎቹን እርምጃዎች መራመድ ጀመረ።

ድህነት አልፎ ለውጥ ሲመጣ ጥሩ መብላት፤ ጥሩ መልበስ ሲጀመር አዲስ ብዙ ጓደኞችን አፈራ። ለእናቱ የሚሰጠውን ጊዜ ትቶ ማምሸት እና መጠጣት መገለጫው ሆነ። እናቱ እድሜ እየተጫናቸው ሕመም እየተደራረበባቸው ቢመጣም እሱ ግን ወደ ቤቱ መልስ የማለቱን ነገር ተወው።

ሕመምና መከፋት ብሎም እድሜ ተጨምሮ ቤት ያዋላቸው እናት ድካም በድካም ላይ ተደራርቦ እግር እጃቸው የማይንቀሳቀስ በሰው ድጋፍ ወዲያ ወዲህ የሚሉ ሆኑ። አብስለው አፅድተው የሚጠብቁት እናቱ ጭራሽ የእሱን ድጋፍ ሲፈልጉ መሰልቸት ጀመረ።

## አዲስና አዲሷ ፍቅረኛው

በሕይወቷ ውድቀት ውስጥ ያልኖረች እንዴት መኖር እንዳለባት የማታውቅ ናት ይላታል አዲስ አዲሷን ፍቅረኛውን። ፍቅረኛው ለማንም ግድ የሌላት እሷ የምታድግበት ከመሰላት ማንንም ጥላ ብታልፍ ቅር የማይላት ሴት ናት። ነፍሷ በንቀት የተሞላች ማንም ለመዘርጠጥም ለማድነቅም ቅድመ ሁኔታን የማትጠብቅ ወጣ ያለች ሴት ናት።

ራስዋን ለፈለገችው ነገር በሙሉ መስዋት አድርጋ ለማቅረብ ከማግኘት በላይ ምክንያት ማግኘት የማትፈልግ ለምድሪቱ መስዋዕትነትን ከፍለው ምድራዊ ታላቅነትን ማምጣት ሕልሟ የሆነች ናት።

አዲሷ የአዲስ ፍቅረኛ አዲስን በማድነቅ ነበር ሴራዋን ሁሉ የጀመረችው፡፡ ለማወቅ የሚኖርን ሰው እወዳለሁ ትላለች የአዲስን ለትምህርትና አዲስ ነገር ለማግኘትና የማወቅ ፍላጎቱን ስታደንቅ። በምድር ላይ ታላቅ ሰው የመሆን ምክንያት እውቀት ነው ትላለች። ምንም እንኳን በዚያ ሂደት የራሱን ውድቀት እንደሚያፋጥን ባያውቅም እውቀትን የሚፈልጋት እሱ ታላቅ ሰው ነው በማለት ለሁሉም ነገር ፍጥነቱንና ድፍረትን እንዲታጠቅ ታደርገዋለች።

በስራው የሚተጋና የሚፈጥን ሰው እወዳለሁ ምንም እንኳን ከስራው ለራሱ ትርፍ ባያገኝም ለሌላው ሰው ከብትና እርሻውን ያበዛለታልና በማለት ዘወትር ታወድሰዋለች፡፡ በሂደትም ከአድናቆቷ ጎን ለጎን የእሷን ጥሪት ከፍ ለማድረግ መሰናክል ናቸው ብላ ያሰበችውን የአዲስን እናት እንዲጠላ ማድረግ ጀመረች።

ለራሷ ስህተት ከሚመስላት ነገሮች መራቅን ምርጫዋ በማድረግ ሰውን ወደ ስህተት መንገድ ለመገፍተር የማትራራ ነበረች ″መልካም ስምና ዝናውን የሚጠብቅ እወዳለሁ፤ ምንም እንኳን በስሙ ውድቀቱን ቢያፋጥንም ለስሙ ሲል መኖር፣ ለስሙም ሲል መሞት ያውቅበታል″ እኔም እንደዛው ነኝ ትላለች።

″ ቤቱ ቢሸጥና ሌላ ቦታ የተሻለ ቤት ብንገዛ.... ″ ትላለች። ትንሽ ቆይታ ደግሞ የምንጋባው በስማችን አንድ ነገር ሲኖር ነው ″ ትላለች። ብቻ ሴት የላከው ሞት አይፈራም ይሉት ነገር እንዲደርስብት ከስር ከስር በአማሩ ቃላት እየለወሰች እናቱን ከሕይወቱ እንዲያወጣ ትወተውተው ገባች።

እንደዛ ለአይኑ የማያምናቸውን እናቱን ጠላ። ቁጭ ብላ ከነገራቸው እናቱ ጋደም ብላ የነገረችው ሚስቱ ሆኖበት የሚስቱን ቃል ሰምቶ የእናቱን ሞት መመኘት ጀመረ። ማመናጨቅና ማጥላላት የዘወትር ተግባሩ ሆነ። ቤት በገባ ቁጥር በእርጅና የተዳከሙትን እናቱን ከመንከባከብ ይልቅ በየእለቱ መራገምና መሳደብ ስራው ሆነ።

ወዳጅ ጎረቤት እስኪታዘበው ድረስ ያ ትሁት የእናቱን ስም አንስቶ የማይጠግበው ልጅ እናቱን ሰዳቢና አመናጫቂ መሆኑ ሰውን ሁሉ ከንክኖታል። በዚህም የተነሳ ጎረቤት ወዳጅ ዘመዱ ልጁን በአይነ ቁራኛ መከታተል ጀመሩ።

## ስባስውስታ የተከፈለው ቅጣት

የመጀመሪያዋ መጋቢ እናት። የመጀመሪያዋ ዶክተር የመጀመሪያዋ መምህርት እናት። ሊያውም በችግር ተቆራምዳ ለራሷ ሳትኖር ለወግ ማዕረግ ያበቃችንን የባለውለታ ጥግ ውለታዋ ተከፍሎ የማያልቀውን ደግ ሴት በልጇ ክፉ ምላሽ ተመለሰላት። መኖር ጠልታ ሞቷን እየናፈቀች ያለችን እናት አበርትቶ ፈጣሪ እስኪወስዳት መንከባከብ ቀርቶበት ልጇ በገዛ እጁ ይሸኛታል ብሎ ማን ያስባል።

የልጁ ሙሉ ስም አዲስ አስራት ይባላል። በጥር 16 ቀን 2015 ዓ.ም ነበር። እንደ ልቡ እናቱ መሆናቸውን የሚነግረው አዲስ ስራ ከመውጣቱ በፊት ሊመግባቸው ከተኙበት አንስቶ በእቅፍ ሶፋ ላይ የመጣና ያስቀምጣቸዋል። ከሌሊቱ በግምት 11፡00 አካባቢ ስለነበር እናትየው በእንቅልፍና በመንቃት ላይ እንዳሉ ሶፋ ላይ የተቀመጡት እናት በእንቅልፍ ልባቸው መወዛወዝ ጀመሩ። በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ደብረ ሰላም ትምህርት ቤት አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ሆነው ከእንቅልፍ ጋር የሚታገሉት የ78 ዓመት አዛውንት እንቅልፉ አሸንፏቸው መሬት ላይ ጥቅልል ብለው ይወድቃሉ።

አዲስም ወላጅ እናቱን ካስቀመጣቸው ሶፋ መሬት ላይ ወድቀው ሲያገኛቸው እጅግ በጣም ተናደደ ቁጣውን መቆጣጠር ያቃተው ይህ ልጅ በገዛ እጁ አንገታቸውን አንቆ በመያዝ ሕይወታቸው እንዲያልፍ ያደርጋል።

ወትሮም ንጭንጩ ግራ የገባቸው ዘመዶች ልጁን በአይነ ቁረኛ ይከታተሉት ስለነበር ድርጊቱን ፈፅሞ ለመሸፋፈን ሲሯሯጥ በቦታው ደረሱ። ያደረገውን አድርጎ ከመሰወሩ በፊትም በአቅራቢያው ያገኙትን ፖሊስ ይዘው በመምጣት በቁጥጥር ስር እንዲውል አደረጉት።

አፈቀርኳት ያላት ሴት የነገረችው በመስማት እናቱን ጠላ። የእናቱ ጥላቻም አድጎ በገዛ እጁ እናቱን እስከመግደል ደረሰ።

## የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስም ቦታው ላይ እንደደረሰ ልጁን በቁጥጥር ስር አውሎ ሲጠይቅ እናቱ ወድቀው መሞታቸውን ሊያነሳቸው ሲሞክርም ሕይወታቸው አልፎ እንደነበረ አስረዳ። ፖሊስ የልጁን ቃል ማመን ስለተሳነው አስክሬኑን ወደ ሆስፒታል በመላክ ምርመራ ሲያስደርግ በመታነቅ ሕይወታቸው ማለፉን በፎረንሲክ ምርመራ ይደረስበታል።

ያንን የተረዳው ፖሊስ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር አውሎ የአዛውንቷ ስርዓት ቀብር እንዲፈፀም አስከሬኑን ለወዳጅ ዘመድ እንዲመለስ ያደርጋል።

ሴት የላከው ሞት አይፈራም ሆኖበት ሲጠየቅም ያለ ምንም ፀፀት መልስ ይሰጥ ነበር፡፡ ያደረገውን በሙሉ በተግባር በማሳየት የእምነት ክህደት ቃሉን ይሰጣል። የምርመራ ውጤቱንና የእምነት ክህደት ቃሉን የያዘው ፖሊስ መረጃውን አጠናቅሮ ለአቃቤ ሕግ ላከ።

## የአቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር

የአቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር እንደሚያስረዳው አዲስ አስራት ይመር የተባለ ተከሳሽ ጥር 16 ቀን 2015 ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት 11፡00 ሲሆን በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ደብረ ሰላም ትምህርት ቤት አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ዕድሜአቸው 78 ዓመት የሆናቸውን ወላጅ እናቱን ካስቀመጣቸው ሶፋ መሬት ላይ ወድቀው ሲያገኛቸው በእጁ አንገታቸውን አንቆ በመያዝ ሕይወታቸው እንዲያልፍ በማድረጉ ምክንያት በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ ተጣርቶ በሴቶችና ሕጻናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በወ/ሕ/አ 540 መሰረት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት ክስ ቀርቦበት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በክርክሩ ሂደትም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ የመከላከያ ምስክሮች ማስረጃነት አቅርቦ ያሰማ ቢሆንም በዐቃቤ ሕግ የቀረበለትን ክስ መከላከል አልቻለም።

## ውሳኔ

**በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት በተከሳሽ ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ ስመስጠት በዋለው ችሎት ተከሳሽ በ10 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡**

# ርዕሰ አንቀፅ

## መንግስት ለፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ትግበራ ያሳየው ቁርጠኝነት የሚመሰገን ነው!

የሰላም እጦት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ሀገራችንን እንደ ሀገር እየተፈታተነ ያለ ትልቅ ተግዳሮት ነው። የለውጡ እሳቤና ተጨባጭ አካሄድ ያልተመቻቸው የውጪና የውስጥ ኃይሎች በተናጠልና በተቀናጀ መንገድ የለውጡን ጉዞ ለማደናቀፍ በስፋት ተንቀሳቅሰዋል። በዚህም የተፈጠረው የሰላም እጦት የመላውን ሕዝባችንን የዕለት ተዕለት ሕይወት እየተፈታተነ ይገኛል።

በተለይም በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ሕወሓት ብዙ የሰላም አማራጫችን ረግጦ በቀሰቀሰው ግጭት ሀገርን ለሁለንተናዊ ቀውስ መዳረጉ የሚታወስ ነው። በዚህም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ለሞትና ለአካል ጉዳት፤ በቢሊየን የሚቆጠርም የሀገር ሀብት ለውድመት ተዳርጓል። የችግሩ ሰብአዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጠባሳም ዛሬም ሀገርን ብዙ ዋጋ እያስከፈለ ነው።

መንግስት ግጭቱ በሰላማዊ መንገድ ይፈታ ዘንድ ይዞት የነበረውን የቀደመ የጸና አቋም ታሳቢ በማድረግ፣ "ለአፍሪካዊ ችግር በአፍሪካዊ መፍትሄ " በሚል ከወዳጅ ሀገራትና ከአፍሪካ ሕብረት ጋር በመሆን በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ግጭቱ በሰላማዊ መንገድ በስምምነት እንዲቋጭ ትልቁን ኃላፊነት ወስዶ ተንቀሳቅሷል።

ብዙ ሰላምን የሚፈታተኑ ተግዳሮቶችን በቋርጠኝነት በመሻገር፤ ግጭቱ በሰላም ስምምነት መፍትሄ እንዲያገኝ ረጅም ርቀቶችን ተጉዟል። በዚህም በአካባቢው የሰላም አየር እንዲነፍስ አድርጓል። ለሰላም ያለውን የጸና አቋም በድጋሚ ለመላው ሕዝባችንና ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በተጨባጭ ማሳየት ችሏል።

በስምምነቱ የተገኘውን ሰላም ዘላቂ በማድረግ፤ በግጭቱ ምክንያት መልከ ብዙ ችግሮች ውስጥ የሚገኙ ዜጎቻችንን ሕይወት ለመታደግ እና ወደቀደመው የተረጋጋ ሕይወታቸው እንዲመለሱ፤ የተገኘውን ሰላም የሚገዳደሩ ፈተናዎችን በሆደ ሰፊነት ለመሻገር ረጅም ርቀት ተጉዟል፤ ለዚህም ብዙ ዋጋ ከፍሏል።

በተለይም የትግራይ ሕዝብ፤ ጦርነቱ ከፈጠረው የስነልቦና ስብራት እንዲያገግም፤ በእለት ተእለት ሕይወቱ ላይ የተደቀነውን የከፋ አደጋ ለመቀልበስ፤ የሀገሪቱ አሁነኛ አቅም ሊፈቅድ የማይችለውን ከፍተኛ ሀብት በመመደብ ለሕዝቡ ያለውን አጋርነት አሳይቷል። ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትን ወደ አካባቢው በመላክ አጋርነቱን አሳይቷል፡፡

ሕዝቡ የባንክ፣ የቴሌኮም፣ የመንገድ፣ የጤና፣ የትምህርትና ..ወዘተ መሰረታዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ሰፊ ጥረቶችን በማድረግም፤ የፕሪቶርያ ስምምነት በተፈረመ በሳምንታት ጊዜ ውስጥ በጀትና ባለሞያዎችን በመመደብ በክልሉ መሠረታዊ አገልግሎቶች እንዲጀመሩ አድርገዋል፡፡

በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል የክልሉን የዘርፍ መሥሪያ ቤት ለማጠናከር ከተወሰዱ ርምጃዎች ባሻገር ለካፒታል በጀት 4.9 ቢልዮን ብር፤ ለመደበኛ በጀት 11.4 ቢልዮን ብር፣ እንዲሁም ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ 400 ሚልዮን ብር፤ በድምሩ 16.7 ቢሊዮን ብር በ2015/16 ለክልሉ ሰጥቷል፡፡ በክልሉ ለሚገኙ አራት ዩኒቨርሲቲዎች 5.1 ቢልዮን ብር ሰጥቷል፡፡ በልማት አጋሮች በኩል የ1.7 ቢሊዮን ብር ድጋፍ ለትግራይ ክልል እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ በቻናል አንድ 1.7 ቢሊዮን እንዲሁም የገንዘብ ሚኒስቴር በክልሉ ባቋቋመው ጽ/ቤት በኩል፣ በትግራይ ለሚከናወኑ የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች እና ለአየር ንብረት ለውጥ ፕሮጀክቶች በድምሩ ከ565 ሚልዮን ዶላር በላይ ፈሰስ ተደርጓል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ ፕሮጀክትም 65 ሚሊዮን ብር ለክልሉ ተላልፏል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እና የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በክልሉ የሚገኙ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶችንና ተቋማትን ለማብቃት ሥልጠና ሰጥተዋል፤ ቁሳቁስ አሟልተዋል፤ የገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጾታን መሠረት ላደረጉ ጥቃቶች የምላሽ አገልግሎት የሚውል ከ7 ሚልዮን ዶላር በላይ ለክልሉ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

በጦርነቱ የተጎዱ ድልድዮችን በጊዜያዊነት ለመጠገን እንዲቻል ሁለት ተገጣጣሚ ድልድዮች የተለገሱ ሲሆን አራት ድልድዮችን ለመገንባት ጨረታ ወጥቷል፡፡ በጦርነቱ ወቅት የተቋረጡ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችንም በልዩ ፕሮግራም የክልሉ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ለዘጠኝ ከተሞች የፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚውል ከ409 ሚሊዮን ብር በላይ እና ከ7 ሚሊዮን ዶላር በላይ ለክልሉ ተላልፏል፡፡

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደርም ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ እና ለመንገድ ፕሮጀክት ጥገና ከ418.6 ሚልዮን ብር በላይ ወደ ክልሉ ልኳል፡፡ ለትግራይ ገጠር መንገድ ጥገና ከመንገድ ፈንድ ከብር 107 ሚልዮን ብር በላይ፤ የ2026 በጀት ቅድመ ክፍያ ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ ተልኳል፡፡ በፕላንና ልማት ኮሚሽን በኩል ደግሞ በጠቅላላው የ4.2 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ድጋፉ ከሁሉም በላይ የትግራይ ሕዝብ ወደቀደመ ሰላማዊ ሕይወቱ እንዲመለስ በመንግስት በኩል ያለውን እና የነበረውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው። ለፕሪቶሪያው ስምምነት ተፈጻሚነት፣ ምን ያህል ከስምምነቱ በላይ ምን ያህል ረጅም ርቀት እየተጓዘ እንዳለ በተጨባጭ የሚያመላክት ነው።

በዚህ ደረጃ ከፍ ባለ ሕዝባዊና ሀገራዊ ኃላፊነት እየተንቀሳቀሰ ያለው የፌደራል መንግስት፤ በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት አንዲተገበር የነበረው ዝግጁነትና ያሳየው አፈጻጸም በማንኛውም ሚዛን ቢለካ እውቅና ሊሰጠው የሚገባና የሚያስመሰግነው ነው!።


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ስለ ሠላም ሲባል ...

በምስጋና

ሠላም የማይነካው ጉዳይ የለም፡፡ የሠላም በር እየተዘጋ፤ የግጭት፣ የጦርነት፣ ተስፋ የማጣት እና የመሳሰሉት ችግሮች እየገዘፉ መምጣት እንደ ተራ የምናያቸው ነገሮች ቅንጦት እንዲሆኑብን ያደርጋል። ቢያንስ በአንድ ቀን ሁለት ጊዜ መመገብ ቀርቶ የዕለት ጉርስን ያስናፍቃል፡፡ ጥጋብ ቀርቶ መቅመስን ብቻ ያስመኛል፡፡ ውሃ ጠጥቶ ከመርካት ይልቅ ጠብታው አፍን መንካት እጅጉን ያስናፍቃል፡፡ አገርን ለቆ ወደ ማያውቁት አገር ያስናፍቃል፣ ያስኮበልላል፤ ያሰድዳል፡፡

በጦርነት፣ በጸጥታ መደፍረስ፣ በተፈጥሮ እና በሠው ሠራሽ ችግሮች ጉዳት ከሚደርስባቸው መካከል እናቶች ሴቶች ሕፃናት አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ለእነርሱም ሆነ ለመላው ሕዝብ ሠላም ልክ እንደ ‹‹አየር›› ነው። ያለ ሠላም መኖር አይቻልም፡፡ መኖር እንኳን ቢቻል ኑሮ አይባልም፡፡

ያለ ሠላም ምንም ማድረግ አይቻልምና ሁሉም ነገር ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ይሆናል፡፡ የተራቡትን፣ የታረዙትን፣ የተቸገሩትን ለመርዳት እንኳን የአገር ሠላም መሆን ግድ እና ግድ ነው፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀር አይደለም የሌላውን ጉድለት ለመሞላት ይቅር እና ለራስ መሆንም ብርቅ ይሆናል፡፡

ሠላም ሲደፈርሱ ሁሉም ነገር እንዳልሆነ ይሆናል፡፡ የትምህርቱ ዘርፍ ላይ የሚጥለው አሻራ ቀላል አይደለም። ከታችኛው የቅድመ አንደኛ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በራቸው እንዲዘጋ ያስገድዳል። በዚህም መጪው ትውልድ ከትምህርት፣ ከስልጣኔ፣ ከቴክኖሎጂ፣ ከእውቀት፣ ከአምራችነት፣ ከሥራ ፈጣሪነት እና ከመሳሰሉት ነገሮች ተጠቃሚ እንዳይሆን ያግዱታል፡፡

የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች መማር ሲኖርባቸው ከትምህርታቸው ሳይወድ እና ሳይፈልጉ ገሸሽ እንዲሉ ያደርጋቸዋል፡፡ እንደ እኩያዎቻቸው እውቀት ለመገብየትም ሆነ እገረ መንገዳቸውን ተጫውተው ለመግባትም የሠላም አስፈላጊነትን ማስረዳት ለቀባሪው እንደማስረዳት ያለ ነው ፡፡

ንግዱም፣ ግብይቱም፣ ቁጭ ብሎ ማውጋቱ፣ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለብዙ ዓላማ መዘዋወር የሚቻለው ሠላም ሲኖር እና ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ለደስታም ይሁን ሀዘንን ለመጋራት የሚደረጉ ጎዞዎች መጨረሻቸው የሰመረ እንዲሆን የሰላም ዋጋው እጅግ እልፍ ነው ፡፡

ይሁንና ዛሬም ቢሆን ተስፋ የሚሰጡ ነገሮች አልጠፉንም፡፡ በመንግስት እና በትግራይ ክልል በተደረሰው የሰላም ስምምነት ውጤቱን እያየነው እንገኛለን፡፡ በዚህም ምክንያት ዛሬ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች የእለት ጉርሱን የማግኘት እና ሌሎች መሠረተ ልማቶች ይሻሻሉልን እንጂ ሠላም አስፍኑልን ከሚለው አጀንዳ ከፍ ብሎ ታይቷል፡፡

ዛሬ ላይ መንግስታዊም ይሁኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ወደ ክልሉ በማቅናት የተለያዩ ሥራዎችን እየሠሩ ከመሆን ባሻገር ብዙ ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት የመጣው የሠላም ተስፋ ቦግ ብሎ በመታየቱ ነው፡፡

ከሰሞኑ የብልጽግና ፓርቲ ባደረገው ስብሰባ ላይ እንዳስታወቀው፤ የተሟላ ሀገራዊ ሰላም ለማስፈን እንዲቻል ከታጣቂ ቡድኖች ጋር የተጀመሩ ሰላማዊ አማራጮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ ይህም የሚበረታታ እና ብዙ ሊሠራበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

በሰላማዊ የፖለቲካ መንገድ ጥያቄዎቻቸውን ለሚያቀርቡ አካላት ሰላማዊ መንገዶች እስከሚቻለው ድረስ እንዲመቻቹ፤ በፕሪቶርያው ስምምነት የተገኙ የሰላም ፍሬዎችን በመንከባከብ፣ የጎደሉ ክፍተቶችን በመሙላት፣ ወደ ዘላቂ ሰላም እንዲሸጋገር ፓርቲው የተጀመሩ ጥረቶችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ማሳወቁም የሚደነቅ ነው።

አሁን እየታየ ባለው የጸጥታ ችግር ሠላምን ሙሉ በሙሉ ለማስፈን ሂደቱ እና ጉዞው ቀላል እንደማያደርገው ይጠበቃል፡፡ ስለ ሰላማችን ከእኛ በላይ ማን ጠንቅቆ እና አብልጦ ሊያውቅልን አይችልም፡፡ የውጭ አገራት ሸምጋዮቻችንም ሠላም እንዲሰፍን ከራሳቸውን ጥቅም እንዲሁም የሕልውና ስጋት በመነሳት ነውና እነርሱን ለጥረታቸው በማመስገን የራሳችንን ችግር በራሳችን አቅም ፈተን ማሳየት፤ አንድም ብልሃት አንድ በራስ መተማመንን ማሳየት ነው፡፡

> ያለ ሠላም ምንም ማድረግ አይቻልምና ሁሉም ነገር ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ይሆናል። የተራቡትን፣ የታረዙትን፣ የተቸገሩትን ለመርዳት እንኳን የአገር ሠላም መሆን ግድ እና ግድ ነው፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀር አይደለም የሌላውን ጉድለት ለመሞላት ይቅር እና ለራስ መሆንም ብርቅ ይሆናል

ጉልበትም ሆነ አቅም መፈታተሹ ትርፉ ኪሳራ፤ መጨረሻውም ያላማረ እና ሀገሪቱን የቁልቁለት ጉዞ እንድትሄድ የሚያደርግ መሆኑን የሁለት ዓመት የጦርነት ጉዞ በሚገባ የሚያስተምረን ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ታሳቢ በማድረግ በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች የሚታዩን የጸጥታ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ልንፈታ ይገባል።

ቁጭ ብለን ችግሮቻችንን ለዘለቄታው እንዴት እንፍታው? ብሎ ሰከን ብሎ ማሰብ፣ መወያየት መነጋገር እና መተማመንን ይተበቅብናል፡፡ ይህ እንዲሳካ ደግሞ የአገር ሽማግሌዎች ተሰሚነታቸውን እና ቱባ ባህላችንን እንድንጠቀም ድልድይ በመሆን ለተፈፃሚነቱ የድርሻቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

የሀይማት አባቶችም እውነተኛ የሆነውን ፍቅርን፣ መዋደድን፣ ሠላምን እና መተማመንን በመስበክ አርአያነታቸውን በሚገባ ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡ ተከታዮቻቸውን በቃላት ከማስተማር ይልቅ በተግባር የተረጋገጠ አርአያነታቸውን ማሳየትም ይጠበቅባቸዋል፡፡

መንግስትም እንደ መንግስት ስለ ሰላም ሲል ሆደ ሰፊነቱን ማሳየት፤ ለውይይት ፍላጎት ከማሳየት ባሻገር በሰላም ግንባታ ዙሪያ ምሁራን፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን እና መላውን ሕዝብ አቀናጅቶ መንቀሳቀስ ይኖርበታል። የሲቪክ እና ሌሎች ድርጅቶች እንዲሁም ሁሉም ዜጋ የአቅሙን እና የድርሻውን ሚና በመወጣት ስለ አገር ሰላም የበኩሉን አስተዋጽኦ መወጣት ይኖርበታል፡፡

ሀገር ከጥቅም ውጭ ሆና ዳግም ለማቅናት ተጠራርቶ ለመነጋገር እና ለመወያየት ከመምከር ይልቅ ዘመኑ እና ወቅቱ እንደሚፈልገው አስቀድሞ ችግሮችም ከመለየት ባሻገር ችግሮቹን ተወያይቶ እና ተነጋግሮ መፍትሄ ማበጀት ቅድሚያ ብሎም ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው መሆን ያለበት፡፡

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

# መልካም ዓይኖች - ትናንትን ሳለፉ፤ ነገን ለሚያሻግሩ እጆች

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

1996 ዓም፡፡ ተመሳሳይ ስሜትና ፍላጎት፤ አንድ አይነት ዓላማና ግብ ያላቸው ወገኖች ስለ አንድ ወሳኝ ጉዳይ በአንድ ሆነው ሊመክሩ ተገናኙ፡፡ እነሱን መሰል ወገኖች መስራት እየቻሉ የሰው እጅ እያዩ ነው፡ ዕውቀት ችሎታው እያላቸው ዕድል፣ አጋጣሚን ስላጡ ብቻ አስታዋሽ ዓይን አላገኙም። ይህ እውነት በበርካቶች ውስጠት የኖረ ሀቅ ነው፡፡ አሁን ለዚህ እንቆቅልሽ መልስ ለመሻት አንድነት ኃይል ሊሆን እነሆ ጊዜው ደርሷል፡፡

በርካቶቹ አካል ጉዳተኞች ባለባቸው ችግሮች ምክንያት ለበዙ መከራዎች ይጋለጣሉ፡፡ ሰርቶ ለማደርና፣ ቤተሰባቸውን በወጉ ለማስተዳደር አመቺ ሁኔታ ባለመኖሩም፣ የሰው እጅ በማየት ለልመና የሚዳረጉ ጥቂቶች አይደሉም፡፡

ይህን እውነት እየኖሩት ካሉት በርካቶች መሀል «ችግር ይብቃን፣ ራሳችንን እንቻል» ያሉ ሰብሰብ ብለው ስለነጋቸው መከሩ፣ ተማከሩ፡፡ ውሎ አድሮ የምክሩ ሀሳብና ዓላማ የገባቸው ሌሎች ተቀላቀሏቸው። ሁሉም ከዕለት ገቢያቸው እየነጠቁ፣ ያላቸውን እየቆጠቡ፣ ለቁምነገር ተዘጋጁ፡፡ የቻሉ ጥርሳቸውን ነክሰው ቁጠባቸውን ቀጠሉ።

ኑሮና ህይወት ያንገዳገዳቸው ደግሞ ጅምር መንገዳቸው ተቋረጠ፡፡

ከበረቱት ጥቂቶቹ የሀሳባቸው ጉልበት በርትቶ፣ የኪሳቸው አቅም ዳበረ፡፡ ይህኔ ዓላማቸውን ከግብ ሊያደርሱ፣ ሀሳብ ህልማቸውን ሊፈቱ ጥያቄ ይዘው አቀረቡ፡፡ በወቅቱ ከቤት ከጓዳቸው፣ ከልጆቻቸው አፍ እየነጠቁ የቆጠቡት በቂ ጥሪት በእጃው ነበር። ጥያቄው የቀረበለት የመንግሥት አካል ሀሳባቸውን ያስረዱ ዘንድ ዕድሉን ሰጣቸው፡፡

ብርቱዎቹ አካል ጉዳተኞች ውጣ ውረድ የበዛበትን አስቸጋሪ ህይወታቸውን ለማሳየት እማኝ አላሻቸውም።

ፈታኙን ኑሮ የሚለውጥ፣ ታሪካቸውን የሚቀይር ራስን የመቻል ሀሳብ መሰነቃቸውን በዝርዝር አስረዱ፡፡ ለዚህ እቅዳቸው የሚመጥን የመስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸውም ጠየቁ።

በወቅቱ የነበሩ የወረዳ ኃላፊዎች የእነሱን ሀሳብ ላለመቀበል «ጆሮ ዳባ ልበስ» አሉ፡፡ በ«አናውቃችሁም» ሰበብ ፊት ሊያዞሩባቸው ሞከሩ። ይባስ ብሎ ለመሰብሰብና ተገናኝቶ ለመወያየት እንዳይችሉ ገደብ ጣሉባቸው።

ብርቱዎቹ አካል ጉዳተኞች ግን በተስፋ መቁረጥ ዝም አላሉም፡፡ በየዕለቱ በግንባር ተገኝተው ሀሳቡን በሀሳብ ሞገቱ። እንደ ዜግነታቸው መብታቸው ተከብሮ፣ ሊደራጁ፣ ቦታ ሊሰጣቸውና የሥራ ዕድል ሊፈጠርላቸው እንደሚገባ አስረዱ፡፡

የጀመሩት ጉዳይ በወረዳው ላይ ብቻ አልቀረም። ከፍ ብሎ ክፍለ ከተማ የሚያደርሳቸው ሆነ፡፡ አሁንም በስፍራው ሲገኙ የያዙትን ዓላማና የሰነቁትን በጎ ተስፋ ለሚመለከታቸው አካላት አንድ በአንድ ዘረዘሩ፡፡ ሰርቶ በመለወጥ የሚተገብረውን ዕቅድና ያላቸውን አቅም አሳይተው ምላሹን ጠበቁ፡፡

ውሎ አድሮ ሀሳብ ፍላጎታቸው ከልብ ገባ፣ መልካም ዓይኖች በትኩረት አስተዋሏቸው። ጥያቄያቸው ተቀባይነት አግኝቶም የተነፈጉት የመሰብሰብ ዕድል ተፈቀደላቸው። የዓመታት ህልማቸውን ዕውን ሊያደርጉ ሌት ተቀን ባዘኑ። በወቅቱ ጥቂት በጎ አድራጊ ድርጅቶች ዓላማቸውን ደግፈው ከጎናቸው ቆሙ፡፡

1996 ዓ.ም መገናኛ አካባቢ የሚገኝ የማምረቻ ቦታን በሊዝ ተረክበው ሥራ ሲጀምሩ «ብሩክ፣ ሀብታሙና ጓደኞቻቸው» የስጋጃ አምራች ማህበር በሚል ስያሜ ሆነ። በተረፉቸው ገንዘብ የማምረቻ ማሽኖችንና የተለያዩ ቁሶችን አሟሉ፡፡ የልፋታቸው ዋጋ ለተጨማሪ ወገኖች ዋርካ ሆኖ ብዙኃንን አሰባሰበ፡፡

ማህበሩ አካል ጉዳተኞች በራሳቸው አቅም ሰርተው እንዲያድሩ፣ ከልመናና፣ የሰውን እጅ ከማየት ልማድ እንዲላቀቁ ተምሳሌት ሆነ፡፡ በወቅቱ ከሰላሳ በላይ አባላት የነበሩት ይህ ማህበር በእኔነት ስሜት ተመስርቷልና ትርጉሙ ዋጋ አላጣም፡፡ ሁሉም ዕውቀት ጉልበቱን ሰጥቶ የማህበሩን ምሰሶ ሊያቆም ታገለ፡፡

ያለአንዳች ብድርና የመንግሥት እርዳታ ሥራ የጀመረው ማህበር አንዱን ከአንዱ እየሞላ በእንቅስቃሴው ተጓዘ፡፡ መንገዱ ዕዳ ላለመግባትና ላለመክሰር ጥንቃቄ ያለበት ነበር፡፡ እንቅስቃሴው ያለ ማንም ድጋፍና የገንዘብ እገዛ ነበርና በአቅም ማጣት መንገዳገዱ አልቀረም፡፡


ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

የማህበሩ የሥራ ልፋትና የሌት ተቀን ድካሙ የታሰበውን ያህል አልሆነም፡፡ የገበያ ትስስሩና፣ የማቴሪያል አቅርቦቱ ዋጋ መናር ችግር ያስከትል ያዘ። የሚገኘው ገቢ ማነስ ለውጥን ለሻቱት ብርቱዎች ተስፋ አስቆረጠ፡፡ ውሎ አድሮ ችግሩን መቋቋም ያልቻሉ አባላት ከማህበሩ ራቁ፡፡ ሌሎችም በሞት ተለዩ፡፡ ይህ አጋጣሚ የማህበሩን አባላት ቁጥር ዝቅ ማድረጉ አልቀረም፡፡

የማህበሩ ህልውና ግን ከእርምጃው አልተገታም። ከነችግሮቹም ቢሆን መስመሩን ይዞ በጥንካሬ ተጓዘ፡ ፡ ከሚያመርታቸው የስጋጃ ውጤቶች ባሻገር መወልወያ፣ መጥረጊያና ቡሩሽን በተለየ ጥራት እያዘጋጀ በጠባብ ዕድልም ቢሆን ለገበያ ማቅረብ ያዘ፡፡ የሻወር ቤቶችን በመስራት፣ የጓሮ አትክልቶችን በማልማት ለገቢ ምንጬ ታተረ፡፡ ሱቆች ከፍቶ የእጆቹን ጥበብ «እነሆ»አለ፡፡

አቶ ብሩክ መልካሙ የማህበሩ መስራችና ሰብሳቢ ናቸው፡፡ ባለ ትዳርና የሰድስት ልጆች አባትም ናቸው። ድርጅቱ በ1996 ዓ.ም ሲቋቋም ዓላማ አድርጎ የተነሳው አካል ጉዳተኛ ወገኖችን ራስን ለማስቻልና ለልጆቻቸውና ለቀጣዩ ትውልድ የሞራል ስብራት ላለመሆን እንደነበር ይናገራሉ፡፡

በዚህ ሂደት በነበረው ጉዞም ሥራና ተግባራቸው ለሌሎች ጭምር አርአያ መሆኑን ማሳየት ጥረታቸው መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ እንደ አቶ ብሩክ ዕምነት አካል ጉዳተኞች ዕድልና አጋጣሚውን ካገኙ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ የሚያግዳቸው አይኖርም፡፡

በአሁኑ ጊዜ ማህበሩ የተለያዩ አካል ጉዳት ያለባቸውን ወገኖች በአባልነት አቅፎ ይገኛል፡፡ አቶ ብሩክ ደጋግመው እንደሚሉት፤ ይህ ሀሳብ ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ በአስቸጋሪ የኑሮ ፈተና ውስጥ የሚገኙ በርካታ አካል ጉዳተኞች በየቤታቸው ያሉ በመሆኑ እነዚህ ወገኖች በማህበሩ ታዛ ስር ቢካተቱ ምኞታቸው ነው፡፡

አግኝቶ ማደር፣ ሰርቶ መለወጥ የብሩክ፣ ሀብታሙና ጓደኞቻቸው ትጋትና ህልም ነው፡፡ ማንም አካል ጉዳተኛ ባለበት ተጽዕኖ ምክንያት ከቤት መዋልና መቸገር አይኖርበትም ፡፡ ይህን እውነት ከግብ ማድረስ ዓላማው የሆነው ማህበር እስካሁን የራሱን ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል።

በማህበሩ ሰርቶ ለመለወጥ፣ አግኝቶ ለማደር የሚተጉ ነፍሶች ሌት ተቀን መልፋት ልምዳቸው ነው። አንዳንዴ ግን ይህ ልፋት ድካማቸው በአንድ እጅ የማጨብጨብ ያህል ጎዶሎ ይሆናል፡፡ እነዚህ ወገኖች ጥረታቸው ቢቀጥልም ምርቶቻቸውን የሚጎበኙላቸው፣ ለሽያጭ የደረሱትን አይቶ «ልግዛችሁ» የሚላቸውን ጠያቂ አላገኙም፡፡

ትናንት ብዙ ዋጋ ከፍለው ያቋቋሙት ማህበር ዛሬ በዚህ የኑሮ ውድነት አቅም ሊሆናቸው ሲገባ ሆድ ያስብሳቸው ይዟል፡፡ ባላቸው አቅም ተፍጨርጭረው የሚያመርቷቸው ውጤቶች በበቂ ሁኔታ የገበያ ትስስሩን ዕድል አላገኙም፡፡

በዓመት ለጥቂት ቀናት የባዛር ዕድል ቢኖርም በሚገኘው ገንዘብ ዕቃ ከመግዛት የዘለለ ደሞዝ ይሉትን አያውቁትም፡፡ አብዛኞቹ ጧፍ በመሸጥ፣ ቤተሰቦቻቸውን ያኖራሉ፡፡ የማህበራቸው መቆም ህልውናቸው ነውና ዛሬም ከስፍራው አልራቁም። ይህ እውነት በብዙ እየፈተናቸው ያለው ወገኖች አሁን ላይ የብዙኃንን ትኩረት ይሻሉ፡፡

አቶ ብሩክ እንደሚሉት የማህበራቸው መቋቋም ዋና ዓላማ ለጥቂት ሰዎች ብቻ አይደለም፡፡ በብዙ ችግሮች ውስጥ ለሚገኙ በርካታ አካል ጉዳተኞች ጭምር እንጂ፡፡ ያሰቡት ተሳክቶ የልባቸው ቢሞላ ድርጅታቸውን ይበልጥ አስፋፍተው ብዙኃንን የማሳተፍ ውጥን ነበራቸው፡፡

ዛሬ ላይ በዚህ ማህበር በህይወት የተለዩትን ጨምሮ በተስፋ መቁረጥና አቅም ማጣት የራቁት አባላቶች ጥቂቶች አይደሉም፡፡ እንዲህ ለመሆኑ ዋንኛ ምክንያት ከማህበሩ የሚገኘው ገቢ በቂ አለመሆኑና ቋሚ የደመወዝ ተከፋይነት ልምድ አለመኖሩ ነው፡፡

አቶ ብሩክ በሀገራችን በርካታ ባለሀብቶች ስለመኖራቸው ያስታውሳሉ፡፡ በጎ ልቦና ያላቸው ሰዎችም ጥቂቶች አይደሉም ባይ ናቸው፡፡ እነሱ ወደ እነዚህ ወገኖች ቀርበው ማህበሩን ቢጎበኙና የቻሉትን አስተዋጽኦ ቢያደርጉ ድርጅቱ ስብራቱ ተጠግኖ የሚያገግምበት አጋጣሚው የሰፋ ነው፡፡

ይህ ማህበር በዋንኛነት የአካል ጉዳተኞችን ያሰባሰበ ቢሆንም ጉዳት አልባ የሆኑ ጭምር በሙያና በጉልበታቸው ያግዙታል፡፡ እንደ ማህበሩ መስራቾች ዕምነት ድርጅቱ በታሰበው ልክ ቢሰፋ ኖሮ ለበርካታ ወገኖች የገቢ ምንጭ ለመሆን በቻለ ነበር፡፡

አቶ ሀብታሙ አሰፋ የማህበሩ ምክትል ሰብሳቢ ናቸው፡ ፡ በድርጅቱ የሚገኙ አካል ጉዳተኞች የእጅ ጥበብ ለሌሎች በአርአያነት የሚጠቀስ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ እንደሳቸው አባባል በመረሳት ላይ ያለውን የስጋጃ ሥራ ጨምሮ ሌሎችም ምርቶች ባህልና ቅርስን በማቆየት ድርሻቸው የላቀ ነው፡፡ ድርጅቱ በነበረው ጠንካራ እንቅስቃሴ ከሌሎች ወረዳዎች በተሻለ ሞዴል ሆኖ ሲመሰገን ቆይቷል፡፡

እንደ አቶ ሀብታሙ አገላለጽ በአሁኑ ጊዜ ማህበሩ በቀድሞ ማንነቱ እንዳይቀጥል ሌላ ፈተና እየገጠመው ነው፡፡ አካባቢው ለመንገድ ልማት በማስፈለጉ ምክንያት የግቢው ግማሽ ይዞታ እንዲፈርስ ሆኗል። የይዞታው መፍረስ ደግሞ የነበሩ እሴቶችን ጭምር በማክሰም የገቢ ምንጮችን አስቀርቷል፡፡

ይህ ስፍራ በርካታ ጉድለቶችን የሚሞላ፣ ገቢን የሚደጉምና ሰፊ ዕቅድ የታያዘበት ነበርና ብዙ አጉድሏል። እንዲህ መሆኑ ቀድሞ በነበረ ችግር ላይ ሌላ ችግር እንዲደረብ ምክንያት እየሆነ ነው፡፡

ለአካባቢው ማህረበረሰብ ጥቅም ይውሉ የነበሩ የመሸጫ ሱቆች፣ ዘመናዊ የመጸዳጃና የሻወር ቤቶች የማህበሩን ጎን በመደጎም ላቅ ያለ ድርሻ ነበራቸው። እነዚህ ቤቶች በሚገነቡ ጊዜ ከፍተኛ የሚባል ወጪ ተደርጎባቸዋል፡፡ በርከት ያሉ የባህር ዛፎችን ጨምሮ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችም በከተማ ግብርና ዕውቅና የተቸራቸው የማህበሩ ሀብት ንብረቶች ነበሩ፡፡

እንደ አቶ ሀብታሙ አባባል እሳቸውን ጨምሮ ሁሉም የማህበሩ አባላት የአካባቢውን መልማትና ማደግ የሚቃወሙ አይደሉም፡፡ በመጣው ለውጥና ግንባታ ከልብ ደስተኞች ናቸው፡፡ ነገን በተሻለ ለመራመድ የስፍራው መለወጥ በጎ ስለመሆኑ በጽኑ ያምናሉ፡፡

ማህበሩ በራሱ አቅምና በሌሎች አጋርነት ለመስራት ያሰባቸውን ስራዎች ለመከወን ግን ይህ አጋጣሚ ጊዜ የማይሰጥ ፈተና ጋርጦበታል፡፡ ቀድሞ የነበረውን የአቅም ማነስ ለማዳከምም አስተዋጽኦው ቀላል አይደለም። በወቅቱ ከሚመለከተው አካል ዳግም ለመስራት ቃል የተገባላቸው ቢሆንም እስካሁን የተጀመረ ውጥን ባለመኖሩ ሀሳብ ላይ ወድቀዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የብዙዎችን ህይወት የሚፈትነው የኑሮ ውድነት የእነሱንም በር እያንኳኳ ነው፡፡ ለገቢና ትርፍ ሳይሆን የማህበሩን ህልውና ለማቆየት የሚታገሉት አባላት ዛሬም በሌላቸው በቂ አቅም በጥረታቸው መጓዙን ቀጥለዋል፡፡

ሁሉም አባላት በከፍተኛ ድካምና ጥንቃቄ በዓይነሰውራን እጆች የሚሰሩ ምርቶች ገበያ አግኝተው ገቢ ይኖራቸው ዘንድ ይሻሉ፡፡ ባለሀብቶችን ጨምሮ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል ባሉበት ደርሰው ቢጎበኙዋቸው የከበዱ ሸክሞቻቸውን ለማቅለል ይቻላቸዋል፡፡ አቶ ሀብታሙም ይህን መልዕክት ለሚመለከታቸው ሁሉ «ይድረስልን »ይላሉ፡፡

አቶ ካሳዬ ደገፋው በማህበሩ የሂሳብ ሹም በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ይህ ድርጅት ዓላማ ቀርጾ ሲቋቋም በርካታ ዕቅዶችን ሰንቆ እንደሆነ ያስታውሳሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ አባላቱ በገቢ ማነስ፣ በማህበሩ ይዞታ መፍረስና በገበያው ውድነት ምክንያት ፈተና ላይ ወድቀዋል፡፡

ችግሮቹ እንዳሉ ሆኖ ጊዜያዊ መፍትሄ ለመሻት ሁሉም የአቅሙን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ባለው ቦታ ላይ የጓሮ አትክልት በመትከል፣ ገቢ ለማግኘት የሚደረገው ሙከራ እንዳለ ነው፡፡ በአጭር ጊዜ የሚደርሱ ምርቶችንም ለሽያጭ የማቅረብ ዝግጁነቱ አልተቋረጠም፡፡

አቶ ካሳዬ እንደሚሉት የችግሮቹን ቀዳዳዎች ደፍኖ ለማለፍ የሚደረገው ጥረት በሁሉም የማህበሩ አባላት ዘንድ በጽኑ ፍላጎት መከወኑን ቀጥሏል፡፡ ይህ የአንድ ወገን ጥረት ግን ብቻውን ለውጥ አያመጣም። አሁን ላይ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና ህብረተሰቡ «የት ናችሁ? ምን ጎደላችሁ? ቢላቸው ፍላጎታቸው ነው፡፡

አቶ ካሳዬ ማህበሩ ይህን ጥሪ ሲያቀርብ ትኩረት እንጂ እርዳታን እየጠየቀ አለመሆኑን አጽንኦት ይሰጡታል። እንደሳቸው ዕምነት ሌሎች ወገኖች ቀረብ ብለው ምርቶቻቸውን ቢገዙ፣ «አይዟችሁ፣ አለን» ቢሏቸው ስለነገው ሞራላቸው ይገነባል፡፡ በርካታ የሥራ ዕድል ያላገኙ፣ በጎዳናና በቤታቸው የዋሉ ሌሎች አካል ጉዳተኞች ጭምር ይጠቀማሉ፡፡

የአራት ልጆች አባት የሆኑት አባወራ ማህበሩን በሙያቸው ከመደገፍ ባሻገር ለዕለት ጉርሳቸው በየበአላቱ ጧፍ በመነገድ፣ በጓሯቸው ዶሮ አርብተው ዕንቁላሉን በመሸጥ ይተዳደራሉ፡፡ የማህበራቸው ህልውና ግን ዘወትር ከሀሳባቸው ርቆ አያውቅም። እንደ ትናንቱ ጅማሬ ነገን አብቦና ፈክቶ ለፍሬ መድረሱን ይመኛሉ፡፡

ብሩክ፣ ሀብታሙና ጓደኞቻቸው የስጋጃ አምራች ማህበር እንደተቋም ተመስርቶ ስራውን ሲጀምር ታላቅ ራዕይ አንግቦ ነው፡፡ በርካታ አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ሌሎች ወገኖችን በማቀፍ ውጤት ያለው ተግባር ማከናወንም ቀዳሚ የሚባል ዕቅዱ ነበር፡፡

ይህ ማህበር ዛሬ ላይ ባሉበት ተደራራቢ ችግሮችና መሰል ምክንያቶች ህልውናው አደጋ ላይ ይገኛል፡፡ ይህን ስጋት ለመቅረፍና መፍትሄ ለመሻትም ለአባላቱ ጥረት ጊዜ መስጠት የግድ ይላል፡፡ ዛሬ ትናንትን በጽናት ያለፉ፣ ነገን በብርታት የሚያሻግሩ ጥበበኛ እጆች ትኩረትን ይሻሉ፡፡

የገበያ ትስስሩን በማቀላጠፍ፣ ምርቶች ለሽያጭ እንዲቀርቡ፣ ገቢው እንዲዳብርና የላብ ፣ የልፋት ዋጋ ከግምት እንዲገባ የሁሉም አካላት ትብብርና የትኩረት ዓይኖች ሊገለጡ ይገባል፡፡ እንዲህ ከሆነ የጥበብ እጆች አይነጥፉም፤ የሚሮጡ እግሮች አይዝሉም፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## አባባ ማሙሽ እና እማማ ሚጡ

**መክሊት ወንድወሰን**

የምንኖርባት ዓለም በየቀኑ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸውን አዳዲስ የሚወለዱ ሕፃናትን ታስተናግዳለች። በዚህም የህዝብ ቁጥር ከቀን ወደ ቀን ይጨምራል። ሀገራት የሚኖራቸው የህዝብ ቁጥር መጨመር ደግሞ በተለምዶው በ"ሶስተኛው ዓለም" ወይም በታዳጊ ሀገራት ላይ በስፋት ይስተዋላል፡፡

ይህ ትዝብቴ ግን በእናታቸው ማህጸን ዘጠኝ ወራትን ቆይተው ስለሚወለዱ ጨቅላ ሕፃናት ሳይሆን፣ በምድር ቆይታቸው በሥራና ኃላፊነታቸው "አንቱ" ወይም፣ "አዋቂ" የሚሰኙ፤ በተግባራቸው ግን ማሙሽና አቡሽ ስለሆኑ ሰዎች ነው፡፡ በዚች አጭር ጽሑፍ የትኛውን አንስቼ የትኛውን እንደምተወው ባላውቅም፤ በየዘርፉ "ትልልቅ" የሚባሉ ሰዎች በእድሜ የማይመጥናቸውን ሥራ ሲሠሩ ይስተዋላል፡፡ ‹‹ምነው ትልቅ ሰው አይደለህ/ሽ፣ ፊደል አልቆጠርክም/ሽም›› የሚሉ ቃላትም ትልቅ ከምንላቸው/ከምናከብራቸው ሰዎች ያልተለመደ ተግባር ስናይ የምንጠቀማቸው ቃላት ናቸው፡፡ አባባ ማሙሾች እንዴት ያሉት እንደሆኑ እና እነማን እንደሆኑ አንድ ሁለት ብዬ አስታውሳችኋለሁ፡፡ እርግጠኛ ነኝ አንባቢያን ታውቋቸዋላችሁ፡፡

አባባ ማሙሾች ከቤታችን ውጪ የምንጠቀምባቸው የህዝብ መገልገያዎችን በኃላፊነት የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ እስኪ ስንቶቻችን ነን የመስሪያ ቤቶቻችን መጸዳጃ ቤት ውስጥ የምናያቸው ግድ የለሽ አጠቃቀሞች፤ በእውኑ እዚህ መጸዳጃ ቤት ውስጥ ሕፃናት ናቸው ወይስ በእውነት አብረውን የሚውሉት ባለሱፍና ባለ ክራቫቶቹ የቢሮ ሰራተኞች ናቸው የሚገለገሉበት? የምንለው። በመጸዳጃ ቤቱ ውስጥ ውሃ ቢኖርም የተጠቀሙበትን ለማጽዳት እጃቸው የማይዘረጋ፣ በመጸዳጃ ቤቱ በር ላይ የተለጠፉ መመሪያና ማስጠንቀቂያዎችን ችላ የሚሉ እና ለጽዳት ሰራተኞች ጉልበት ቦታ ባለ መስጠት ጥፋትን ይሰራሉ፡፡ ጽዳትን ከድመት እንኳን የማይማሩ ከውጪ አንቱ የሚባሉ፤ ሰው በማያያቸው ቦታና ሰአት ነውርን እና ጥፋትን የሚፈፅሙ ናቸው፡፡

ሌላኛዎቹ አባባ ማሙሾች እና ሚጡዎች ደግሞ ከትዳራቸው ውጪ የሚወሰልቱ ሴቶችና ወንዶች፣ በእድሜ ከሚያንሷቸው ጋር የሚወሰልቱ ባለትዳር ወንዶች ናቸው፡፡ ባለቤቱ በማን እንደሆነ ባይታወቅም እንደነዚህ አይነት ሰዎችን ‹‹ወመሽ›› (ወጣት መሳይ ሽማግሌ) የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ተቀባይነትንም አግኝቶ መታወቂያቸው ሆኗል።

ከነሱ እድሜ ያነሱ፣ በወጣትነት እድሜ ላይ የሚገኙ ከስነ-ምግባር ታርቀው ራሳቸውን በጤነኛ ግንኙነት ውስጥ አድርገው ህይወታቸውን ይመራሉ። ሰዎችን ከትምህርት ቤት ባሻገር እድሜና ህይወት ይበልጥ ያስተምራል ሲባል ብንሰማም እነዚህ ሰዎች ግን በዚህ አጸያፊ ተግባር ላይ ተሰማርተው የመገኘታቸው ምክንያት መለከፍ (ልክፍት) እንጂ ሌላ ምን ምክንያት ሊገኝለት አይችልም፡፡

ሌላው አባባ ማሙሽ ደግሞ በትዳር ውስጥ ሁሉንም የቤት ውስጥ ኃላፊነቶች ሚስት እንድትወስድ የሚፈልግ ነው፡፡ ትዳር በሁለት ሰዎች ጥምረት የሚመሰረት ተቋም ሲሆን ቤቱን የማቅናት ኃላፊነትም የሁለቱ ሰዎች ነው፡፡ አንዳንዶች ግን ሚስት ማለት ሞግዚት የምትመስላቸውና ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይቅርና ከወለዷቸው ልጆች እኩል ትኩረትና እንክብካቤን የሚሹ፤ "የሚበላ በጊዜ አልቀረበልኝም፤ ልብሴ ታጥቦ አልተተኮሰም፤ ጫማዬ የታለ?" የሚሉ ጥያቄዎችን በማግተልተል ሌላ ሸክም ይሆናሉ፡፡

ሚስት እንክብካቤን የምትሻ፤ ተፈጥሮ በራሱ ብዙ ሸክሞችን ያሸከማት በመሆኗ እነዛን ሸክሞች ደግሞ አብራው እንድትኖር ከመረጠችው አጋሯ በተሻለ ሌላ ማንም ሊካፈላት የማይችል በመሆኑ አባባ ማሙሾች የትዳር አጋሮቻቸውን የመርዳትም የመረዳትም ኃላፊነታቸውን ማስታወስ ይገባቸዋል።

እነዚህ የልጅነት ባህሪ የሚያጠቃቸው ሰዎች አንዳንዴ ደግሞ ታክሲ ላይ ያጋጥማሉ፡፡ የጫኑት የሰው ህይወት የማይመስላቸው ለራሳቸውም ለተሳፋሪዎቻቸውም ግድ የሌላቸው እና እንደ ልጅነት ጊዜያቸው በጓደኞቻቸው ላለመቀደም በውድድር የተጠመዱ ናቸው፡፡ የያዙት የህዝብ መጓጓዣ ሳይሆን የስፖርት ውድድር መኪና የሚመስላቸው። ‹‹ኧረ ቀስ ብለህ ንዳ፤ የምን መንቀዥቀዥ ነው›› ለሚለው አስተያየት ቦታ የሌላቸው። ፈጣሪን የማይፈሩ፣ ኃላፊነት የጎደላቸውና በልጅነታቸው የተጫወቱትን የሽቅድድም ውድድር ዛሬ ላይም በሰው ህይወት ሊያስቀጥሉ የሚዳዳቸው ናቸው፡፡

ድሮ ድሮ አስታውሳለሁ "እከሌ እከሌን ትችለዋለህ?" እንዴታ፣ አናፍጠዋለሁ። ሌላኛውን ወገን ደግሞ "አንተስ? እሱ አናፍጠዋለሁ እያለ ነው"፤ "አይ እኔ ድብድብ አልወድም፤ እናቴ ትቆጣኛለች" ሲል ዛሬ ተደባድበህ እራስህን አታስከብርም፤ ፈሪ" ይለዋል አንድ የቦክስ ዳኛ የሆነ የሚመስለው እና ሰውን ከሰው በማፋጀት መከባበር ያሰፈነ የሚመስለው የጸብ ጫሪነት ጂኒ ያለበት ሕፃን፡፡

ልጆቹም ፈሪ ላለመባልና ሁሌ ሲሰደቡ ላለመኖር በማሰብ ጸብ ይጀምራሉ፡፡ አንዱ ይመታል፤ ሌላው ደግሞ ተመቶ ወደ ቤቱ ይገባል፡፡ ነገር ግን፣ ዛሬ ይመታ እንጂ ነገ ተደራጅቶ ወይም ተዘጋጅቶ ብድሩን ይመልሳል፡፡ ይሄ ነገር አዙሪት ስለሚሆን መቼም የማይቆምን ጠብ ይወልዳል፡፡

ታዲያ ይህ አይነቱ በልጅነት የሚጠናወት ጂኒ ባህር ማዶ ድረስ ተከትሎ ይሄድና በሰላም አብሮ ሲኖር የቆየን ማህበረሰብና ህዝብ ማባላት ይጀምራል። እሱ ልጆቹን የሞቀ ፍራሽ ላይ እያስተኛ ሰዎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለጎዳና እንዲዳረጉ ያደርጋል፡፡ ያኔስ አለማወቅ ነው፤ ልጅነት ይሆናል ተብሎ የሚታለፈው ስህተት ዛሬ ላይ ስህተት ብቻ ነው ለማለት አያስደፍርም፤ እጅግ አረመኔያዊ ተግባር ነው፡፡

እንደዚሁ ሁሉ እነእማማ ሚጡም አሉ፡፡ የእናት አባቶቻቸው ትከሻ ላይ ተቀምጠው ለቤተሰቦቻቸው ሸክም የሚሆኑ፤ በውበታቸው ተመክተው ከወንድ ወንድ እያቀያየሩ የሰዎችን ትዳር የሚያፈርሱ፤ የሴቶች እኩልነት ማለት ምን እንደሆነ በትክክል ያልተረዱ፡፡

እንደልጅነታቸው ካልታዘልን፤ እንኮኮ ካልተባልን የሚሉና ዛሬም ራሳቸውን ላለመቻል እንቶፈንቶ ምክንያትን እየደረደሩ ሰው ላይ ሸክም የሚሆኑ እና በስሌት በመኖሪያቸው ሰአት በስሜት የሚኖሩ እማማ ሚጡዎች አሉ፡፡ ልክ ልጅ የቤተሰቦቹን ኪስ እንደማይረዳ ሁሉ የባሎቻውን የኪስ ሁኔታ ከመረዳት ይልቅ እራሳቸውን ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር እያወዳደሩ ያላቸውን ሳይሆን የሌላቸውን በመቁጠር የትዳራቸውን ሰላም የሚያደፈርሱ፤ የያዙት ህይወት እና ኑሮ መሆኑን ረስተው በፉክክር መድረኮቻቸውን ጎልተው ለመታየት ባሎቻቸውን ጎል የሚከቱ ናቸው፡፡

በዚህ ነገር ስንቱ ባል እንደተፈተነ ቤት ይቁጠረው። "እኔ አልሰርቅም፤ ህዝቤን አልበድልም፤ አደራ አላጎድልም" ሲል በሴቶች የነገር መርፌ ጠቅ ተደርገው ወደ ወንጀል እና ሙስና የገቡት። እንደዚህ አይነት አባዜ ያለባችሁ ሴቶች እባካቹ አድቡ፡፡ ቁመት መለካካት በልጅነታችን የቀረና ሰው እንደቤቱ እንጂ እንደጎረቤቱ አይኖርም የሚልን አስተሳሰብ ከጭንቅላታሁ አስገብታችሁ ባላችሁ ነገር መደሰት ባትችሉ እንኳን ሰላማችሁን ለማስጠበቅ ስሩ የሚለው የበርካቶች ምክር ነው።

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ለሕንድ የ4 ቢሊዮን ዶላር ድሮን ሽያጭን አጸደቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአሜሪካ የውጭ መሥሪያ ቤት አራት ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ 31 ወታደራዊ ሰው አልባ አውሮፕላኖች (ድሮኖች)፣ ሚሳኤሎች እና ሌሎች ወታደራዊ ቁሶች ለሕንድ በሽያጭ እንዲተላለፉ አጸደቀ።

ኤምኪው-9ቢ ፕሪዴተር የተባለው ድሮን ለሕንድ በሽያጭ እንደሚተላለፍ ይፋ የተደረገው የሕንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ ባለፈው ዓመት ሰኔ በአሜሪካ ጉብኝት ባደረጉ ወቅት ነበር።

ይሁን እንጂ ኅዳር 2016 ዓ.ም. በአሜሪካ ምድር የሕንድ ዝርያ ባለው ግለሰብ ላይ ግድያ ለመፈጸም የሕንድ መንግሥት አሲሯል መባሉን ተከትሎ ምርመራ እንዲደረግ ከተወሰ በኋላ የሽያጭ ስምምነቱ እንዲዘገይ ተደርጎ ነበር።

ስምምነቱ በኮንግረሱ ከጸደቀ በኋላ የጦር መሳሪዎቹ ለሕንድ በሽያጭ ይተላለፋሉ ተብሏል።

ይህ ስምምነት 31 ኤምኪው-9ቢ ስካይጋርዲያን ድሮኖች፣ 170 ኤጂኤም-114አር ሄልፋየር ሚሳኤል እና የተለያዩ ዓይነት ቦምቦች፣ የግንኙነት እና የስለላ መሳሪዎችን እንደሚያካትት የአሜሪካ መከላከያ መሥሪያ ቤት ፔንታገን አስታውቋል።

የሕንድ መንግሥት ተሳታፊ ሳይሆን አይቀርበትም የተባለውን የግድያ ሴራን ሲመረምሩ የነበሩት የሴኔት ኮሚቴ አባሉ ሴናተር ቤን ካርዲን፣ የአሜሪካ መንግሥት ጉዳዩ ላይ ዝርዝር ምርመራ ለማድረግ ከተስማማ በኋላ የጦር መሳሪያ ሽያጭ ስምምነቱ ላይ ተጥሎ የነበረው ገደብ እንዲነሳ መስማማታቸውን ሮይተርስ የዜና ወኪል ዘግቧል።

የባይደን አስተዳደር ምርመራ አድርጎ ተጠያቂነትን እንደሚያረጋግጥ ተስማምቷል ያሉት ሴናተር ካርዲን፤ መሰል እንቅስቃሴዎች የሕንድ መንግሥትን ተጠያቂ የሚያደርጉ ናቸው ብለዋል።

ከጥቂት ወራት በፊት ዋሽንግተን አሜሪካዊ ዜግነት ያለው እና ከሕንድ ተገንጥላ ካሃሊስታን የተባለች ሉዓላዊት ሀገር ለመመሥረት የሚንቀሳቀስ ሕንዳዊ የዘር ግንድ ያለውን ግለሰብ አሜሪካ ምድር ላይ ለመግደል ዴልሂ አሲራለች ብላ ነበር።

የሕንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ግን የሀገሪቱ መንግሥት በጉዳዩ ምንም ተሳትፎ እንደሌለው ገልጿል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ጨምሮም ከአሜሪካ ዘንድ የቀረበውን ክስ እና የደኅንነት ስጋት የሚያጣራ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ያሉበት ኮሚቴ ማቋቋሙን አስታውቋል።

ሐሙስ ዕለት ፔንታገን ወታደራዊ ቁሶቹ ለሕንድ በሽያጭ መተላለፋቸው የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን ከመደገፉ በላይ የአሜሪካ-ሕንድ ስትራቴጂካዊ ግንኙነትን ያጠናክራል ብሏል።

## በኬንያ መዲና ናይሮቢ በተከሰተ ከባድ የጋዝ ፍንዳታ ቢያንስ ሦስት ሰዎች ሲሞቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ቆሰሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በኬንያ መዲና ናይሮቢ የጋዝ ሲሊንደር በጫነ መኪና ላይ በተከሰተ ፍንዳታ ቢያንስ ሦስት ሰዎች ሕይወታቸው ሲያልፍ ወደ 300 የሚጠጉ ሰዎች ላይ ጉዳት ደረሰ።

አደጋው ከባድ ፍንዳታ ያደረሰው ሐሙስ ዕኩለ ሌሊት አካባቢ መሆኑን የኬንያ መንግሥት ቃል አቀባይ ገልጸው፣ በአካባቢው በነበሩ ተሽከርካሪዎች እና መኖሪያ ቤቶች ላይ ጉዳት አድርሷል።

አደጋውን ተከትሎ በማኅበራዊ ገጾች የተለቀቁ ቪዲዮዎች ፍንዳታው ባጋጠመበት አካባቢ ያሉ መኖሪያ ቤቶች፣ ሕንጻዎች እና ተሽከርካሪዎች በእሳት ተያይዘው አሳይተዋል።

ከአደጋው በኋላ 271 ሰዎች ባጋጠማቸው ጉዳት ከተማ ውስጥ ወደ ሚገኙ የተለያዩ ሆስፒታሎች መወሰዳቸው እና ተጨማሪ 27 ሰዎች ደግሞ እየተፈለጉ እንደሆነ የኬንያ ቀይ መስቀል ማኅበር ገልጿል። የአደጋው መንስኤ እየተጣራ ነው።

የመንግሥት ቃል አቀባዩ አይዛክ ማውራ አደጋው ኬንቴኔሪ በተባለ ድርጅት ውስጥ መከሰቱን ተናግረዋል።

አይዛክ በኤክስ ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ ድርጅቱ ጋዝ እየሞላ ሳለ አደጋው ማጋጠሙን አንስተው በርካታ ሰዎች ወደ ሆስፒታል መዋሰዳቸውን ጠቁመዋል።

"ድርጅቱ የነበረበት ህንጻ ክፉኛ ተጎድቷል። የእሳት አደጋው መንስኤ እስካሁን አልታወቀም። የነፍስ አድን ሥራው በመቀጠሉ ነዋሪዎች ወደ አካባቢው ከመጓዝ መቆጠብ አለባቸው" ሲሉ መክረዋል።

የተከሰተው እሳት ወደ ሌሎች የመኖሪያ ህንጻዎች ተዛምቶ ስለነበረ የሟች እና የተጎጂዎች ቁጥር ሊጨምር እንደሚችል ተሰግቷል።

ስፍራው ላይ የነበሩ የዓይን እማኞች ፍንዳታው ሲያገጥም መሬት ሲንቀጠቀጥ ተሰምቶናል ብለዋል።

ከተጎዱት መካከል ቦንፌስ ሲፉና የተባለ ነዋሪ "ከሲለንደሩ ፍንዳታ ለማምለጥ ስሞክር ቃጠሎ አጋጥሞኛል" ሲል ለሮይተርስ የዜና ወኪል ገልጿል።

"ሲሊንደሩ የፈንዳው ከፊት ለፊቴ ነው። በነበልባሉ ተሸፍኜ ወድቄ ነበር። ዕድለኛ ነኝ ከአደጋው ለማምለጥ አቅም አግኝቻለሁ" ሲል አክሏል።

ሌላ ስሙ ያልተጠቀሰ የዓይን እማኝ ደግሞ ለኔሽን ጋዜጣ በሰጠው አስተያየት፤ "ከፍተኛ ፍንዳታ ነበር። እሳቱም ከፍተኛ ነበር። ሰዎች እየጮኹ ወደ ሁሉም አቅጣጫ ይሮጡ ነበር" ብሏል።

ስፍራው ላይ ይኖር የነበረ የኔሽን ጋዜጠኛ በአካባቢው ላይ የነበሩ ሁሉም ሰዎች ከፍንዳታው በኋላ ቤታቸውን ጥለው መሄዳቸውን ተናግሯል።

የኬንያ ቀይ መስቀል ማኅበር አደጋውን ለመቆጣጠር "ያለድካም እየታገለ እንደሆነ" በማኅበራዊ ትስስር ገጹ አሳውቋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ነፃ ሃሳብ

# "የፕሪቶርያው ስምምነት ከምንም በላይ ተግባራዊ ምላሽ ይፈልጋል"

*- የመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት*

ሕወሓት ከሰሞኑ ባወጣው መግለጫ የፕሪቶሪያው ስምምነት እንዲከበር መጠየቁን የፌዴራል መንግሥት በአንክሮ ተመልክቶታል፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ዋነኛው መፍትሔ የፕሪቶርያውን ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ መሆኑን የኢፌዴሪ መንግሥት በጽኑ ያምናል። ይሄንንም በተመለከተ የፌዴራሉ መንግሥት ከመነሻው እስከ አሁን ያለው አቋም ወጥ እና የማይናወጥ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የፕሪቶርያው ከአቋም ባሻገር ተግባራዊ እንቅስቃሴም አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል። የፌዴራል መንግሥቱ ለሰላም፣ ለፖለቲካዊ መፍትሔና ለትብብር ያለውን አቋም የገለጠው ከፕሪቶርያው ስምምነት በፊት ጀምሮ ነው፡፡ የመከላከያ ሠራዊቱ ወደ መቀሌ ከተማ እንዳይገባ የተደረገው ለሰላም ዕድል ለመስጠት ነው፡፡

ከስምምነቱ በኋላ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተመራ የተለያዩ ተቋማት አመራሮች ያሉበትን ቡድን ወደ ትግራይ የላከው የፌዴራል መንግሥት ነው፡፡ የፌዴራል መንግሥት ተቋማትና ክልሎች ለትግራይ ሕዝብ ድጋፋቸውን ያሳዩት ወዲያው ነው፡፡ የክልል ፕሬዚዳንቶች በመቀሌ ተገኝተው ለሕዝቡ ያላቸውን አጋርነት በማሳየት የሚቻላቸውን ድጋፍ በዓይነትና በገንዘብ አድርገዋል።

በፕሪቶርያው ስምምነት መሠረት የገዢው ፓርቲ ሊኖረው የሚችለውን ድርሻ በመተው ሕወሓትና የታጣቂ አመራሮች ጊዜያዊ መንግሥቱን እንዲያቋቁሙ አድርጓል፡፡ ምክንያቱም ከልዩ ልዩ አካላት ተውጣጥተው በጊዜያዊ አስተዳደሩ ውስጥ የሚካተቱ አመራሮች እስኪተዋወቁና እስኪግባቡ ድረስ የትግራይ ሕዝብ የችግር ወቅት እንዳይራዘም በማሰብ ነው፡፡ በዚህም ለትግራይ ሕዝብ ሰላም ያለውን ቁርጠኝነት ከፕሪቶርያው ስምምነት በላይ በመሄድ አረጋግጧል፡፡

ለትግራይ ሕዝብ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ እንዲቻል የባንክ፣ የቴሌኮም፣ የመንገድ፣ የጤና፣ የትምህርትና የርዳታ ሥራዎችን የሚመሩ የሥራ ኃላፊዎች በትግራይ ተገኝተው ከክልሉ ቢሮዎች ጋር እንዲወያዩ የተደረገው የፕሪቶርያ ስምምነት በተፈረመ በሳምንታት ጊዜ ውስጥ ነው። እነዚህ የሥራ ኃላፊዎች በጀትና ባለሞያዎችን በመመደብ በክልሉ መሠረታዊ አገልግሎቶች እንዲጀመሩ አስችለዋል፡፡

በክልሉ ተቋርጦ የነበረውን የትምህርት ሂደት ለማስቀጠል ልዩ ልዩ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ የሰው ኃይልና የተቋም ዐቅም ግንባታ፣ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ላይ ሥልጠና፤ የዩኒቨርሲቲዎችን የአመራር ቦርድ የማደራጀት ሥራ ተሠርቷል፡፡ በትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም በኩል 165.8 ሚልዮን ብር በዕቅድ ተካትቶ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ ለአንደኛና ለሁለተኛ ሩብ ዓመታት ማስፈጸሚያ 517.9 ሚልዮን ብር በገንዘብ ሚ/ር በኩል ለክልሉ ተልኳል፡፡

በትምህርት ላይ ከሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት 1.46 ቢልዮን ብር ድጋፍ የተደረገ ሲሆን፣ በ2016/17 በትምህር ቤቶች ላይ ለሚሠሩ ሥራዎች የ111.08 ሚልዮን ብር ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ የትምህርት ተቋማት መልሶ ግንባታ 441.5 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ተደርጓል። ከዚህም በተጨማሪ የኦሮሚያ ክልል የ5 ሚልዮን፣ የአዲስ አበባ አስተዳደር ደግሞ የ109 ሚልዮን ብር የትምህርት ድጋፍ አድርገዋል፡፡

የክልሉን የማዕድናት ልማት ወደሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ ለዘርፉ መሥሪያ ቤት የመገልገያ ቁሳቁሶች ድጋፍ ተደርጓል፤ የክልሉን የኢንቨስትመንት አማራጮች የሚያሳይ ኤግዚቢሽን በሚሌኒየም አዳራሽ በፌዴራል ወጪ ተከናውኗል፡፡ የሞሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ወደ ሥራ ተመልሷል፡፡ በፋብሪካና በባህላዊ መንገድ ወርቅ የሚያመርቱ አካላትን በመደገፍ ሥራ ጀምረዋል፡፡ ለወርቅ ሥራ የሚያገለግሉ ሁለት ከባድ ተሽከርካሪዎች በርዳታ ተለግሰዋል፡፡

በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል የክልሉን የዘርፍ መሥሪያ ቤት ለማጠናከር ከተወሰዱ ርምጃዎች ባሻገር ለካፒታል በጀት 4.9 ቢልዮን ብር፤ ለመደበኛ በጀት 11.4 ቢልዮን ብር፣ እንዲሁም ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ 400 ሚልዮን ብር፤ በድምሩ 16.7 ቢልዮን ብር በ2015/16 ለክልሉ ተሰጥቷል፡፡ በክልሉ ለሚገኙ አራት ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ በድምሩ 5.1 ቢልዮን ብር ተላልፎላቸዋል፡፡ በልማት አጋሮች በኩል ደግሞ የ1.7 ቢልዮን ብር ድጋፍ ለትግራይ ክልል እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ከእነዚህም በተጨማሪ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ በቻናል አንድ 1.7 ቢሊዮን እንዲሁም የገንዘብ ሚኒስቴር በክልሉ ባቋቋመው ጽ/ቤት በኩል፣ በትግራይ ለሚከናወኑ የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች እና ለአየር ንብረት ለውጥ ፕሮጀክቶች በድምሩ ከ565 ሚልዮን ዶላር በላይ ፈሰስ ተደርጓል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ ፕሮጀክትም 65 ሚሊዮን ብር ለክልሉ ተላልፏል። የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እና የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በክልሉ የሚገኙ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶችንና ተቋማትን ለማብቃት ሥልጠና ሰጥተዋል፤ ቁሳቁስ አሟልተዋል፤ የገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጾታን መሠረት ላደረጉ ጥቃቶች የምላሽ አገልግሎት የሚውል ከ7 ሚልዮን ዶላር በላይ ለክልሉ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡ የክልሉን ማረሚያ ቤቶች ለመደገፍም የ28 ሚልዮን ብር ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የከተማና መሠረተ ልማት አገልግሎቶችን ለማጠናከር ሲባል የቢሮ ዕቃዎችና የተሽርካሪዎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ክልሉ መሠረተ ልማቶችን ለመሥራትና ለመጠገን እንዲችል ከፍተኛ ወጪ የሚያወጡ የግንባታና የጥገና ማሽነሪዎች ተሰጥተውታል፡፡ በጦርነቱ የተጎዱ ድልድዮችን በጊዜያዊነት ለመጠገን እንዲቻል ሁለት ተገጣጣሚ ድልድዮች የተለገሱ ሲሆን አራት ድልድዮችን ለመገንባት ጨረታ ወጥቷል፡፡ በጦርነቱ ወቅት የተቋረጡ የዐቅም ግንባታ ሥልጠናዎችንም በልዩ ፕሮግራም የክልሉ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ለዘጠኝ ከተሞች የፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚውል ከ409 ሚልዮን ብር በላይ እና ከ7 ሚልዮን ዶላር በላይ ለክልሉ ተላልፏል፡፡

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደርም ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ እና ለመንገድ ፕሮጀክት ጥገና ከ418.6 ሚልዮን ብር በላይ ወደ ክልሉ ልኳል፡፡ ለትግራይ ገጠር መንገድ ጥገና ከመንገድ ፈንድ ከብር 107 ሚልዮን ብር በላይ፤ የ2026 በጀት ቅድመ ክፍያ ከ50 ሚልዮን ብር በላይ ተልኳል፡፡ በፕላንና ልማት ኮሚሽን በኩል ደግሞ በጠቅላላው የ4.2 ሚልዮን ብር ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የትግራይ ክልልን የባህልና ስፖርት እንቅስቃሴ ከተቋረጠበት ለማስጀመር የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና የሚመለከታቸው የስፖርት ፌዴሬሽኖች ተገቢውን ድጋፍ ከማድረጋቸውም በላይ የተለያዩ የስፖርት እንቅስቃሴዎች በክልሉ እንዲከናወኑ አድርገዋል። ለክልሉ የስፖርት ክለቦችም የገንዘብ ማሰባሰብ ሥራዎችን ሠርተዋል፡፡

የክልሉን የጤና ዘርፍ ዐቅም ለመገንባት እንዲቻል 164 ልዩ ልዩ ባለሞያዎች ተመድበው ድጋፍ እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡

ሁሉንም በክልሉ የሚገኙ የጤና ተቋማት በመደገፍ ወደ አገልግሎት ለመመለስ የተቻለ ሲሆን፣ ሁሉም ሆስፒታሎች ተኝቶ የማከም አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ተችሏል፡፡ ከ830ሺ በላይ ሕጻናት የኩፍኝ ክትባት ከማግኘታቸውም ሌላ ከ65ሺ በላይ ሕዝብ የኮቪድ ክትባት አግኝቷል። ከአምቡላንሶች በተጨማሪ ወደ 2 ቢልዮን ብር በሚጠጋ ወጪ የመድኃኒትና የሕክምና መሣሪያዎች ድጋፎችም ተከናውነዋል፡፡ በ2015/16፣ ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ከ600.2 ሚልዮን ብር በላይ ለትግራይ ክልል የጤና ዘርፍ የገንዘብና የግብአት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ትግራይ በቱሪዝም ሀብት የታወቀ ክልል ነው፡፡ ይሄንን ሀብት መልሶ ወደ ጥቅም ለማዋል እንዲቻል ቱሪስቶችን የማበረታታት ሥራ ተጀምሯል፡፡ አልነጃሺ መስጊድንና የገርዓልታ ገዳምን ለቱሪስቶች የማስከፈት እንቅስቃሴም ተከናውኗል፡፡ የውኃ ሀብትን ለመጠቀምና ውኃን ለሕዝቡ ለማዳረስ እንዲቻል ለዘርፉ ተቋም ልዩ ልዩ ድጋፎች የተደረጉ ሲሆን፣ የክልሉን ቢሮ የማደራጀትና በቁሳቁስ የማሟላት ሥራ ተሠርቷል፡፡ ለተበላሹ የአገልግሎት ሰጪ ሀብቶችም ጥገና ተከናውኗል፡፡

በክልሉ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎችን መልሶ ወደ ሥራ ለማስገባት በተደረገው ሁለገብ እንቅስቃሴ 217 ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ ለማስገባት ተችሏል። ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ የገበያ ትሥሥር እንዲፈጠር በተለያዩ ባዛሮችና ኤክስፖዎች ላይ የትግራይ ክልል ኢንዱስትሪዎች እንዲሳተፉ ተደርጓል። የመሠረታዊ ሸቀጦችን ተደራሽነት ለማስፋት መንግሥት በወሰደው ርምጃ የተለያዩ የምግብና የመጠቀሚያ ሸቀጦች ለትግራይ ክልል ቀርበዋል፡፡

የነዳጅ ማደያዎችን እንዲጠገኑ በማድረግ፣ በክልሉ በቂ ነዳጅ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ የትግራይ ክልል ንግድ ፈቃድ ላላቸው 7240 ነጋዴዎች፣ ከተለመደው አሠራር ወጣ ብሎ ከሐምሌ 1/2014 ጀምሮ በአዲስ አበባ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

የትግራይን ክልል የግብርና ሥራ በማሳለጥ ገበሬው የሚገባውን ያህል ምርት እንዲያገኝ ሲባል 51.3 ሚልዮን ብር ለዘር ግዥ ወጪ ተደርጓል፡፡ በ2015/16 13.4 ሚልዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለክልሉ የቀረበ ሲሆን፣ ለ1427 አርሶ አደሮች መጠቀሚያ የሚሆን 1720 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ በዚሁ የምርት ዘመን ፕሮጀክቶች በኩል ለክልሉ ተገዝቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

በ2015/16 የምርት ዘመን ክልሉ 80ሺ የተለያዩ ማዳበሪያዎች ጠይቆ ሁሉም ቀርቦለታል፡፡ ለ2016/17 ምርት ዘመን ደግሞ ክልሉ ከጠየቀው መካከል የ70ሺ ቶን ማዳበሪያ ተገዝቷል፡፡ ለግብርና መገልገያ የሚሆኑ የትራክተሮች፣ የውኃ ፓምፖች ድጋፍ ለአርሶ አደሮች ተለግሷል፡፡ በልማታዊ ሴፍቲኔት በኩል 6.2 ሚልዮን ብር የተላለፈ ሲሆን፣ የዓለም ምግብ ፕሮግራምና የግብርና ሚኒስቴር ባደረጉት ስምነት መሠረት ደግሞ 7መቶ ሺ ኩንታል እህል ተገዝቶ ለክልሉ ቀርቧል፡፡ ለ55 ወረዳዎች በየወረዳው አንዳንድ መኪናና ሞተር ሳይክል፤ እንዲሁም ኮምፒውተሮችና ፕሪንተሮች ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በዘላቂ የመሬት አስተዳደር ፕሮግራም አማካኝነትም 89.2 ሚልዮን ብር ለክልሉ በቁሳቁስ መልክ ተሰጥቷል፡፡ ከኦሮሚያ ክልል ብቻ 11ሺ ኩንታል ምርጥ ዘርና 30 ትራክተሮች ለትግራይ ገበሬዎች ተለግሷል። ሌሎች ክልሎችም ተመሳሳይ ድጋፍ አድርገዋል።

የዊዝሆልዲንግ ታክሶችን ጨምሮ ብር 3.9 ቢልዮን ብር ወደ ክልሉ ትልልፍ ተደርጓል፡፡ ከክልሉ ግብር ከፋዮች የተሰበሰበ ብር 138.06 ሚልዮን ብር ወደ ክልሉ ሂሳብ ተላልፏል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለተጠቀሱትና ለሌሎችም ወጪዎች ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ ከ37 ቢልዮን ብር በላይ የፌዴራል መንግሥት ለትግራይ ክልል ድጋፍ አድርጓል፡፡ በተመደበው በጀትና ድጋፍ የክልሉ ዕቅድ ተግባራዊ ተደርጎ ለሕዝብ ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣም ይጠብቃል፡፡

ተፈናቃዮችን ወደ መደበኛ መኖሪያቸው ለመመለስ እንዲቻል የፌዴራሉ መንግሥት የሚመለከታቸውን አካላት አቀናጅቶ ሥራ ጀምሯል። በአንዳንድ አካባቢዎችም ትክክለኛ ተፈናቃዮችን ወደ መኖሪያቸው እንዲመለሱ አድርጓል፡፡ የአከራካሪ ቦታዎችን ሁኔታ በዘላቂነት ለመፍታትም በሕገ መንግሥቱ መሠረት ሕዝበ ውሳኔ እንዲደረግ ጉዳዩ በዋናንት ከሚመለከታቸው ከአማራና ከትግራይ ክልሎች ጋር መግባባት ላይ ተደርሶ ነበር።

በፕሪቶሪያው ስምምነት መሠረት በሕወሓት በኩል ታጥቀው ሲዋጉ የነበሩ ታጣቂዎች ወደ ሰላማዊ ኑሮ መመለስ አለባቸው፡፡ ለዚህም የሚረዳ የተሐድሶ ኮሚሽን የፌዴራሉ መንግሥት አቋቁሟል። በፌዴራሉ መንግሥት በኩል የሚጠበቅበትን የሰው ኃይልና በጀትም መድቧል፡፡ ከሰሜኑ ጦርነት ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን በተመለከተ የፌዴራል መንግሥቱ ተገቢውን ርምጃ በእርሱ በኩል ወስዷል። ተጠያቂ መሆን ያለባቸውንም ተጠያቂ አድርጓል፡፡

ሌሎች ሥራዎችንም ለማከናወን እንዲቻል የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዐዋጅ ረቂቅ ዝግጅት አጠናቋል፡፡ ይህ ሂደት እንዲሳካም እንደ ሌሎቹ ክልሎች ሁሉ የትግራይ ክልልም ተገቢው ሚና እንዲጫወት ይጠበቃል፡፡ ለትግራይ ሕዝብ ሰላም፣ ልማትና ደኅንነት ሲባል የፌዴራሉ መንግሥት እነዚህን ተግባራት ከሚገባው ባሻገር ተጉዞ አከናውኗል። ለክልሉ ሕዝብ መደረግ ያለባቸው ድጋፎችንም በራሱ ዐቅምም ሆነ ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ለማከናወን የፌዴራሉ መንግሥት ምንጊዜም ዝግጁ ነው፡፡

አሁንም ቢሆን ለትግራይና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም፣ ልማትና ደኅንነት ሲባል የፕሪቶርያውን ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ በሚያደርጉ፤ የክልሉን ዕቅዶች ወደ መሬት በሚያወርዱ፤ የክልሉን ሕዝብ ችግሮች በተጨባጭ ለመፍታት በሚያስችሉ ገቢራዊ ነገሮች ላይ ማተኮር አማራጭ የሌለው ነው ብሎ የፌዴራሉ መንግሥት ያምናል፡፡ እነዚህ ነገሮች ተግባራዊ ተደርገው የትግራይ፣ በአጠቃላይም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም፣ ልማትና ደኅንነት እንዲረጋገጥ የፌዴራል መንግሥቱ ያለውን ቆራጥ አቋም በድጋሚ ያረጋግጣል፡፡

የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትም ለፕሪቶሪያው ሰላም ስምምነት መፈጸም ሙሉ ድጋፋቸውን እንዲያደርጉ የፌደራል መንግሥቱ ጥሪውን ያቀርባል።

ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ
የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

# ስፖርት

## በቦስተን የቤት ውስጥ ውድድር ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች የበላይነቱን ለመቀዳጀት ይሮጣሉ

ብርሃን ፈይሳ

በዓለም አትሌቲክስ መሪነት በተለያዩ ዓለማት የቤት ውስጥ ቱር ውድድሮች እየተካሄዱ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከወር በኋላ በግላስኮ ከሚካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና አስቀድሞ የሚደረገው ቱር የተለያዩ ደረጃዎች ያሉት ሲሆን፤ የወርቅ ደረጃ ከተሰጣቸው መካከል የሆነው የቦስተን ኒው ባላንስ ግራንድ ፕሪክስ ከነገ በስቲያ ይደረጋል፡፡ ለሁለት ቀናት በሚደረገው በዚህ ውድድር ላይም ኢትዮጵያዊያኑን ጨምሮ በርካታ ስመጥር አትሌቶች ተካፋይ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

እአአ ከ1996 አንስቶ ይህንን ውድድር በማካሄድ ላይ የሚገኘው ቦስተን ጠንካራ አትሌቶችን በማፎካከር የሚታወቅ ሲሆን፤ በርካታ የዓለም ክብረወሰኖች በተለያዩ ርቀቶች የተሰበሩበት ስፍራም ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች መሰረት ደፋር እና ጥሩነሽ ዲባባ (ለሁለት ጊዜ) ይገኙበታል፡፡ ከነገ በስቲያ በሚደረገው በዘንድሮው ውድድር ላይም በሴቶች የ5ሺህ ሜትር እንዲሁም በ3ሺህ ሜትር የወንዶች የዓለም ክብረወሰን ባለቤቶቹ ጉዳፍ ጸጋይ እና ለሜቻ ግርማ ተሳትፏቸውን ማረጋገጣቸውን ተከትሎ በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ በጉጉት እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

የመካከለኛና ረጅም ርቀት አትሌቷ ጉዳፍ ጸጋይ የውድድር ዓመቱን የመጀመሪያ ሩጫዋን በካዛኪስታን እንደምታደርግ ቢጠበቅም ከሳምንታት በፊት መሰረዟን አስታውቃ ነበር፡፡ አትሌቷ ባራዘመችው የውድድር መርሃ ግብሯ መሰረትም ከነገ በስቲያ ቦስተን ላይ የተለመደ አስደማሚ ብቃቷን ለማሳየት ተዘጋጅታለች፡፡ የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮናን ጨምሮ በኦሊምፒክ፣ በዓለም ቻምፒዮና፣ በዳይመንድ ሊግ፤ እንዲሁም በሌሎች ውድድሮች ኢትዮጵያን ያስጠራችው የ5ሺህ ሜትር ንግስቷ ጉዳፍ ከሃገሯ ልጆች ጋር በመሆን በ1ሺህ 500 ሜትር ትሮጣለች፡፡



አትሌት ጉዳፍ ጸጋይ፤



አትሌት ለሜቻ ግርማ፤

አትሌቷ ከቡዳፔስቱ ስኬታማ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና መልስ በዳይመንድ ሊግ የ5ሺህ ሜትር ክብረወሰን መስበሯ የሚታወስ ነው፡፡ በብቃቷ ጫፍ ላይ የምትገኘውን ምርጧን አትሌት በቤት ውስጥ ውድድርም ስኬታማ ስትሆን፤ እአአ 2016 በፖርትላንድ ሃገሯን በመወከል የነሃስ ሜዳሊያ አጥልቃለች። ኢትዮጵያ ከዓለም አንደኛ ደረጃን ይዛ ባጠናቀቀችበትና ከሁለት ዓመት በፊት ቤልግሬድ ላይ በተደረገው ቻምፒዮና ደግሞ የወርቅ ሜዳሊያ ነበር ያስመዘገበችው፡፡ የአትሌቲክስ አፍቃሪያን በፓሪሱ ኦሊምፒክ ላይ ሊመለከታት የሚጓጓላት ጉዳፍ ባለችበት ወቅታዊ አቋም በቱር ውድድሩ ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ ሀገሯን ለምትወክልበት ቻምፒዮና በቀጥታ ከመሳተፍ ባለፈ በ1ሺህ 500 ሜትር የቤት ውስጥ የዓለም ክብረወሰን የመጨበጥ እድሏ ከፍተኛ እንደሚሆንም ይጠበቃል፡፡

ልምድ ያላት ጉዳፍ ከወጣቶቹ አትሌቶች አያል ዳኛቸው እና ብርቄ ኃየሎም ጋር ውድድሩ ላይ የምትሳተፍ ሲሆን፤ ሌሎች ተፎካካሪዎች ፈተና መሆናቸው አያጠያይቅም። ምክንያቱ ደግሞ በዓለም የወጣቶች ቻምፒዮና የ800 እና 1ሺህ 500 ሜትር አሸናፊዎች የሆኑት አያል እና ብርቄ ጠንካራ ተፎካካሪና ለአሸናፊነትም ተጠባቂ በመሆናቸው ነው፡፡ በዚሁ ርቀት በወንዶች በኩል አትሌት ዮናስ አስማረ እና ሳሙኤል ዘለቀም ተካፋይ መሆናቸው ታውቋል፡፡

ሌላኛው የቻምፒዮናው ተጠባቂ ውድድር በወንዶች 3ሺህ ሜትር ሲሆን፤ ውድድሩን ከሚያደምቁ አትሌቶች መካከል አንዱ የሆነው ለሜቻ ግርማ ነው፡፡

በዓለም ቻምፒዮና የሶስት ጊዜ እንዲሁም በኦሊምፒክ አንድ ጊዜ የብር ሜዳሊያ ያገኘው ወጣቱ አትሌት ኢትዮጵያን በ3ሺህ ሜትር መሰናክል ካስጠሩ ጥቂት አትሌቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ቤልግሬድ ላይ በነበረው ቻምፒዮናም በተመሳሳይ የብር ሜዳሊያውን መውሰድ ችሎ ነበር፡፡ አትሌቱ ባለፈው ዓመት ሌቪን ላይ በተደረገው የቤት ውስጥ ቱር ውድድር ርቀቱን 7:23.81፣ ከቤት ውጪ ደግሞ 7:52.11 በሆነ ሰዓት በመሸፈን ሁለቱንም ክብረወሰኖች ከእጁ ማስገባቱም አይዘነጋም፡፡ ይህም ውድድሩን አጓጊ የሚያደርገው ሲሆን፤ ተፎካካሪዎቹን በአሳማኝ ብቃት በመርታት ግላስኮ ላይ ኢትዮጵያን የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት ያደርጋታል በሚልም ይጠበቃል፡፡

በዚህ ውድድር ከለሜቻ ባሻገር ወንድሙ ድሪባ ግርማ እና ሳሙኤል ፍሬው ለአሸናፊነት የሚፋለሙ አትሌቶች ናቸው፡፡ በርቀቱ በሴቶች በኩል ደግሞ አትሌት መዲና ኢሳ፣ መልክናት ውዱ፣ ፈንታዬ በላይነህ፣ ሰናይት ጌታቸው እንዲሁም አይናዲስ መብራቱ ይሮጣሉ፡፡ በየውድድሩ ተግባራዊ በማድረግ በሚታወቁበት ቅንጅት የሚሮጡት ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ለተፎካካሪዎቻቸው ስጋት በመሆን የበላይነቱን እንደሚወስዱም ይገመታል፡፡

እያንዳንዱ የቱር ውድድር አትሌቶች በሚኖራቸው ተሳትፎ የሚያስመዘግቡት ነጥብ ተደምሮ ከሚያገኙት ከፍተኛ መጠን ያለው ሽልማት ባለፈ በዓለም አቀፉ ቻምፒዮና በቀጥታ ሃገራቸውን ወክለው የሚሳተፉበትን እድል ሊያስገኝላቸው ይችላል፡፡ የዘንድሮው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና በእንግሊዟ ግላስኮ አዘጋጅነት ለ19ኛ ጊዜ ይደረጋል፡፡